ትምህርት ሦስት

ተሠገዎ፥ ክፍል አንድ

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍለ ትምህርቶች ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም እግዚአብሔር ፍጹም ሰው መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተምረናል። ነገር ግን ይህ ሊሆን የማይችል ይመስላል! አንድ ሰው እንዴት እግዚአብሔርም ሰውም ሊሆን ይችላል? ክርስቲያኖች ይህን ጥያቄ ለሁለት ሺህ ዘመናት ሲጠይቁ ቆይተዋል። እኛም ለሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ይህንኑ ጥያቄ ሲያስነሣ የኖረውን የተሠገዎ ታላቅ ምሥጢር ጠለቅ ብለን እናጠናለን። በዚህ ሳምንት ግን፥ ስለ ኢየሱስ ተሠገዎ ማለትም ስለ እርሱ ሰብአዊም አምላካዊም ባሕርይ ደህና አድርገው የሚገልጹና ጠቃሚ የሆኑ ሦስት የማስረጃ ጥቅሶችን ከአዲስ ኪዳን ውስጥ እናጠናለን። ከዚያም ቤተ ክርስቲያን በጥንታዊ ታሪኳ ውስጥ ስለ ተሠገዎ እንዴት ግንዛቤዋን እያሳደገች እንደ መጣች መቃኘት እንጀምራለን። በሚመጣው ሳምንት ደግሞ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ስለ ተሠገዎ እያዳበረች ስለመጣችው ግንዛቤ ማጥናታችንን የምንቀጥል ስንሆን፥ አያይዘንም በኢትዮጵያ ስላለው የተሠገዎ አስተምህሮ እናጠናለን። በመጨረሻም፥ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎች ስለ ተሠገዎ ስላላቸው ግንዛቤ እንመለከታለን። ስለሆነም በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ ግባችን የሚሆነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ተሠገዎ የሚናገረውን መገንዘብና ለዛሬዪቱ ኢትዮጵያ በግልጽና በትክክል ማስረዳት ይሆናል።

የመጀመሪያ ቀን— ተሠገዎ በዮሐንስ 1

ዛሬ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሠገዎ የሚናገር፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚ ክፍለ ምንባቦች መካከል አንዱ የሆነውን ዮሐንስ 1፡1—14 ያለውን ጥቅስ በጥንቃቄ እናጠናለን። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ዮሐንስ ደጋግሞ ስለ «ቃል» ይናገራል። ይህን ክፍለ ምንባብ ከማጥናታችን በፊት አስቀድመን መጠየቅ ያለብን፥ «ዮሐንስ ስለ ቃል ሲናገር ምን ማለቱ ነው?» «ቃል» ማለት በግሪኩ ሎጎስ ማለት ነው። በዓለማዊው የግሪክ ፍልስፍና እሳቤ «ሎጎስ» ከዚህ ከሚታየው ፍጥረት በስተጓላ ያለና ሁሉም ነገር በእርሱ ህልውናን የሚያገኝበት መለኮታዊ መንሥዔ ማለት ነው። እንደዚሁም የሰው ነፍስ መሠረት «መነሻ» ወይም «ውስጣዊ እሳቤ» ማለትም ነው። ነገር ግን ለግሪኮች ሎጎስ ግላዊ ወይም ተሠገዎ አልነበረም።

1ኛ ጥያቄ፥— ዘፍጥረት 1፡3፥ 6፥ 9፥ 14፥ 20፥ 24፤ መዝሙር 33፡6—9፤ 107፡20፤ ዘዳግም 32፡46—47፤ ኢሳይያስ 55፡11 አንብቡ። በእነዚህ ምንባቦች መሠረት የእግዚአብሔር ቃል ምን ያደርጋል?

ዕብራውያን ብሉይ ኪዳንን ወደ ግሪክ በተረጎሙ ጊዜ «ሎጎስ» የተባለውን ቃል ተጠቅመውበት ነበር። የእግዚአብሔር ሎጎስ ይፈጥራል (ዘፍጥረት 1፤ መዝሙር 33፡6)፥ ሕይወትን ይሰጣል (ዘዳግም 32፡46—47)፤ ይፈውሳል (መዝሙር 107፡20)፤ የእግዚአብሔርን ድኅነት ይፈጽማል (ኢሳይያስ 55፡11)፥

የእግዚአብሔር ቃል እርሱ ኃያልነቱን በፍጥረት ውስጥ የሚያሳይበት ግልጸተ መለኮትና አርነት ነው።

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ውስጥ ዮሐንስም ይህን ጥንታዊ የግሪክና የዕብራውያንን አሳብ በመውሰድና በማዳበር ስለ ኢየሱስ አዲስ ነገር ግንሊያስተምር ችሎአል።

1. «ቃሉ» ማን ነበር?

2ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 1፡1–5 አንብቡ። ስለ «ቃል» በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ እውነት የሆኑትን ሁሉ ጻፉ። ስድስት ልዩ ልዩ ነገሮችን ለማግኘት ሞክሩ።

3ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 1፡1 አንብቡ። ዮሐንስ ቃል ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት የተናገረውን ዘርዝሩና አስረዱ።

በመጀመሪያዎቹ አምስት ቁጥሮች ላይ ዮሐንስ «ስለ ቃል» ስድስት ልዩ ልዩ ነገሮችን ያስረዳል።

1. በመጀመሪያ ቃል ነበረ። ዮሐንስ፡ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» ሲል ቃል ያልነበረበት ጊዜ በፍጹም አልነበረም ማለቱ ነው። ማንኛውም ነገር ከመጀመሩ በፊት ቃል ነበረ። ቃል ባለፉት እልፍ ዘመናት ለዘላለም ነበር። ለዘላለም የነበረው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ እንግዲህ ይህ በሌላ አባባል ቃል እግዚአብሔር ነው ማለት ነው።

2. ቃልም ከእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ቃል ከእግዚአብሔር ተለይቶ የሚታወቅና ከእግዚአብሔርም ጋር ግንኙነት ወይም አንድነት ያለው ነው።

3. ቃልም እግዚአብሔር ነው። ሆኖም ቃል ከእግዚአብሔር ጋር ነበር ማለት ብቻ አይበቃም። ቃልም እግዚአብሔር ነበር። በመጀመሪያው ትምህርታችን ላይ እንደተመለከትነው፥ ኢየሱስ እግዚአብሔር ለመሆኑ ይህ ከግልጽ ማረጋገጫዎች መካከል አንዱ ነው። ዮሐንስ ቃል በእግዚአብሔር ወይም በመለኮት የሚመሰል ነው አላለም። እርሱ የሚለው ቃል ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ነው። ዮሐንስ ቃል ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ይህ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ሊል እንዴት ቻለ? እንደ ሰው አስተሳሰብ ከሆነ ይህ ስሜት የሚሰጥ አይደለም። ነገር ግን ዮሐንስ የፈለገው ከሰዎች አስተሳሰብ የተለየ ገለጻ ለማቅረብ ነበር። በአንድ መንገድ ቃል እግዚአብሔርም ነው፥ ከእግዚአብሔር የተለየም ነው። ዮሐንስ እንድንገነዘብ የፈለገው የኢየሱስ ቃላትና ተግባራት የእግዚአብሔር የራሱ ቃላትና ተግባራት መሆናቸውን ነው።

4ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 1፡3 አንብቡ። እንደዚህ ጥቅስ ከሆነ፥ ዓለምን የፈጠረው ማን ነው?

4. ቃል ዓለምን ፈጠረ። የእግዚአብሔር ዓለምን መፍጠር በቃሉ ሆነ (ዘፍጥረት 1–2)። እግዚአብሔር ብቻ ሊፈጥር ስለሚችል፤ ቃል

እግዚአብሔር ለመሆኑ ይህ ሌላ ማረጋገጫ ነው። እንደዚሁም ጊዜና ፍጥረት ሲጀመር ቃል ነበር የሚለውንም እንደገና ያጠናክራል።

5ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 1፡4–5 አንብቡ። ሀ) የሕይወት ምንጭ ማን ነው? ለ) ዮሐንስ፥ «ብርሃን» ሲል ምን ማለቱ ይመስላል? ሐ) ብርሃን ምን አደረገ?

5. ቃሉ ለሰዎች መንፈሳዊ ብርሃንን የሚሰጥ የሕይወት ምንጭ ነው። በራሱ ሕይወት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ሕይወትን ስለሚሰጣቸው፥ ዕጽዋት፥ እንስሳትና ሰዎች ሕይወት አላቸው። ነገር ግን ይህ ጥቅስ ቃሉ በራሱ ሕይወት አለው ይላል። ማንም ለእርሱ ሕይወትን አልሰጠውም፤ እንዲያውም እርሱ ለሌሎች የሕይወት ምንጭ ነው። ስለሆነም ኢየሱስ እግዚአብሔር ለመሆኑ ይህ ጥቅስ ተጨማሪ ምስክር ነው። ቃሉ የሕይወት ምንጭ እንደ መሆኑ፥ ለሌሎች መንፈሳዊ ብርሃንን ይሰጣል። ዮሐንስ ቃል የሰዎች ብርሃን ነው ሲል ቃሉ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያስተውሉት፥ እንዲያዩትና እንዲያውቁት ያደርጋል ማለቱ ነው። ዮሐንስ፥ ኢየሱስ መለኮትና ሰው መሆኑን ማመልከቱን ይጀምራል። ቃል እግዚአብሔር ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔርም ደግሞ ራሱን ለሰዎች የገለጠበት መንገድ ነበር።

6. የቃሉም ብርሃን በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ በራ፥ ነገር ግን በጨለማ የሚኖሩት ሕዝቦች ሊገነዘቡት አልቻሉም ወይም ጨለማው አላሸነፈውም። ቃሉ ከእርሱ በተለዩ እርሱንም ባላወቁ ሰዎች መካከል እግዚአብሔርን ገለጠ። ነገር ግን ምንም እንኳን ቃሉ እግዚአብሔርን ቢገልጥላቸውም፤ እነርሱ ግን ሙሉ በሙሉ አልተገነዘቡትም፥ አላወቁትም። «አላሸነፈውም» የሚለው ቃል በኦሪጅናል ግሪክ ውስጥ ሁለት ትርጉሞች አለው። «አላሸነፈውም» ወይም «አልተገነዘበውም» ማለት ነው። ምናልባት ዮሐንስ ሁለቱንም ትርጉሞች እንድናጤን ፈልጎ ይሆናል። በኢየሱስ ዙሪያ የነበረው መንፈሳዊ ጨለማ አላሸነፈውም፤ ነገር ግን እርሱ ስለ እግዚአብሔር ስለሚገለጠው ነገርም አልተገነዘበም።

እነዚህ ጥቅሶች ስለ ተሠገዎ ምሥጢር ጥቂት ጠቃሚ ማብራሪያዎችን ይሰጡናል። ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ይነግሩናል። እርሱ ለዘላለም የነበረ፥ ፈጣሪና የሕይወት ምንጭ መሆኑን ይገልጡልናል። ይሁን እንጂ ኢየሱስ እግዚአብሔር ቢሆንም ይህ ለሰው ግንዛቤ አስቸጋሪ ነው። እንደዚሁም እርሱ ከእግዚአብሔር የተለየ ነው። ቃሉ ሰው ሆኖ ለመኖር በምን ምክንያት ወደ ምድር መጣ? ቃሉ ለማያውቁት ሁሉ መንፈሳዊ ብርሃን ሊሰጥና እግዚአብሔርንም ሊገልጥላቸው ወደዚህ ምድር መጣ። ምንም እንኳን ቃልን የተገናኙ አብዛኛዎቹ እርሱ ስለ እግዚአብሔር ምንን እንደሚገልጥ ባይገነዘቡም፥ እግዚአብሔርን ለዓለም ለመግለጥ የነበረውን ዓላማ ሊሽሩት አልቻሉም።

6ኛ ጥያቄ፡– በግላችሁ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እንዴት ገለጠላችሁ?

ሐዋርያው ዮሐንስ ከቁጥር 6–8 ላይ የመጥምቁ ዮሐንስን ሥራ በአጭሩ ይገልጻል። ሥራው ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ማመላከት ነበር። ከዚያም ስለ ኢየሱስ መናገሩን ይቀጥላል።

2. በቃልና በዓለም መካከል የነበረው ግንኙነት ምን ነበር?

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1፡9–13 ባለው ክፍል በቃልና በዓለም መካከል ስላለው ግንኙነት ይገልጻል። ስለዚህ ግንኙነትም ሦስት ነገሮችን ያስረዳል።

7ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 1፡9–13 አንብቡ። እነዚህ ጥቅሶች ስለ ቃልና ዓለም የሚናገሩትን ጻፉ። ቢያንስ ሦስት ልዩ ልዩ ነጥቦችን ለማግኘት ሞክሩ።

8ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 1፡9፤ 3፡19–21፤ 8፡12፤ 9፡39–41 አንብቡ። ብርሃኑ ምን ያደርጋል?

1. ዮሐንስ በምዕራፍ 1፡9 ውስጥ የኢየሱስ መምጣት ለሕዝቡ ሁሉ እግዚአብሔርን የሚገልጥ ብርሃን እንደሆነ ይናገራል። በተቀረውም የወንጌሉ ክፍል ኢየሱስ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ሲገልጥ እንመለከታለን። ይሁን እንጂ ሰዎች ልባቸውን ከፍተው ኢየሱስ እግዚአብሔርን መግለጡን ሁልጊዜ አይቀበሉም። አንዳንድ ጊዜ ብርሃኑን ችላ ይሉታል። ነገር ግን እርሱ ብርሃን በመሆኑ፥ እግዚአብሔርን እየገለጠ፥ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ውሳኔ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ለማገናኘት ዓይነተኛው መንገድ ከክርስቶስ ጋር ማገናኘት ነው።

9ኛ ጥያቄ፡– ኢየሱስን እንድታምኑ ያደረጋችሁ ምንነቱ ነው? ሌሎች ሰዎች ክርስቶስን እንዲያምኑ፥ የግል ልምምዳችሁን እንዴት ትጠቀሙበታላችሁ?

10ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 1፡10–11 አንብቡ። አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ኢየሱስን እንዴት ተቀበሉት?

2. ምንም እንኳን ኢየሱስ እግዚአብሔርን ለዓለም ያሳየ ብርሃን ይዞ ቢመጣም፥ የዓለም ሕዝብ ግን እርሱነቱን አላወቁትም ወይም አልተቀበሉትም። የኢየሱስ የራሱ ወገን የነበሩ አይሁዳውያን እንኳን ከእግዚአብሔር እንደ ተላከና፥ እግዚአብሔርንም ለእነርሱ የሚገልጥ መሆኑን አላወቁትም ወይም አልተቀበሉትም። ምንም እንኳን ኢየሱስ እግዚአብሔርን የሚያንጸባርቅ ብርሃን ቢሆንም፥ አብዛኛዎቹ ሰዎች ይገልጥላቸው የነበረውን ሊቀበሉ ፈቃደኞች አልሆኑም።

11ኛ ጥያቄ፡– ለምንድን ነው ዛሬ ሰዎች ኢየሱስን ለማወቅም ሆነ ለመቀበል አሻፈረን የሚሉት? ሰዎች እግዚአብሔር ስለ ኢየሱስ ሲገልጥላቸው ለመቀበል እምቢ የሚሉባቸውን አንዳንድ ሁኔታ ጻፉ።

12ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 1፡12–13 አንብቡ። ሀ) አንዳንድ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ምን ያስባሉ? ለ) ታዲያ የዚህ ዓይነት ስሜት ያላቸው ምን ሆኑ?

3. ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ የዓለም ሕዝቦች ኢየሱስን መቀበል ችላ ቢሉም፥ የተወሰኑ ተቀብለውታል። የተቀበሉትም እግዚአብሔርን ለእነርሱ በእውነት መግለጡን አምነዋል። እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነት የተገለጠላቸው መሆኑን አምነው የተቀበሉት የእግዚአብሔር ልጆች ሆኑ። የእግዚአብሔር ልጅ መሆን፥ ነገር ግን እንደ ሰብአዊ ሕፃን ሆኖ መወለድ አይደለም። ይህ የሥጋና የደም ልደት አይደለም፥ ወይም አንድ ባል ልጅ ለማግኘት ፈልጎ እንደሚወለድለት ያለ ልጅነትም አይደለም። የእግዚአብሔር ልጆች የሚሆኑት ኃይልን በተሞላ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ተግባር ነው።

ዮሐንስ 1፡9–13 ውስጥ ወንጌላዊው የተሠገዎ ምሥጢርን ያብራራና ይህ የክርስቶስ ተሠገዎ ለዓለም ስለነበረው ዓላማና ስላስከተለው ውጤት ይናገራል። ቃል እግዚአብሔርን ሊገልጥ ወደ ዓለም መጣ። በዓለም ያሉ አብዛኛዎቹ ሰዎች ግን ማንነቱን አውቀው አልተቀበሉትም። ሆኖም ጥቂቶቹ ተቀበሉት። የተቀበሉት ሁሉ ግን በእግዚአብሔር በራሱ ሉዓላዊ አሠራር ታላቅ የልጅነት መብትን አገኙ።

3. ማጠቃለያ፡ – ቃሉ በምን ምክንያት ወደ ዓለም መጣ?

በዮሐንስ 1፡14 ውስጥ ሐዋርያው ዘላለማዊው ቃል ለምን ወደ ዓለም እንደ መጣ ሲናገር የነበረውንና ያብራራውን ያጠቃልላል።

13ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 1፡14 አንብቡ። ሀ) በቃሉ ላይ ምን አዲስ ነገር ሆነ? ለ) ቃሉ «በእኛ መካከል ያደረው» ውጤት ምን ነበረ?

14ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 1፡17–18 አንብቡ። ሀ) ሙሴ ምንን ገለጠ ለ) ኢየሱስ ምንን ገለጠ? ሐ) ሰዎች እግዚአብሔርን ሊያውቁ የሚችሉበት ተመራጭ መንገድ ምንድን ነው?

15ኛ ጥያቄ፡– ዘፀአት 40፡34–35 አንብቡ። እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበሩ ጊዜ የእግዚአብሔርን ክብር እንዴት አዩት?

ሐዋርያው ዮሐንስ በምዕራፍ 1፡14 ውስጥ አዲስ ነገር መፈጸሙን ይነግረናል። ቃል «ሥጋ ሆነ» ይለናል። ዮሐንስ ሲናገር፥ ቃል ራሱን በሥጋ ሸፈነ፥ ወይም ወደ ሰው አካል ገባ አላለም። በአንጻሩ ግልጽ አድርጎ ሥጋ ሆነ ሰውም ሆነ ይላል። በተሠገዎ ኢየሱስ በውስጥ እግዚአብሔር ሲሆን፥ በውጪአዊው ደግሞ ሰው ነበር ብለን ላለማሰባችን ዮሐንስ እርግጠኛ መሆን ይፈልጋል። እኛ እግዚአብሔር የሆነው ዘላለማዊው ቃል (ዮሐንስ 1፡1–5) ሙሉ በሙሉ ሰው ስለመሆኑ ግንዛቤ መጨበጣችንን ለማረጋገጥ ይፈልጋል። እግዚአብሔር ቃል፥ ራሱን ለሰው ልጆች ለመገለጥ ብሎ ሰው ሆኖአል።

ዮሐንስ አክሎም ቃል ሥጋ ሆነ «በእኛም አደረ» ይላል። «በእኛ አደረ» የሚለው በግሪክ ቃል በቃል ሲፈታ፥ «በመካከላችን ድንኳኑን ተከለ» ማለት ይሆናል። ምናልባት ዮሐንስ «ድንኳኑን ተከለ» ሲል አንባቢዎቹ እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበሩ ጊዜ ያመልኩበት የነበረውን የማደሪያውን ድንኳን እንዲያስታውሱ ለማድረግ ሳይሆን አይቀርም (ዘፀአት 40፡34–35)፥

በምድረ በዳ በነበሩ ጊዜ በሲና ተራራ ትይዩ በነበረው ድንኳን ላይ እግዚአብሔር እንዴት እንደ ወረደ እንዲያስቡም ፈልጎአል። አንባቢዎቹ የኢየሱስን በመካከላቸው መገኘት በዚያን ጊዜ በማደሪያው ድንኳን ላይ ያንጎብጎብ በነበረው የክብር ደመና ውስጥ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል እንደ መገኘቱ አድርገው እንዲረዱት ፈልጓል።

እግዚአብሔር ቃል ለአጭር ጊዜ በመካከላችን በመቆየቱ ምክንያት፥ እግዚአብሔርን በአዲስና በተለየ መንገድ ልናውቀው ችለናል። የእግዚአብሔርን ክብር አይተናል። የእግዚአብሔርን ጸጋና እውነትም አይተናል። እግዚአብሔርን ከኢየሱስ መምጣት በፊት ይቻል ባልነበረ ሁኔታ ልናየው ችለናል። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ይታወቅ የነበረው በሙሴ ሕግ አማካይነት ነበር (ዮሐንስ 1፡17)። ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና እውነት በኢየሱስ በኩል ሊታወቅ ይቻላል። ምንም እንኳን እግዚአብሔርን አብን ፊት ለፊት ያየው ባይኖርም፥ እግዚአብሔርን ልናውቀው ግን እንችላለን። እንዴት? በኢየሱስ አማካኝነት እናውቀዋለን። ኢየሱስ እግዚአብሔርን ይገልጣል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ በመሆኑ፥ እርሱ ከሁሉ በላይ የሆነ የእግዚአብሔር መግለጫ ነው።

ዮሐንስ 1፡1–18 ያለው ክፍል ስለ ተሠገዎ ምሥጢር ሦስት ጠቃሚ ትምህርቶችን ይሰጠናል፡– 1) ዘላለማዊው ቃል እግዚአብሔር ነበር እና ዘመናት ከመቆጠራቸው በፊትም እንኳ እግዚአብሔር ነበር። 2) በታሪክ ውስጥ በአንድ ወቅት ዘላለማዊው ቃል ሰው ሆነ። 3) ሰዎች እግዚአብሔርን ያውቁት ዘንድ እግዚአብሔር ቃል ሰው ሆነ። አብዛኛዎቹ ግን አላወቁትም። ጥቂቶች ግን አውቀው ተቀበሉት። እነዚህ የአወቁትና የተቀበሉት የእግዚአብሔር የራሱ ልጆች ሆኑ።

16ኛ ጥያቄ፡– በሕይወታችሁ ውስጥ ኢየሱስን በማየት እግዚአብሔርን ማወቅ ስለሚገባቸው ሰዎች አስቡ። ከዚያም ስሞቻቸውን ጻፉ። በዚህ ሳምንት ኢየሱስን ለእነዚህ ሰዎች እንዴት ታቀርባላችሁ? ቃል ሳትናገሩ በድርጊት ብቻ ኢየሱስን ልታሳዩዋቸው የምትችሉባቸውን ሁኔታዎች አስቡ። ቀጥሎም ሳታስቀይሟቸው ኢየሱስን ልትገልጹላቸው የምትችሉበትን አነጋገር አስቡ። ኋላም አሳባችሁን ጻፉ።

17ኛ ጥያቄ፡– እናንተስ ኢየሱስን በተሻለ ሁኔታ እንዴት እያወቃችሁት ነው? ከዮሐንስ ወንጌል አንድ ምዕራፍ መርጣችሁ አሁኑኑ አንብቡ። ከዚያም ስለ ኢየሱስ ክፍሉ የሚያስተምራችሁን ጻፉ። ቀኑንም ስታስቡት ዋሉ። ከዚያም ተመልሳችሁ ኢየሱስን በማወቃችሁ እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ እንዴት እንዳወቃችሁት ጻፉ።

ሁለተኛ ቀን – ስለ ተሠገዎ በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 2

ትናንትና ስለ ኢየሱስ ተሠገዎ የሚያስተምር በጣም ጠቃሚ ከሆኑ ጥቅሶች መካከል አንዱ የሆነውን ዮሐንስ ምዕራፍ አንድን አብረን አጥንተናል። ዛሬ ደግሞ ሌላ በጣም ጠቃሚ የሆነና ስለ ተሠገዎ ምሥጢር የሚያስረዳውን ከፊልጵስዩስ 2፡5–11 ያለውን ክፍል እንማራለን።

18ኛ ጥያቄ፡– ፊልጵስዩስ 2፡5 አንብቡ። ክርስቲያኖች ምን ዓይነት ዝንባሌ ሊኖራቸው ይገባል?

ፊልጵስዩስ 2፡6–11 የቀድሞ ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ የዘመሩትን መዝሙር ይመስላል? ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ አመራርና ግፊት ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ልጅ ሰው በሆነ ጊዜ ምን እንደ ተደረገ ሊያመለክተን ይህን መዝሙር ጽፎታል። ነገር ግን ሐዋርያው ይህን የጻፈበት ዋነኛው ምክንያት ክርስቲያኖች ልክ ኢየሱስ የነበረውን ዓይነት የትሕትናና ራስን ዝቅ የማድረግ ልብ እንዲኖራቸው ለማበረታታት ነው። ይህ መዝሙር ኢየሱስ አምላክ ሆኖ ሳለ እንዴት በፈቃዱ ሰው ሆኖ ለእኛ ሲል ሊሞት ወደዚህ ዓለም መምጣቱን ይገልጽልናል። ኢየሱስ ለትሕትና እጅግ በጣም ጥሩ ምሳሌያችን ነው። ስለዚህ ክርስቲያኖች የክርስቶስን ትሕትና የሕይወታቸው ምሳሌ አድርገው ሊወስዱት ይገባል።

1. ኢየሱስ ወደ ዓለም ከመምጣቱ በፊት ምን ይመስል ነበር?

19ኛ ጥያቄ፡– ፊልጵስዩስ 2፡6 አንብቡ። ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ምን ይመስል ነበር? ለ) ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ሰው ሆኖ ከመምጣቱ በፊት፥ ስለ መለኮታዊ ተፈጥሮ የነበረው አመለካከት ምን ነበር?

ስለ ኢየሱስ ትሕትና ለመገንዘብ በመጀመሪያ ወደዚህ ምድር ከመምጣቱ በፊት የነበረውን የክብር ስፍራ ልናስተውል ይገባል። ጳውሎስ ኢየሱስ ከመወለዱ በፊትም እንደነበረ የምናውቅ አድርጎ ይገምታል። ታዲያ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ምን ይመስል ነበር። (የቀድሞው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም «በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ» ይላል። በእንግሊዝኛው «ቅርጽ» የሚለውን ቃል በግሪኩ ትርጉም ሲታይ ውጪአዊውን መልክ ብቻ የሚመለከት አይደለም። በአንጻሩ ቃሉ ውጪአዊውን መልክና ውስጣዊውንም ተፈጥሮ ሁለቱንም ይመለከታል። ቃሉ በጥቅም ላይ ሲውል፥ የውጪውን መልክና ከበስተኋላው ያለውንም ባሕርይ ይገልጻል። እንዲህ ማለት ታዲያ ኢየሱስ ውጫዊ የእግዚአብሔር መልክና ውስጣዊ የእግዚአብሔር ባሕርይም አለው ማለት ነው፤ እርሱ እግዚአብሔር ነው፤ እናም የእግዚአብሔር ክብር፥ ሞገስና ኃይል አለው። አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፥ «የመለኮት ባሕርይ አለው» ሲል ይህንኑ ያመለክታል። ለምሳሌ፥ ከልጆቼ ጋር በመንገድ ላይ ሳለሁ ብታገኙኝና ልጆቼን ስንከባከብ ብታዩ፥ «እስጢፋኖስ፥ ዛሬ በእርግጥ አባት ትመስላለህ?» ትሉኝ ይሆናል። እኔ አባት መምሰሌን መግለጻችሁ ብቻ ሳይሆን አባት አለመሆኔንም ነው። በዚህ ፈንታ እስጢፋኖስ፥ «አባት ነህ፥ በእውነት አባት ትመስላለህ?» ልትሉ ትችላላችሁ። ጳውሎስ ኢየሱስ ከተወገዎ በፊትም እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ስለ እርሱ የሆነው ሁሉ የእርሱን አምላክነት እንደሚገልጽ ይናገራል። እርሱ የእግዚአብሔር ኃይል ነበረው። ይህ ኃይል በተናገረው ቃል ፍጥረተ ዓለምን (ዩኒቨርስን) የመሠረተ ነበር። የእግዚአብሔር ጥበብ ነበረው። በኃላፊ ጊዜያት ስለተከናወኑት፥ አሁንና ወደፊትም ስለሚከናወኑት ሁሉ ፍጹም እውቀት አለው። እርሱ የእግዚአብሔር ክብርና ሞገስ ነበረው። ይህም በእልፍ አእላፋት መላእክት ውዳሴ የተከበበ አንጸባራቂ የሰማይ ፀዳል፥

ፍጹም ብርሃንና ክብር ነበር። እርሱ የእግዚአብሔር ፍጹም ባሕርያት የሆኑ ቅድስና፥ መልካምነትና ንጽሕና ነበረው። ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን በሰማይ የነበረው ክብሩ ገልጾታል።

20ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ኢየሱስ እግዚአብሔር ለመሆኑ የሚያመለክቱ ሌሎች ባሕርያቱ የትኞቹ ናቸው? ለ) እናንተ ከእርሱ ጋር ላላችሁ ግንኙነት እነዚህ እያንዳንዳቸው ለምን ጠቃሚዎች ሆኑ?

ኢየሱስ እግዚአብሔር የመሆን ክብሩን በመብትነት መያዝን አልፈለገም። በዚህ ፈንታ በገዛ ፈቃዱ የእግዚአብሔርነትን ክብርና ግርማ አሳልፎ ለመስጠት ወደደ። በግሪኩ ቋንቋ፥ «ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም» የሚለው አገላለጽ፥ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን እንደ ራሱ መልካም ዕድል አድርጎ ሊጠቀምበት አልፈለገም የሚል ነው። ምንም እንኳን ክርስቶስ እግዚአብሔር ቢሆንም፥ የመለኮቱን ኃይልና ክብር ለጥቅሙ ሊያውል አልፈለገም። እግዚአብሔር የመሆኑን ክብር ለራሱ ጥቅም ሊያውለው አልፈቀደም። በዚህ ፈንታ ኢየሱስ መለኮትነቱን እንዴት ተጠቀመበት?

2. ኢየሱስ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ ምን ይመስል ነበር?

21ኛ ጥያቄ፡– ፊልጵስዩስ 2፡7–8 አንብቡ። እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ ስለ አከናወናቸው አምስት ነገሮች ምን ይላሉ?

ኢየሱስ መለኮትነቱን ለግል ጥቅሙ በማዋል ፈንታ፥ አራት ነገሮችን አድርጓል።

1) በቀድሞው የአማርኛ ትርጉም «ራሱን ባዶ አደረገ» የሚለው ሐረግ፥ የጥቅሱ የመጀመሪያው ሐረግ ባይሆንም በግሪኩ የጥቅሱ የመጀመሪያው ሐረግ ነው። በአዲሱ የአማርኛ ትርጉም ላይም የመጀመሪያው ሐረግ ሆኖ ተጽፎአል። «ራሱን ባዶ አደረገ» የሚለው የአማርኛው የቀድሞ ትርጉም፥ የግሪኩን ሐረግ ቃል በቃል ተርጉሞታል። እንዲህ ማለት ምን ማለት ነው? እንዲህ ማለት ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ የመለኮትነቱን ባሕርይ ትቶ ነበር ማለት ነው? ደግሞስ ወደ ምድር ሲመጣ አምላክነቱ አበቃ ማለት ነው? አይደለም። ይህ ሐረግ ኢየሱስ የፈጸመውን ተግባር ጠቅለል አድርጎ ያቀረበበት የጳውሎስ ልማዳዊ አገላለጽ ነው። የሚቀጥሉት ሦስት ሐረጎች ምን ማለቱ እንደሆነ ዘርዘር አድርገው ይገልጻሉ። ሐረጉ ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን ትቷል አይልም። ሐረጉ የሚለው ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑ እንዳለ ሆኖ፥ ሌላ ነገር ሆነ ነው። በነበረው መለኮታዊ ባሕርይ ላይ ሌላ ባሕርይ ጨመረ።

2) ጌታ ኢየሱስ የባሪያን መልክ ወሰደ። በድሮው የአማርኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም «መልክ» የሚለው ቃል በቁጥር ስድስት ከሚገኘው ጋር አንድ ነው። የባሪያን መልክ ወሰደ ማለት ኢየሱስ ሁለቱንም፥ የባሪያን ውስጣዊ ውስጣዊ ባሕሪና ውጪአዊ መልክ ያዘ ማለት ነው። እርሱም ባሪያ ሆነ፥ በእውነትም የባሪያን መልክ ወሰደ። ከተሠገዎ በፊት ኢየሱስ

እግዚአብሔር ነበር። በእግዚአብሔርነትም ተገልጦአል። ከተሠገዎ በኋላ ባሪያ ሆነ፥ እንደ ባሪያም ተገለጠ። የጥንት ዓለም ሰዎች ስለ ባርነት ደህና አድርገው ያውቁ ነበሩ። ባሪያዎችን በየቀኑ ይመለከቱ ነበር። ባሪያዎች ጨርሶ መብት ያልነበራቸው ሰዎች ነበሩ። ታዲያ ኢየሱስ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ በገዛ ፈቃዱ ክብሩንና ታላቅነቱን በመተው በሰዎች ዘንድ ባሪያ መስሎ ተገኘ።

3) ኢየሱስ የሰውን መልክና ምሳሌ ወሰደ። የግሪኩ ቃል «መምሰል» የሚለው በትክክል እንደ አንድ ነገር መሆን ሊሆን ይችላል። እርሱ እንደሚለው ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ከሰው ዘር ጋር ተመሳስሏል። ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ ራሱን ባዶ በማድረግ የተቀሩት የሰው ልጆች እንደሚኖሩት ኖረ። «መልክ» የሚለውን የግሪኩ ቃል «በስሜት ሕዋሳት የሚታወቅ አቀራረብ፥ ቅርጽ ወይም አበጃጀት» ይለዋል። እንዲህ ማለት ኢየሱስ እውነተኛ ሰው አይደለም ማለትም አይደለም። በአንጻሩ ይህ አገላለጽ ሁሉም ሰው እርሱ ሰው መሆኑን ያውቅ ነበር ማለት ነው። እርሱ እንደ ሰው ተገለጠ፤ በአካባቢው የነበሩ ሰዎችም ግንዛቤ እርሱ ሰው እንደሆነ ነበር። ይህ በአጽንኦት የሚያመለክተው ምንም እንኳን ኢየሱስ የአምላክነቱን ባሕርይ እንደ ያዘ ቢሆንም፥ የተገለጠው በሰው መልክ መሆኑን ነው። ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው ከሰዎች ጋር በመኖር ራሱን ባዶ አድርጓል። አብሮአቸው የኖረው ሰዎች የተመለከቱት እንደ እግዚአብሔር አድርገው ሳይሆን ልክ እንደ እነርሱ ሰው አድርገው ነበር። እነዚህ ቃላት በአንድነት የሚገልጹት ኢየሱስ በሰዎች መካከል ሰው ሆኖ በመኖር ራሱን ባዶ እንዳደረገ ነው። እርሱ እውነተኛ ሰው ሆኖ ኖሯል።

22ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ዘዳግም 21፡23 አንብቡ። በአይሁዶች አስተሳሰብ በተለይ የተረገመ ማን ነበር? ለ) ገላትያ 3፡13 አንብቡ። ኢየሱስ ለእኛ ምን ሆነ?

---

4) ኢየሱስ ሞካኔና ሥቃይ በሞላበት ሁኔታ ተሰቅሎ ሞተ። ኢየሱስ በመጨረሻው ላይ ራሱን ባዶ ያደረገውና የነበረውን ክብር አሳልፎ የሰጠው ለሞት ራሱን ባስገዛ ጊዜ ነበር። ኢየሱስ ሰው ለመሆን መፍቀዱ ብቻ ሳይሆን፥ ራሱን ለሞት አሳልፎ በመስጠት ራሱን ትሑት አድርጎአል። የኢየሱስ ሕይወት ሙሉ በሙሉ የአባቱን ፈቃድ በመታዘዝ ላይ የተመሠረተ ነበር (ዮሐንስ 5፡30፤ 6፡38)። ነገር ግን በተለይ ራሱን ለስቅላት አሳልፎ በሰጠ ጊዜ ለአባቱ ፈቃድ ታዛዥነቱን አሳይቷል። ስቅላት በጥንቱ ዓለም ከባድ ሞካኔ ያለበት የውርደት ሞት ነበር። ሥቃይና መከራ ያለበት የአሟሟት ዘዴ ስለነበረ ቅጣቱ በሮም መንግሥት ላይ ላመፁ ከፋ ወንጀለኞች የተመደበ ነበር። በተለይም ስቅላት ለአንድ አይሁድ በጣም የከፋ ድርጊት ነበር። በኦሪት ዘዳግም 21፡23 ላይ፥ «በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነው» ይላል። እንዲህ ማለት በዚህ ሁኔታ የሚሞቱ ሰዎች ከእግዚአብሔር የበረከት ኪዳን ውጭ ስለሚሆኑ፥ የመዳን ተስፋ የላቸውም ማለት ነው። በእውነቱ ኢየሱስ ለእኛ ይገባ የነበረውን የኃጢአት መርገም ተሸከመ (ገላትያ 3፡13)። ራሱንም አሳልፎ እስከ መስቀል

ሞት በመስጠት የነበረውን መብትና ክብር በፈቃዱ ተወ። ሙሉ ለሙሉ ራሱን ባዶ አደረገ።

ፊልጵስዩስ 2፡6–8 ስለ ተሠገዎ ከፍተኛ አጽንኦት የተሰጠበት ክፍል ነው። በእነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ ከተሠገዎ በፊት ለእግዚአብሔርነት በተገባ ክብርና ሞገስ ፍጹም የተላበሰ አምላክ ነበር። ነገር ግን በዚህ ሁሉ ክብሩ መጠቀም ሲችል ትቶታል። ይህን ሁሉ ክብሩን የተወው ወደ ምድር በመምጣት፥ እንደ ማንኛውም ሰው በመኖርና እውነተኛ ባሪያ በመሆን ነበር። እንደ እግዚአብሔርነቱ የነበረውን ትሩፋት (ልዩ መብት) ሁሉ ትቶ ለስቅላት ፈቅዶ ራሱን ሰጠ።

3. ኢየሱስ ዓለምን ትቶ ከሄደ በኋላ ምን ሆነ? ወደፊትስ ምን ይሆናል?

23ኛ ጥያቄ፡– ፊልጵስዩስ 2፡9–11 አንብቡ። ሀ) ኢየሱስ ትሑት በመሆኑ፥ እግዚአብሔር ምን አደረገለት? ለ) ወደፊትስ ፍጥረታት ሁሉ ለኢየሱስ እንዴት ያለ ምላሽ ይሰጣሉ?

በፊልጵስዩስ 2፡6–11 ያለው መዝሙር እግዚአብሔር ለኢየሱስ ትሕትና በሰጠው ምላሽ ይደመደማል። ጌታ ኢየሱስ ክብሩን ሁሉ ትቶ በፈቃዱ ትሑት ስለሆነና ራሱንም ዝቅ ስላደረገ፥ እግዚአብሔር ከፍጥረታት ሁሉ በላይ ከፍ ወደ አለው ክብሩ መለሰው። ነገር ግን እግዚአብሔር ኢየሱስን ወደ ቀድሞ ክብሩ ከመመለስ የላቀ አድርጓል። ወደፊት ፍጥረቱ የሆኑ የሰው ልጆችና መላእክት ሳይቀሩ ኢየሱስ ሥልጣን ሁሉ ያለውና የፍጥረተ ዓለም ሁሉ ገዥ መሆኑን ተረድተው ያከብሩታል፥ ያመልኩታልም። ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሥጋ ከለበሰ በኋላ ቀድሞ በአምላክነቱ በሰማይ ሠራዊት ይደረግለት የነበረውን ክብርና ሞገስ በፈቃዱ ተወ። ይሁን እንጂ ወደፊት ገና እንደ አምላክነቱ ክብር ያልሰጡት ጭምር የሚገባውን አምልኮና ክብር ይሰጡታል።

ነገር ግን አስተውሉ፥ እግዚአብሔር በተለይ ኢየሱስ ለተባለው ስም ሥልጣንና ገዥነትን ሰጥቶታል። «ኢየሱስ» የሚለው ስያሜ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ወደ ዓለም ሲመጣ የተሰጠው ሰብአዊ መጠሪያ ነበር። ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ሰው ሆኖ መጥቶ በሰውነቱ ስለአከናወናቸው ተግባራት፥ እግዚአብሔር ከፍ አድርጎ ከሥልጣን ሁሉ በላይ ሥልጣን ሰጠው። «ኢየሱስ» ማለት አዳኝ ማለት ነው። ኢየሱስ ሰው እስከ መሆን ደረጃ ራሱን ዝቅ በማድረጉና ዓለምን ከኃጢአቱ ለማዳን ሲል የከፋ ሞት ለመሞት በመፍቀዱ፥ ምክንያት እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አደረገው። የኢየሱስ ፍጥረተ ዓለም (የዩኒቨርስ) ገዥ እንዲሆን ከፍ ከፍ የመደረጉ ሁኔታ ሰውም አምላክም በመሆኑ ላይ የተመሠረተ ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ የቀድሞ ክብሩን ትቶ የተናቀና የተዋረደ ሰው ሆኖ በመኖሩ፥ ከተሠገዎ በፊት እንደ አምላክነቱ ክብር ያልሰጡት እንኳ አንድ ቀን ክብርና ምስጋናን ያቀርቡለታል።

ኢየሱስ ሰው ሆኖ ሳለ አምላክነቱን ትቷል ብሎ ፊልጵስዩስ 2 ያስተምራል? እንዲህ ብሎ አያስተምርም። ይህ ክፍል የሚያስተምረው፥ እርሱ የአምላክነት ክብሩና ሞገሱን ተወ ብሎ ነው። ለእግዚአብሔር የተገባውን መብትና ክብር ሁሉ ተወ ነው የሚለው። ያላንዳች ክብርና መብት በመሆን የባሪያን ስፍራ ወሰደ ነው የሚለው። እንደ ሰው ሆኖ ኖረ፥ ሰዎችም ሰው አድርገው ተቀብለው አብረውት ኖሩ ነው የሚለው። ይህ ክፍል ለእግዚአብሔር አብ እስከ መስቀል ሞት ድረስ በትሕትና መታዘዙን ያስተምራል። እግዚአብሔር እግዚአብሔርነቱን አይተውም፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሌሎች ክፍሎ ምንባቦችንም እንደ ተመለከትን ኢየሱስ በምድር ሳለ እንኳን አምላክ ነበር። ፊልጵስዩስ 2፡5-11 ኢየሱስ የአምላክነቱን ክብርና ሞገስ በፈቃዱ ተወ ብሎ ቢያስተምርም፥ አምላክ አልነበረም ብሎ አያስተምርም።

24ኛ ጥያቄ፡- ፊልጵስዩስ 2፡3-4 አንብቡ። ሀ) መብታችሁንና ክብራችሁን አሳልፋችሁ መስጠት የሚከብዳችሁ መቼ ነው? ለ) የሌሎችን ጥቅም ከራሳችሁ ጥቅም ለማስቀደም አስቸጋሪ ሆኖ የምታገኙት መቼ ነው? ሐ) በዚህ ሳምንት የራሳችሁን መብት ትታችሁ የሌሎችን ጥቅም ለማስቀደም የምትችሉበትን ቢያንስ ሦስት መንገዶችን ጻፉ።

ፊልጵስዩስ 2፡5-11 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርይ ብቻ የሚያስተምረን አለመሆኑን መርሳት የለብንም። በመሠረቱ ይህ ክፍል የተጻፈው እንዴት እንደምንኖር ሊያስተምረን ነው። ኢየሱስ ክብሩንና መብቱን እንደ ተወ ሁሉ እኛም የራሳችንን መብትና ጥቅም ከሌሎች ማስቀደም ትተን በዙሪያችን ያሉ የሌሎች ፍላጎት ለማሟላት ተጠርተናል። አንዳንዴ ሌሎችን ለመርዳት ጊዜያችንን አሳልፈን መስጠት ይኖርብን ይሆናል። አንዳንድ ጊዜም ሌሎችን ለመርዳት የእኛን ደረጃ ትተን ዝቅ ማለት ይገባናል። አንዳንዴም ለሌሎች ለየት ያለ አገልግሎት መስጠት ይኖርብን ይሆናል። አንዳንድ ጊዜም የማንስማማበት አሳብ ቢሆንም እንኳ፥ ሌሎች ውሳኔ እንዲሰጡ የምንፈቅድበት ጊዜ አለ። በምናደርገው ሁሉ ኢየሱስን ጥሩ ምሳሌያችን በማድረግ እርሱን እናስቀድም። ራስን አሳልፎ ለሌሎች በመስጠት፥ በትሕትና፥ ከጥቅማችን ሌሎችን በማስቀደም ረገድ ኢየሱስ ቋሚ ምሳሌያችን ነው።

ሦስተኛ ቀን- ስለ ተሠገዎ በዕብራውያን ምዕራፍ 2

ዛሬ በዕብራውያን 2፡5-18 ያለውን ስለ ተሠገዎ የሚያስተምረውን ሦስተኛውን ቁልፍ ክፍለ ምንባብ እንመለከታለን። ይህ ክፍል ኢየሱስ እግዚአብሔር ሆኖ እያለ በምን ምክንያት ፍጹም ሰው ለመሆን እንዳስፈለገው እንድንገነዘብ ይረዳናል።

1. እኛ ፍጥረታትን እንድንገዛ፥ ኢየሱስ ሰው ሆነ

25ኛ ጥያቄ፡- ዕብራውያን 2፡5-8 አንብቡ። ሀ) እግዚአብሔር የሚመጣውን ዓለም ለማን ነው የማይሰጠው? ለ) የሚመጣውን ዓለም ለማን ይሰጣል? ሐ) እኛስ ገና ያላየነው ምንድን ነው?

26ኛ ጥያቄ፡– ዕብራውያን 2፡9 አንብቡ። ምንን እናያለን?

27ኛ ጥያቄ፡– ይህን ክፍል ከአነበባችሁ በኋላ ኢየሱስ ሰው እንዲሆን ያስፈለገበትን ምክንያት ለማለላለል ጊዜ እንዲኖራችሁ አድርጉ። ከዚያም ስታለላስሉ የቆያችሁትን አሳብ በማስታወሻ ደብተር ጻፉ።

ዕብራውያን 2፡5–18 ለሰው ልጆች በተሰጠ አስደናቂ የተስፋ ቃል ይጀምራል። ጸሐፊው በዕብራውያን 2፡1–4 ውስጥ አንባቢዎቹ ለወደፊቱ ስለሚጠብቃቸው የደኅንነት ፍስሐ በማብሰር ይናገራል። ይህ ደኅንነት የሚመጣውን አስደናቂ ዓለም ይጨምራል ይላል። ነገር ግን ይህ መጪው ዓለም ለመላእክት አይደለም። ታዲያ የእግዚአብሔር ዓላማ መጪውን ዓለም ለማን ለመስጠት ነው? ደራሲው ለዚህ መልስ ለመስጠት መዝሙር 8፡4–6 ይጠቅሳል። ምንም እንኳን የሰው ልጆች ከመላእክት ጥቂት ቢያንሱም፥ በመጪው ዓለም ግን የክብርና የምስጋና ዘውድን ይቀዳጃሉ። ሰዎች በመጪው ዓለም የእግዚአብሔርን ፍጥረተ ዓለም ሁሉ (ዩኒቨርስን) ይገዛሉ። እኛ አማኞች ከሚኖሩን ታላቅ የደኅንነት በረከቶች አንድ ቀን እግዚአብሔር በፈጠረው ሁሉ ላይ ገዥዎች የመሆናችን እውነታ ነው።

ነገር ግን ይህን አስደናቂ በረከት ገና አልተቀበልንም። አሁን ባለንበት ሕይወት ሰብአዊ ፍጡር በፍጥረታት ላይ ያለውን የአገዛዝ ሥልጣን ገና አላየነውም። እነዚህን በረከቶች አንድ ቀን እንደምንቀበል እንዴት ልናውቅ እንችላለን? ይህን የወደፊት በረከት የሚያረጋግጡልን አንዳንድ ነገሮችን እናያለን። በአንድ ወቅት ሰው በመሆን ዝቅ ብሎ የውርደትንና የትሕትናን ሕይወት የኖረው ኢየሱስ ከፍ ከፍ ሊል አይተናል። ኢየሱስ ልክ እንደ እኛው ሰው ሆነ። ለእኛ ሊሞት ብሎ ሥጋን ለበሰ። ይህ ከእኛ እንደ አንዱ ሆኖ የኖረው ኢየሱስ አሁን በሰማይ ከፍ ከፍ ብሎ ይገኛል። መላ ፍጥረተ ዓለምን (ዩኒቨርስን) የመግዛት ክብር፥ ሞገስና ገናናነት ያለው ኢየሱስ ብቻ ነው። ነገር ግን ኢየሱስም ሰው ስለነበረና በዚህ ባሕርይ ስለምንዛመደው እኛም የዚህ አገዛዝ ተካፋዮች የመሆን ባለ መብት ነን።

አንድ ሰው የአገሩ ፕሬዚዳንት ሆኖ በሚመረጥበት ጊዜ፥ እርሱ ብቻውን የሥልጣንና የማንኛውም ክብር ባለቤት ሆኖ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ አይኖርም። ባለቤቱና ልጆቹ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ አብረውት በመሆን ክብር የተመላበትን ሕይወት ይጋራሉ። በዚሁ መሠረት እኛም ከኢየሱስ ጋር ባለን ተዛምዶ ከእርሱ ጋር ሆነን በአዲሱ ዓለም ክብርና ደስታ የተሞላበትን ሕይወት እንኖራለን። ጌታ ኢየሱስ ሰው ሆኖ ተሠቃይቶ ከሞተልን በኋላ በሰማይ ከፍ ብሎ ስላለ፥ የደኅንነት በረከቶቻችንን እንደምናገኝ እርግጠኞች ነን። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰውም–አምላክም የሆነውን ኢየሱስን ከሁሉም በላይ ከፍ ከፍ ስላደረገው፥ ተስፋውን ጠብቆ ልጆቹ ፍጥረታትን እንዲገዙ ከፍ ከፍ እንደሚያደርጋቸው እናውቃለን።

ከኢየሱስ ጋር እንዴት ልንዛመድ ቻልን? ምክንያቱም እርሱ ፍጹም ሰው ሆኖ እስከ ሞት ድረስ ሥቃይን ስለተቀበለ ዝምድና ልንመሠርት ችለናል። ኢየሱስ የሰው ልጆች እውነተኛ አለኝታ ሆኖ ክብር የተሞላበትን ደኅንነት

ለሰዎች ለመስጠት የእርሱ ሰብአዊነትና ሰብአዊ ሥቃይ አስፈላጊዎች ነበሩ። ደግሞም የኢየሱስ ሰብአዊነት ለመጪው ደኅንነታችን እውነተኛ ዋስትናችን ነው። የወደፊቱን የክብር ወራሽነት እንድናገኝ ኢየሱስ ፍጹም ሰው መሆን ነበረበት።

2. ኢየሱስ ከእኛ ጋር አንድ ቤተሰብ ሆኖ ደኅንነትን ለመስጠት ሰው ሆኖአል።

28ኛ ጥያቄ፡– ዕብራውያን 2፡10 አንብቡ። እግዚአብሔር (ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ለማምጣት ብሎ) በደኅንነት ራስ (ኢየሱስ) ላይ ምን አደረገ?

29ኛ ጥያቄ፡– ዕብራውያን 2፡11–13 አንብቡ። ሀ) ሌሎችን ሊቀድስ የሚችል እርሱ ማን ነው? ለ) የተቀደሱት እነማን ናቸው? ሐ) የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ሁሉ ከአንድ ናቸውና ይላል። «ከአንድ ናቸውና» ሲል ምን ማለቱ ነው?

30ኛ ጥያቄ፡– በቁጥር 11–13 ላይ ኢየሱስ የሰው ልጆችን ምን ብሎ ይጠራቸዋል? ቢያንስ ሁለት መልሶችን ፈልግ።

እነዚህ ጥቅሶች ስለ ኢየሱስ ሰብአዊነት ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ይሰጡናል። በመጀመሪያ ደረጃ ኢየሱስን የደኅንነታችን «ራስ» ሲሉ ይገልጹታል። «ራስ» ተብሎ ከግሪክኛው የተተረጎመው ቃል፥ ከሁሉ ቀድሞ ወደ አዲስ አገር ደርሶ ሌሎች እንዲከተሉት መንገድ የሚከፍት ማለት ነው። ከኃጢአት በስተቀር ኢየሱስ በሁሉም ረገድ እንደ እኛው ሆኖ ብዙ ልጆች በክብር ደኅንነቱ ደስ እንዲላቸው መንገዱን ከፈተላቸው። ነገር ግን ይህን ለማድረግ የሞትን ሥቃይ ተቀብሎ ፍጹም መሆን ነበረበት። ስለዚህ ኢየሱስ ተሠቃይቶ ባይሞት ኖሮ ፍጹም ሰው ሊሆን ባልቻለ ነበር። እንደዚሁም ሥቃይን ተቀብሎ ባይሞት ኖሮ ፍጹም መድኅን ባልሆነም ነበር። ኢየሱስ በሥቃዩና በሞቱ ጊዜ እንኳን ፍጹም ሰው ነበር። ምክንያቱም እርሱ በሥቃዩና በሞቱ ፍጹም ሰው ስለነበረ፥ የእግዚአብሔርን ልጆች ክብር ወዳለው ደኅንነት ለማምጣት የሚችል መድኅን ነበር።

ለመሆኑ ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ሰው ነው? ጸሐፊው ኢየሱስ ሰብአዊ ከሆነ ቤተሰብ የተገኘ ፍጹም ሰው መሆኑን ለማስረዳት ከብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ያቀርባል። የሚቀድሰው ኢየሱስ ራሱ ነው። የሚቀደሱት ደግሞ ሁሉም አማኞች ናቸው። «ከአንድ ናቸውና» ወይም «ከአንድ አባት ናቸውና» ይህን ሲል ከአንድ ቤተሰብ ናቸው ማለቱ ነው። ኢየሱስና የሰው ልጆች አንድ ቤተሰብ ናቸው። ይህን ለማረጋገጥ መዚሑ የተቀሩትን የሰው ልጆች «ወንድሞቼ» ሲል የተናገረውን መዝሙር 22፡22 በመጀመሪያ ይጠቅሳል። ሰዎች የኢየሱስ ወንድሞችና እኅቶች ከሆኑ፥ እርሱ ራሱ ሰው ነው ማለት ነው። በምድር መዚሑ፥ ሌሎች እግዚአብሔርን ሲቃወሙ እግዚአብሔርን ከሚያምኑ የእግዚአብሔር ሰዎች ጋር ራሱን ያመሳሰለበትን በሁለተኛነት ኢሳይያስ 8፡17 ይጠቅሳል። ልክ ሌሎች ሰዎች በእግዚአብሔር እንደሚተማመኑ ሁሉ፥ እርሱም በእግዚአብሔር ይተማመን ነበር። በምድር በነበረበት ጊዜ ፍላጎቱን እግዚአብሔር እንዲያሟላለት በፍጹም ሰብአዊነቱ በእግዚአብሔር ይተማመን ነበር። በመጨረሻውም ላይ፥ መዚሑ ሕዝቡን

«ልጆቼ» ብሎ የተናገረበትን ኢሳይያስ 8፡18 ይጠቅሳል። ምክንያቱም መሢሑ ሰዎች የሆኑ ተከታዮቹን ወንድሞቼና ልጆቼ ብሎ ስለሚጠራቸው እርሱ ሰው መሆኑን በዚህም እንረዳለን። በእርግጥም ኢየሱስ ብዙ ልጆችን ክብርን ወደ ተጎናጸፈ ደኅንነት ለማምጣት ፍጹም ሰው ሆኖአል።

3. ኢየሱስ በሞቱ ሰይጣንን ለማሸነፍ ሰው ሆኖአል።

31ኛ ጥያቄ፡– ዕብራውያን 2፡14–15 አንብቡ። ሀ) ቀደም ሲል በሞት ላይ ሥልጣን የነበረው ማን ነው? ለ) ይህ ምን ማለት ነው? ሐ) ኢየሱስ ስለዚህ ምን አደረገ? መ) ኢየሱስ በሞት ፍርሃት ባርነት ውስጥ ላሉት ምን አደረገ? ሠ) ኢየሱስ ሥጋና ደምን ለምን ተዋሃደ?

32ኛ ጥያቄ፡– ዕብራውያን 2፡18 ኢየሱስ የሚረዳው ማንን ነው?

ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ሰው የሆነበትን ምክንያት ደራሲው በሰፊው መግለጹን አሁንም ይቀጥልበታል። ኢየሱስ፥ ሰይጣን በሰዎች ላይ ያለውን የሞት ሥልጣን ለመሻርና እርሱን ለማሸነፍ ኢየሱስ ፍጹም ሰው መሆን ነበረበት። ደራሲው ሰይጣን የሞት ሥልጣን በሰዎች ላይ አለው ሲል፥ ምን ማለቱ ነው? ይህን ሲል፥ ሰይጣን ሰዎችን የመግደል ሥልጣን አለው፥ ወይም ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ ለሰይጣን የሞት ካሳ ከፈለው ማለት አይደለም። ሰይጣን በሞት ላይ ያለው ሥልጣን፥ ሰዎች ኃጢአት እንዲሠሩ መፈተን ነው። ሰዎች ኃጢአትን በሚያደርጉበት ጊዜ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለሚጥሱ በሥጋም በመንፈስም እንዲሞቱ ይፈረድባቸዋል። ስለዚህ ፍጥረተ ዓለማትን (ዩኒቨርስን) ለመግዛት የተመረጥን የሰው ልጆች ከኃጢአታችን የተነሣ የሞትና የሰይጣን ባሪያዎች እንሆናለን።

33ኛ ጥያቄ፡– ሞትን በመፍራታቸው ስለምታውቋቸው ሰዎች እስቲ አስቡ። በማስታወሻ ደበተራችሁ ውስጥ ከሁለት እስከ ሦስት ሰዎች ጻፉ። እነዚህ ሰዎች በምን ምክንያት ሞትን ይፈራሉ?

ሰዎች በሞት ፍርሃት ምክንያት በባርነት ውስጥ መኖራቸውን በቀላሉ ልንገነዘብ እንችላለን። እስቲ በቅርቡ ስለተገኛችሁበት በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች ልቅሶ አስቡ። የሞቱ ወላጆቻቸውና ወዳጆቻቸው ከሞት በኋላ ምን እንደሚሆኑ እርግጠኞች ባለመሆናቸው ተስፋ በቆረጠ ስሜት ያለቅሳሉ። ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች መሆናቸውን በልባቸው ያውቃሉ። እንደዚሁም በኃጢአታቸው ምክንያት ቅጣት እንደሚገባቸውም ያውቃሉ። ስለዚህ ሰዎች ራሳቸውም ሆኑ ወዳጆቻቸው በሚሞቱበት ጊዜ ቅጣታቸውን የሚቀበሉ መሆናቸውን ስለሚረዱ ሞትን በጣም ይፈሩታል። ሰይጣን ኃጢአትን እንድንሠራ ስለሚያደርገንና ኃጢአታችንም ለቅጣት አሳልፎ ስለሚሰጠን፥ ሰዎች የሞት ፍርሃት ባሪያዎች እንሆ ናለን።

ነገር ግን ኢየሱስ በሞተ ጊዜ ሰይጣን በሞት ላይ የነበረውን ኃይል ደምስሶ ሰዎችን ከሞት ፍርሃት ውስጥ ነፃ አውጥቶአቸዋል።

34ኛ ጥያቄ፡– ቆላስይስ 2፡13–15 አንብቡ። ሀ) ኢየሱስ በሞተ ጊዜ ይኮንኑን ስለነበሩት ሕጎች ወይም የዕዳ ጽሑፎች ምን አደረገ? ለ) ይህ አለቅነትንና ሥልጣናትን ምን አደረጋቸው?

ቆላስይስ 2፡13–15 ኢየሱስ በሞተ ጊዜ የተጻፈውን ጽሕፈት ማለትም የእግዚአብሔርን ሕግ በመስቀል ላይ በሚስማር ጠርቆታል ይላል። በጥንቱ ዓለም፥ አንድ ሰው በሚሰቀልበት ጊዜ፥ በግለሰቡ የስቅላት ቅጣት የደረሰበትን ምክንያት የሚያስረዳ ጽሑፍ እዚያው አጠገቡ በመስቀሉ ላይ በሚስማር ይመታ ነበር። ይህ ጥቅስ የሚነግረን፥ ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ የእርሱ ቅጣት እኛ የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ አለመቻላችን መሆኑን ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሕግ በመጣሳችን ልንከፍል የነበረውን የሞት ዕዳ ኢየሱስ ስለ ከፈለልን፥ እግዚአብሔር ዕዳችንን ሰርዞልናል። እነሆ፣ ዕዳችን ስለ ተከፈለልን፥ ሰይጣንና ጭፍሮቹ በእኛ ላይ የነበራቸው ኃይል ተወግዷል። ስለሆነም ኢየሱስ በሞቱ በእኛ ላይ ይሠለጥን የነበረውን የሰይጣንን ኃይል ደምስሶታል።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ፥ ለእግዚአብሔር መከፈል የነበረብንን የኃጢአት ቅጣት ዕዳ እርሱ ከፈለልን። የክርስቶስን ሞት ለኃጢአታቸው የተከፈለ ቤዛ አድርገው የሚቀበሉ ሁሉ፥ ለኃጢአታቸው ዋጋ ለመከፈሉ ዋስትና አላቸው። ስለዚህ ምንም ጊዜ ሞትን የሚፈሩበት ምክንያት የላቸውም። ከእንግዲህ ወዲያ የኃጢአት ቅጣት አያስፈራቸውም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ በሥቃዩ ቅጣታቸውን ተቀብሎላቸዋልና። ሰይጣን ለምን ጊዜውም ቢሆን የፍርሃት ባሪያ ሊያደርጋቸው አይችልም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ሰው ሆኖ መጥቶ ለኃጢአታቸው ሞቶላቸዋልና። ኢየሱስ የሰው ልጆች ሊሞቱ የሚገባቸውን ሞት ሊሞትላቸው፥ ሥጋና ደምን ወስዶ ሙሉ በሙሉ ሰው ሆነ። ክርስቶስ ይህን ሞት በሞተ ጊዜ ሰይጣንን ድል አድርጎ ከሞት ፍርሃት ነፃ አወጣን። መላእክት ይህን የመሰለ አርነት አይሹም፥ ምክንያቱም ንጹሐን የሆኑት መላእክት ኃጢአት አላደረጉም። ሰዎች ግን ኃጢአትን ፈጽመዋል። ስለዚህ ኢየሱስ በአብርሃም እምነት ውስጥ ያሉትን የሰው ልጆች ከሞት ፍርሃት አርነት ለማውጣት ራሱ ሰው ሆነ።

35ኛ ጥያቄ፡– በ33ኛው ጥያቄ ላይ ስሞቻቸውን ስለ ጻፋችኋቸው ሰዎች አስቡ። ስለ ኢየሱስ ሰብአዊነት ከሚናገረው ከዚህ ምንባብ ውስጥ ለእነርሱ ማበረታቻ የሚሆን የትኛውን አብራችኋቸው ትካፈላላችሁ?

የተሠገዎ ምሥጢር ኢየሱስ ከኃጢአት በስተቀር ሰብአዊነትን ተላብሶ፥ እኛን ከሞት ፍርሃት ነፃ ማውጣቱ ነው። የሞት ፍርሃት አለባችሁ? በክርስቶስ ፍጹም ሰብአዊነት ደስ ይበላችሁ። ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ሰው መሆኑን የምታምኑ ከሆናችሁ፥ ሞትን ከቶ ልትፈሩ አይገባችሁም። ሞትን የሚፈሩ የምታውቋቸው ሰዎች አሉ? ካሉ ስለ ክርስቶስ ሙሉ ሰብአዊነት ያለውን እውነት አብራችኋቸው ተካፈሉ። እርሱ ሙሉ በሙሉ ሰው ስለሆነ፥ ሞትን ጨርሶ ሊፈሩ አይገባቸውም።

4. ኢየሱስ ፍጹም ካህናችን ሊሆን ሰው ሆነ።

36ኛ ጥያቄ፡– ዕብራውያን 2፡17–18 አንብቡ። ኢየሱስ ሰብአዊ ካህን እንዲሆን ለምን አስፈለገ? ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች በመነሣት ሁለት ምክንያቶችን ጻፉ።

ጸሐፊው ኢየሱስ በምን ምክንያት ሰው እንዲሆን እንዳስፈለገ ገለጻውን ለማጠቃለል እንደ ሰብአዊ ካህን የፈጸማቸውን ሁለት ተግባራት ያብራራል። ኢየሱስ በማንኛውም መንገድ እንደ ወንድሞቹ መሆን ነበረበት ይለናል። እንደዚህ ማለት ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ሰው መሆን ነበረበት ማለት ነው። እንደ ሰብአዊ ወንድሞቹና እኅቶቹ እርሱም ሰው መሆኑ ለምን አስፈለገ? ያስፈለገበት ምክንያት ፍጹም ካህናቸው እንዲሆን ነው። ስለዚህ ኢየሱስ በፍጹም ሰብአዊነቱ የሚያከናውናቸው ሁለት ተግባራት አሉ። በመጀመሪያ፥ ኢየሱስ የሰው ልጆችን ኃጢአት ያስተሰርይ ዘንድ ፍጹም ሰብአዊ ካህን መሆን ነበረበት። ደራሲው ይህንን ዘርዘር አድርጎ በዕብራውያን 7–10 ይገልጽልናል። በሚቀጥለው ትምህርት ውስጥ ስለ ኃጢአት ኢየሱስ የከፈለውን መሥዋዕትነት እንሥተን እንወያያለን። እዚህ ላይ ደራሲው የሚነግረን፥ እርሱ ፍጹም ሰብአዊ ካህን በመሆኑ ፍጹም የሆነ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ሊያቀርብ እንደ ቻለ ነው።

ኢየሱስ ፍጹም ሰብአዊ ካህን እንዲሆን ያስፈለገበት ሁለተኛው ምክንያት እርሱ በሕይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች ይገነዘብልን ዘንድና ፈተናዎቹንም እንድንቋቋማቸው ያበረታታን ዘንድ ነው። ደራሲው እንደ ገና በሚቀጥለው ትምህርት ይህን በዕብራውያን 4፡14–5፡10 በበለጠ ዘርዘር አድርጎ ይገልጸዋል። እኛም በሚቀጥለው ትምህርት ውስጥ ስለ ኢየሱስ ካህንነት ተመልሰን እንወያያለን። ነገር ግን ከተሠገዎ ምሥጢር የተነሣ፥ ኢየሱስ ፍጹም ሰብአዊነትን ተላብሶ ፍጹም ርኅሩኅ ካህን በመሆን ሊያገለግል ችሏል።

ዕብራውያን 2፡5–18 እንደሚያብራራው፥ በተሠገዎ ምሥጢር ውስጥ ኢየሱስ ፍጹም ሰው ሆነ። እንዲያውም ሰብአዊነቱ በሥቃይ ሞቱ የተሟላ ሆኖአል። ለወደፊቱ ከእርሱ ጋር ሆነን በእግዚአብሔር መንግሥት መግዛት የምንችልበትን በረከት ሊያረጋግጥልን የቻለው ፍጹም ሰው በመሆኑ ብቻ ነው። እርሱ ሙሉ በሙሉ ሰው በመሆኑ ብቻ ነው እኛም የእርሱ ቤተሰብ አካል ልንሆን የቻልነው። ሙሉ በሙሉ ሰው ከመሆኑ የተነሣ ብቻ ሰይጣንን ድል አድርጎ ከጣለብን የሞት ፍርሃት ነፃ አውጥቶናል። ለእኛ ፍጹም የሆነ ካህን ሊሆን የቻለውም ሙሉ በሙሉ ሰው ስለሆነ ብቻ ነው። ዕብራውያን 2፡5–18 እንደሚያስተምረን የኢየሱስ ፍጹም ሰብአዊነት የእኛን ፍጹም ደኅንነት ያረጋግጥልናል።

37ኛ ጥያቄ፡– በዚህ ትምህርት ውስጥ ለእግዚአብሔር ምስጋና እንድታቀርቡ የሚያደርጋችሁ ምን ቁም ነገር ተማራችሁ? በደብተራችሁ ውስጥ ጻፉትና ጊዜ ወስዳችሁ ጸሎት አድርጉ። ኢየሱስንም ሰው በመሆኑ አመስግኑት።

38ኛ ጥያቄ፡– ሞትን ከሚፈራ አንድ ሰው ጋር ኢየሱስ እንዴት ሰው እንደ ሆነ፥ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ፥ ከዚህ ፍርሃትም ነፃ ሊያወጣው እንደሚችል አብራችሁ ተወያዩ። በዚህ ረገድ ያላችሁን ተሞክሮ ፍሬ አሳቡን በማስታወሻ ደብተራችሁ ውስጥ ጻፉ።

አራተኛ ቀን– በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን የተሠገዎ ታሪክ

ዛሬ ስለ ኢየሱስ ተሠገዎ ማጥናታችንን እንቀጥላለን፥ ነገር ግን ሆኖም ጥናታችን ከሌላ አቅጣጫ ይሆናል። የዛሬው ጥናታችንም የሚጀምረው የተሠገዎ አስተምህሮ በጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት እንደ ተስፋፋ ነው። በሚመጣው ሳምንትም የተሠገዎ አስተምህሮ በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት እንደ ተስፋፋ የምናጠና ሲሆን፥ ይህ አስተምህሮ በኢትዮጵያም ውስጥ እንዴት እንደ ተስፋፋ እንማራለን።

የእምነት አስተምህሮን ታሪክ መማራችን ለምን ይጠቅመናል? ከክርስቶስ ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ሺህ ዓመታት ብዙ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ወንዶችና ሴቶች መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት በታማኝነት ሊገነዘቡትና ሊታዘዙትም ሞክረዋል። በእነዚህ ጥንታውያን ክርስቲያኖች ትምህርት ሁለት ከመሥመር የወጡ ወይም ጽንፍ ዘለል አመለካከቶች እንዳንይዝ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። በአንድ በኩል ትምህርታቸው ዋጋ የለውም ብለን ጨርሰን ልናጣጥለው አይገባም። ተሞክሮአቸውንና የአሳቦቻቸውን መደምደሚያ በማጥናት፥ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት መገንዘብ እንዳለብን ከትምህርቶቻቸው ላይ ብዙ ልንማር እንችላለን። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አስቸጋሪ ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመፍትሔነት በአዘጋጁት የእምነት አቋም ልዩ ትኩረት መስጠት አለብን። ነገር ግን በሌላ በኩል የእነርሱን የትምህርት ድምዳሜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እኩል አድርገን ማስቀመጥ የለብንም። የእነዚህ የጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን አባቶች የእምነት አንቀጾችና ትምህርቶቻቸው በጊዜው ለአጋጠሟቸው ጉዳዮችና ችግሮች በመፍትሔነት የተጠቀሙባቸው ናቸው። እነዚህ ንጥረ ድምዳሜዎች ጠቃሚዎች ናቸው፥ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር በእኩልነት ደረጃ ሊታዩ አይገባም። ስለሆነም ድምዳሜዎቻቸውን በማጥናት ልንማርባቸው እንችላለን። ይሁን እንጂ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በመመለስ ላለንበት ባሕል፥ ለቋንቋችንና ለትውልዳችን ምን ዓይነት ትምህርት እንደሚሰጡ ማብራራት አለብን። ዛሬ ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመሥርተው የእምነት አንቀጾቻቸውንና የአስተምህሮ መሠረታቸውን ሊጽፉ ያስፈልጋል። እነዚህ የእምነት አንቀጾች ከጥንቶቹ ጋር የማይቃረኑ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን ያንኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት በአዲስና ወቅታዊ አገላለጽ ሊያሰፍሩ ይችላሉ።

ለሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት የእምነት አስተምህሮን ታሪክ የምናጠና ስለሆነ የተለመደውን መንገድ በመከተል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎችን በመመለስ በመልሶቻቸው ላይ አንወያይም። በዚህ ፈንታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሆነው ነገር በማጥናት በአጠናነው ትምህርት ላይ ለተመሠረቱት ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን። የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ታሪክን በተመለከተ በምንጭነት ብዙ መጻሕፍትን እጠቀማለሁ። ነገር ግን በተለይ «The Word Became Flesh» (ቃል ሥጋ ሆነ) ከሚለው የሚላርድ ኤሪክሰን መጽሐፍ ውስጥ ለዚህ ትምህርት የሚጠቅመውን ልወስድ እወዳለሁ።

ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን በዓመታት መካከል ስለ ኢየሱስ ማንነት ትክክለኛ ጥርት ያለ ግንዛቤን አዳብራ ቆይታለች። ታዲያ ይህ ግንዛቤ በአመዛኙ ሊዳብር የበቃው በክርስቶስ ማንነት ላይ የተነሡትን የሐሰት ትምህርቶች ለመቋቋም በተወሰደ ምላሽ ነው። የሆኑ ቡድኖች ብድግ ብለው ስለ ክርስቶስ የተሰማቸውን ማስተማር ይጀምሩ ነበር። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደግሞ እነዚህን ትምህርቶች አጥንተው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያስተያዩ ነበር። ከዚያም መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚያስተምረውን በመግለጽ መልስ ይሰጡ ነበር። ከዚህ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል አዲስ ትምህርት ስሕተቱና ትክክለኝነቱ ምኑ ላይ እንደሆነ ለይተው በደንብ ያብራሩ ነበር።

ኢቢዮናውያን

የጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን መልስ መስጠት የነበረባት በጊዜው ከተነሡት ቡድኖች መካከል አንደኛ ለሆነው ለኢቢዮናውያን ቡድን ነበር። ኢቢዮናውያን ከብዙዎቹ የቀድሞ የአይሁድ ክርስቲያኖች ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ ናቸው። እነዚህ ሰዎች አይሁዳውያን ሲሆኑ፥ ኢየሱስንም እንደ አይሁድ መሢሕ አድርገው ይቀበሉት ነበር። እነርሱም አንድ አምላክ እንደነበርና እርሱም አይሁዶች እንደ መመሪያ አድርገው ለምን ጊዜውም የሚታዘዙበትን ሕግ እንደ ሰጣቸው አጥብቀው ያምኑ ነበር። ስለዚህ ኢቢዮናውያን ሰዎች ሊድኑ ከፈለጉ ለሕጉ ተገዢ መሆን እንዳለባቸው ያምኑ ነበር። አቢዮናውያን ኢየሱስን የአይሁዶች መሢሕ አድርገው ይቀበሉት እንጂ እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን አያምኑም ነበር። አንድ አምላክ ብቻ አለ፥ ታዲያ በምን አኳኋን ሰው የሆነው ኢየሱስ እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል የሚል ክርክር ነበራቸው። በምትኩ ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ወርዶ በተለየ ሁኔታ እንደ ማደጎ ልጁ አድርጎ ተቀበለው ብለው ያምናሉ። እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ አድሮ የመሢህን ተልዕኮ ለማሟላት ሠራ ይላሉ። ያ የተባለው ሥራ ምንድን ነበር? ኢቢዮናውያን እንደሚሉት፥ የኢየሱስ ዋነኛ ሥራ፥ ሰዎች ሕገ እግዚአብሔርን እንዲታዘዙ ማስተማር ነው ብለው ያምኑ ነበር። እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ስምምነት ያለው ሕይወት እንድንመራ ልንከተለው የሚገባ ምሳሌያችን ሆኖ ኖረ ይላሉ። የጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ በኢቢዮናውያን አስተምህሮ ላይ ሁለት ችግሮች ታይተዋቸው ነበር። <u>በመጀመሪያ</u>፥ ኢየሱስ ራሱ አምላክ መሆኑን መካዳቸው ሲሆን፤ <u>ሁለተኛ</u>፥ ሰዎች ለመዳን የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ ይገባቸዋል የሚሉት ናቸው። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ኢቢዮናውያንን በአስተማሩት በዚህ ትምህርት አውግዛቸዋለች። ነገር ግን ይህ የተሳሳተ ትምህርታቸው ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ማንነት ያልተበረዘና ጥርት ያለ ትምህርታዊ ግንዛቤን እንድታዳብር ረድቷታል። አባቶች መጽሐፍ ቅዱስን በመመርመር፥ ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት እንኳን አምላክ እንደነበረ አረጋገጡ፥ እንደዚሁም እርሱ ለእኛ ምሳሌ ሲሆን፥ ዋና ተግባሩ ግን ስለ ኃጢአታችን መሞት መሆኑን በጥልቅ ተመለከቱ።

39ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ኢቢዮናውያን ኢየሱስ ማን መሆኑን አመኑ? ለ) ኢቢዮናውያን እግዚአብሔር በኢየሱስ ውስጥ አደረ ብለው የሚያምኑት መቼ ነው? ሐ) ኢቢዮናውያን የኢየሱስ ዋነኛ ሥራ ምን ነበር ብለው አመኑ? መ) ኢቢዮናውያን ያስተማሩትን ትምህርት ብንከተል ኖሮ ዛሬ እምነታችን ምንኛ ይለወጥ ነበር?

40ኛ ጥያቄ፡- ኢየሱስ እግዚአብሔር የተጠቀመበት መልካም ሰው ነበር እንጂ አምላክ አልነበረም ብለው የሚያምኑ የምታውቋቸው ሰዎች ይኖሩ ይሆን? ከእነርሱ ያገኛችሁትን የምታውቁትን ጻፉ። ለ) ቀደም ሲል ከአጠናችኋቸውና ስለ ክርስቶስ ማንነት ከሚናገሩ ጥቅሶች የትኞቹን አብራችኋቸው ትካፈላላችሁ?

41ኛ ጥያቄ፡- የኢየሱስ ዋና ተግባር ለእግዚአብሔር ታማኝ የመሆን ምሳሌነት ነው ብለው የሚያምኑ የምታውቋቸው ሰዎች አሉ? ስለ እነዚህ ሰዎች ያላችሁን ተሞክሮ ጻፉት።

ከዚህ ቀደም እንደተመለከትነው ሁሉ፥ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 እና ፊልጵስዩስ ምዕራፍ 2 ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ሰው ሆኖ ከመምጣቱ በፊትም እንኳ ፍጹም አምላክ እንደነበረ በግልጽ ያስረዳሉ። አንዳንድ የሐሰት ትምህርቶች እንዲሁም ክርስቲያኖች ነን ብለው ራሳቸውን የሚጠሩ ሰዎች ሳይቀሩ ኢየሱስ እግዚአብሔር በውስጡ ያደረበትና የተገለገለበት ቅን ሰው ነበር ብለው ዛሬም ያስተምራሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ጥርት ባለ ሁኔታ ኢየሱስ ሰው ሆኖ ከመወለዱ በፊትም ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ይመሰክራል። ሌላው አንዳንድ ክርስቲያኖች ደግሞ ኢየሱስ ለእኛ ምሳሌ ሊሆን የኖረውን ሕይወት ትኩረት በማድረግ የመጀመሪያውን ስፍራ ይሰጡታል። ምንም እንኳን ኢየሱስ ምሳሌያችን ቢሆንም፥ ቆየት ብለን በሚቀጥለው ትምህርታችን ውስጥ እንደምናየው እርሱ ለእኛ የኃጢአትን ይቅርታ ለመስጠት ሲል የሞተው ሞት ከሁሉም የላቀ ተግባር ነው።

ኖስቲካዊነት

ኢቢዮናውያን ተነሥተው ኢየሱስ ሰው ብቻ ነበር ብለው ባስተማሩበት በዚያው ጊዜ ከኢቢዮናውያን ለየት ያለ ትምህርት ይዘው የተነሡት ደግሞ ኖስቲካውያን ነበሩ። እነዚህ ኖስቲካውያን በትምህርታቸው ውስጥ በተፈጥሮ የተገኘውና ማንኛውም አካላዊ ነገር ሁሉ ክፉ ነው ብለው። ያምኑ ነበር። ማንኛውም ተፈጥሮአዊ ነገር ወይም ቁስ አካል ክፉ በመሆኑ ምክንያት ኢየሱስ ሰው መሆኑ እውነት ሊሆን አይችልም ብለው ያስተምሩ ነበር። መንፈስ ብቻ መልካም ነው ብለው ያምኑ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ እውነተኛ የሰው አካል ያለው እውነተኛ ሰው ሳይሆን እውነተኛ የሰው አካል ያለው መስሎ የተገለጠ ነው ይሉ ነበር። በእርግጥ ኢየሱስን ድንግል ማርያም አላረገዘችውም፥ ነገር ግን በውስጡ ብቻ አለፈ ብለው ያምኑ ነበር። እንደዚሁም ኖስቲካውያን ወደ ደኅንነት ሊደረስ የሚቻለው በእውቀት ነው ብለው የሚያምኑ ነበሩ። ሰው የበለጠ መንፈሳዊ ምሥጢራትን ባወቀ መጠን ክፉ ከሆነው ከቁስ አካላዊ ዓለም ይርቅና መልካም ወደሆነው መንፈሳዊ ዓለም ይቀርባል ባይ ናቸው። የጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእነዚህ በኖስቲካውያን ትምህርት ውስጥ ብዙ ጉድለቶችን ሊመለከቱ ችለዋል። <u>በመጀመሪያ</u>፥ ኢየሱስ በድንግል ማርያም ተፀንሶ የተወለደ፥ እውነተኛ ሰው

መሆኑን ይክዳሉ። ሁለተኛ፥ ቁስ አካላዊው ዓለም በራሱና ከራሱ ክፉ ነው ይላሉ። በመጨረሻም፥ ደኅንነት በመሠረቱ የሚገኘው ጥልቅ በሆነ መንፈሳዊ እውቀት ነው ይሉ ነበር። ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ኖስቲካውያንን በዚህ ሐሳዊ ትምህርታቸው የተነሣ አውግዛቸዋለች፤ ነገር ግን ትምህርታቸው ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ መርምራ ወደ ትክክለኛው ግንዛቤ እንድትደርስ በማድረግ ረገድ ረድቷታል። በመጀመሪያ፥ ኢየሱስ በሰው ተመስሎ ብቻ አልታየም፤ ኃጢአት አላደረገም እንጂ በማንኛውም ሁኔታ እርግጠኛ ሰው ነበር። ሁለተኛ፥ ቁስ አካላዊው ዓለም በራሱ ክፉ አይደለም። እግዚአብሔር መልካም አድርጎ ፈጥሮታል። ቁስ አካላዊውም ሆነ መንፈሳዊው ዓለም ከኃጢአት የተነሣ ክፉዎች ናቸው። ሰዎች ኃጢአትን ወደ ቁስ አካላዊው ዓለም ሲያመጡ ብቻ ክፉ ይሆናል። በመጨረሻም፥ ደኅንነት መንፈሳዊ ምሥጢርን ከመገንዘብ በላይ ነው። ስለሆነም ደኅንነት ማለት በክርስቶስ አምኖ በልብ መለወጥ ነው። ደኅንነት ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመልን ተግባር ላይና ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን በመስጠታችን ላይ የተመሠረተ ነው።

42ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ኖስቲካውያን ስለ ኢየሱስ ማንነት የሚያምኑት ምን ነበር? ለ) ኖስቲካውያን ስለዚህ ስለተፈጠረው ቁሳዊ ዓለም ምን ያምኑ ነበር? ሐ) ኖስቲካውያን ሰው በምን መንገድ ደኅንነትን ያገኛል ይላሉ? መ) ኖስቲካውያን ከአቢዮናውያን እንዴት ይለያሉ? ሠ) ከእነርሱ የሐሰት ትምህርት የተነሣ ስለ ኢየሱስ ምን ግንዛቤ እየጠራ ግልጽ እየሆነ ሄደ?

43ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ከኃጢአት በስተቀር፥ ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ሰው ነው የሚለውን እውነታ በመቀበል ረገድ ችግር ያለባቸው የምታውቃቸው ሰዎች አሉ? ለ) ስለ እነርሱ የምታውቁትን ጻፉ። ሐ) ክርስቶስ በእውነት ሰው መሆኑን የሚያስተምሩ የትኞቹን ከፍለ ምንባቦች አቅርባችሁ አብራችኋቸው ትወያያላችሁ?

44ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ውስጥ ከሁሉ የበለጠው ነገር መንፈሳዊ ምሥጢራትን መገንዘብ ነው ብለው የሚያምኑ፥ የምታውቁዋቸው ሰዎች አሉ? ለ) ስለ እነዚህ ሰዎች የምታውቁትን ጻፉ። ሐ) በዓለም ያለው ቁስ አካል ሁሉ ክፉ ነው ብለው የሚያምኑ የምታውቋቸው ሰዎች አሉ? ስለ እነዚህ ሰዎች ያላችሁን ተሞክሮ ጻፉ።

ኖስቲካውያን ይህ ቁሳዊ ዓለም ክፉ በመሆኑ ኢየሱስ እውነተኛ ሰው ሊሆን አይችልም ብለው አመኑ። እንደዚሁም ወደ ደኅንነት የሚያደርሰው መንገድ በመንፈሳዊ ምሥጢራት ግንዛቤ ነው አሉ። ዛሬም በጎብረተሰቦቻችን ውስጥ የዚህ ዓይነት ተመሳሳይ እምነት ያላቸው ሰዎች አሉ። አንዳንድ ክርስቲያኖች መሆናቸውን እየተናገሩ ኢየሱስ እውነተኛ ሰብእና እንዳለው አያምኑም። እነዚህ ወገኖች ኢየሱስ ሥጋ የለበሰ አምላክ ነወ ቢሉም፥ እንደ እኛ ሰው እንደ ነበረና ሰብአዊ ነፍስና ሰብአዊ መንፈስ እንደ ነበረው ይክዳሉ። ነገር ግን በዮሐንስ ምዕራፍ 1፥ በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 2፥ እንደዚሁም በዕብራውያን ምዕራፍ 2 እና በሌሎችም ክፍለ ምንባቦች ላይ እንደተገነዘብነው ኢየሱስ ከኃጢአት በስተቀር እንደ እኛው ሰው መሆኑን ተምረናል። እኛን ለማዳን ሲል ሰው መሆን እንዳለፈለገውም ተመልክተናል። ራሳቸውን ክርስቲያኖች ብለው የሚጠሩ በጎብረተሰቦቻችን መካከል የሚገኙ

አንዳንድ ሰዎች ጥልቅ የመንፈሳዊ ምሥጢራት ግንዛቤ ካላቸውና መንፈሳዊ ቃላትንም ካወቁ መንፈሳዊ ኃይልና ደኅንነትን የሚያገኙ ይመስላቸዋል። ነገር ግን በሚቀጥለው ትምህርታችን ላይ ደኅንነት በዕውቀት ወይም በልዩ ግንዛቤ የሚገኝ አለመሆኑን እንማራለን። ደኅንነት ፈቃድንና ልብን በመለወጥ ይመጣል።

ሞናርካዊነት ወይም ስባልዮሳዊነት

በጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ኢቢዮናዊነት ከተወገዘ በኋላ የእግዚአብሔርን አንድነት የሚያስጠብቅ የመሰለ የሐሰት ትምህርት ተነሣ። እነዚህ ቡድኖች «ሞናርካዊነት» በተባለ አስተምህሮ ያምኑ ነበር። እነርሱም እግዚአብሔር አንድ በመሆኑ ላይ አጥብቀው አጽንኦት ይሰጡ ነበር። ነገር ግን እነዚህ ቡድኖች የሚያታግል ጥያቄ ነበራቸው፣ ጥያቄያቸው እግዚአብሔር አንድ ከሆነ ኢየሱስ በምን አኳኋን እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል? የሚል ነበር። ከእነዚህ አንዱ የሞናርካዊነት ቡድን ደግሞ ከኢቢዮናውያን ጋር የሚመሳሰል ትምህርት ያስተምሩ ነበር። እነርሱም ኢየሱስ ሰው ነበር፥ ነገር ግን ጻድቅ የሆነ ሰው ነበር። ስለሆነም እግዚአብሔር ይህን ጻድቅ ሰው (ኢየሱስን) በጥምቀቱ ጊዜ ወስዶ በተለየ መንገድ ተገለገለበት ይላሉ። ቤተ ክርስቲያን ኢቢዮናውያንን በተቃወመችበት መንገድ መልስዋን በመስጠት ትምህርታቸው ሐሰተኛ መሆኑን አጋልጣለች። ነገር ግን ሁለተኛ ዓይነት ሞናርካዊነትም ነበር። ይህ ቡድንም በእግዚአብሔር አንድነት ላይ አጽንኦት ነበረው። እነዚህም አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ፥ ይህም እግዚአብሔር በተለያዩ አካላት አማካይነት ራሱን ገልጧል ይላሉ። እነርሱም አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ራሱን እንደ አብ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ እንደ ወልድ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ ራሱን እንደ መንፈስ ቅዱስ ገለጠ ብለው ያስተምራሉ። ስለዚህ እነዚህ ቡድኖች ኢየሱስ እግዚአብሔር በመሆኑ ላይ ቢስማሙበትም፥ ነገር ግን ከእግዚአብሔር አብ ጋር አንድ አካል ነው ይሉ ነበር። የዚህ ሐሰት ትምህርት ዋናው መምህር ሳባልዮስ የተባለ ሰው ነበር። ከዚህ የተነሣ አንዳንድ ጊዜ ትምህርቱ ሳባልዮሳዊነት ተብሎ ይጠራል።

45ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ሞናርካውያን ዋና ትኩረት ይሰጡዋቸው የነበረው ምንን ነበር? ለ) ሰባልዮስ ስለ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ያስተማረው ምን ነበር?

46ኛ ጥያቄ፡– ማቴዎስ 3፡13–17፤ 28፡19–20፥ እንዲሁም 2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14 አንብቡ። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የሳባሊዮስ ትምህርቶች ሐሰት መሆናቸውን የሚያጋልጥ ምን አሳቦች ታያላችሁ?

ሞናርካውያን ሁሉ በእግዚአብሔር አንድነት ላይ አጽንኦታቸውን ያደርጋሉ። ማለትም እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው ይላሉ። ብዙዎቹ የሳባሊዮስን አስተምህሮ በመከተል፥ እግዚአብሔር አንድ ሲሆን፥ ራሱን ግን በተለያዩ አካላት ወይም አምሳል ገልጧል በማለት ያምናሉ። ይህን ሲሉ አንዱ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ እንደ አብ፥ በሌላ ጊዜ እንደ ወልድ፥ እንዲሁም በሌላ ጊዜ ደግሞ እንደ መንፈስ ቅዱስ ራሱን ገልጧል ማለታቸው ነው። ሳባሊዮስ ያስተማረው ራሱን በተለያዩ ሦስት መንገዶች የገለጠ አንድ

እግዚአብሔር ብቻ አለ ብሎ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ አያሌ ጥቅሶች የሳባሊዮስ አስተምህሮ ሐሰት መሆኑን ያረጋግጣሉ። ኢየሱስ በጥምቀቱ ጊዜ ውኃው ውስጥ ቆሞ ሳለ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ ሲያርፍበት፥ ከሰማይ ደግሞ የእግዚአብሔር ድምፅ ሲመጣ ተሰምቶአል። ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ በአብ፥ ሌላ ጊዜ በወልድ እንዲሁም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ በተለያየ ሁኔታ የሚገለጥ እንዳይደለ ግልጽ ነው። ሁሉም የሥላሴ አካላት በአንድ ጊዜ በተለያዩ ሁኔታዎች ይገለጣሉ። በሁለቱም በማቴዎስ 28፡19–20 እና በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14፤ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሁሉም አንድ አምላክ የሆኑ ራሳቸውን የቻሉ አካላት መሆናቸው ተገልጾአል። ስለዚህ የሳባሊዮስ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባለመሆኑ በጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ተወግዟል።

47ኛ ጥያቄ፡– ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሳባሊዮስን አስተምህሮ የተከተለ ምን የሐሰት ትምህርት ታውቃላችሁ?

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሳባሊዮስን የሐሰት ትምህርት የሚከተሉ ቡድኖች «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» አማኒያን የሚባሉ አሉ። «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» ሳባሊዮስ እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም አንዳንድ ጊዜ እንደ አብ፥ በሌላ ጊዜ እንደ ወልድ፥ እንዲሁም ደግሞ እንደ መንፈስ ቅዱስ ራሱን ይገልጣል ብሎ ያለውን የስሕተት ትምህርት በቀጥታ ይከተላሉ። ከእነዚህ ቡድኖች መካከል አንዳንዶቹ ስሜታዊ የሆኑ ዝማሬዎችን ስለሚያሰሙና እምነታቸውንም በዚሁ ስሜት ስለሚያስፋፉ በጣም ተቀባይነት አግኝተዋል። ስለዚህ ብዙ ሰዎች እነዚህ ቡድኖች ትክክለኞች ናቸው፤ ምክንያቱም የሚታይባቸው ደስታና የመንፈስ ግለት ይህን ይመሰክራል ይላሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምረን እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሦስት አካላት እንጂ የአንድ አምላክ ልዩ ልዩ መገለጫዎች አይደሉም። የሳባሊዮስ አስተምህሮት ሐሰት መሆኑ ቢታወቅም ቤተ ክርስቲያን የሥላሴን አስተምህሮ በተመለከተ በማያሻማ ሁኔታ ጥርት ያለ ግንዛቤና አቋም እንዲኖራት በማድረግ በኩል ረድቷታል። በዚህ መሠረት የሥላሴ አስተምህሮ እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነው የሚል ጽኑ አቋም ያዘ።

አርዮሳዊነት

ከጥንት መምህራን አንዳንዶቹ የሳባሊዮስን የሐሰት አስተምህሮ ቢታወሙም ራሳቸው ወደ ባሰ ስሕተት መውደቃቸው አልቀረም። እነርሱም ያቀርቡት የነበረው ክርክር እግዚአብሔር አንድ ከሆነ፥ ወልድ አብን ካልሆነ፥ እንግዲያውስ ወልድ ከአብ ያንሳል፥ ወልድ የእግዚአብሔር አምሳያ ነው የሚል ነበር። አርዮስ የተባለ አንድ መምህር በዚህ ትምህርቱ ታዋቂ ሆኖ ነበር። ይህ ሰው ሲያስተምር አብ ከወልድ በፊት ነበር፥ አብ ወልድን ፈጥሮታል፥ በተጨማሪም ወልድ በሕልውና ያልነበረበት ጊዜ ነበር ይላል። እንደዚሁም እርሱ እንደሚያምነው ወልድ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው

ፍጥረታት የመጀመሪያውና ዋናው ነው። ቀጥሎም አብ ወልድን ከፈጠረ በኋላ በእርሱ አማካይነት ሌሎችን ፍጥረታት ሁሉ ፈጥሮአል ብሎ ያስተምር ነበር። አርዮስና ተከታዮቹ በቆላስይስ 1፡15 ላይ፥ «እርሱ የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው» የሚለውን ጥቅስ በራሳቸው መንገድ በመተርጎም ወልድ መጀመሪያ አለው፥ ስለዚህም በአብ ተፈጥሮአል ብለው ሊያስተምሩ ችለዋል። እንደዚሁም ኢየሱስ በዮሐንስ 14፡28 ላይ፥ «አብ ከእኔ ይበልጣል» ያለውን ሐረግ በመምዘዝ፥ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ የሚያንስ መሆኑን ራሱ ተናግሯል ሲሉ ይከራከራሉ።

48ኛ ጥያቄ፡– ሀ) አርዮስ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ምን ሲል አስተማረ? ቢያንስ ሦስት ነጥቦችን ጻፉ። ለ) አርዮስ ትምህርቱን የሚደግፉ የትኞችን ጥቅሶች ተጠቀመ?

49ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 14፡28 አንብቡ። ይህ ጥቅስ ስለ አብና ወልድ ምንን የሚያስተምር ይመስላችኋል?

አርዮስ በትምህርቱ ወልድ የእግዚአብሔር አምሳያ እንጂ ራሱ አብ አልነበረም ሲል አስተምሮአል። እንደዚሁም ወልድ በህልውና ያልነበረበት ጊዜ ነበር፥ የተፈጠረውም በአብ ሲሆን የፍጥረታት ሁሉ በኩር ነው። ፍጥረታት ሁሉ በእርሱ አማካይነት ተፈጥረዋል ብሎ አስተምሯል። ለዚህም አርዮስ አሳቤን ይደግፋኛል ብሎ የጠቀሰው ቆላስይስ 1፡15 እና ዮሐንስ 14፡28 ናቸው።

ዮሐንስ 14፡28 በእርግጥ የሚያስተምረው ለምንድን ነው? በዮሐንስ 14 ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ትቶአቸው የሚሄድ በመሆኑ ያጽናናቸዋል። አብ ወዳለበት ወደ ሰማይ ቤቱ እንደሚመለስ ነግሮአቸው ነበር። የእርሱ መኖሪያ ወደሆነውና ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ወደነበረው ክብር፥ እንዲሁም አብ ወዳለበት የክብር ስፍራ ይመለሳል። ስለዚህ ኢየሱስ የአብን ክብር ወልድ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ከነበረው ክብር ጋር ያመዛዝናል። እርሱ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የአብ ክብር፥ ከእርሱ ክብር በጣም የላቀ ነበር። ስለዚህ እዚህ ላይ ኢየሱስ «አብ ከእኔ ይበልጣል» ሲል፥ እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም ማለቱ አይደለም። መግለጽ የፈለገው እርሱ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ አብ የነበረውን ክብር ነው።

እንደዚሁም በትምህርት አንድ ውስጥ በቆላስይስ 1፡15 እንደተመለከትነው ኢየሱስ የመጀመሪያው ፍጡር አይደለም። «እርሱ የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው» የሚለው ኢየሱስ በጊዜ የመጀመሪያው ነው ማለት ሳይሆን ከፍጥረታት ሁሉ በላይ ነው ለማለት ነው። እንደዚሁም ቆላስይስ ምዕራፍ 1 ኢየሱስ በእግዚአብሔር ባሕርይ የተሞላ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪና የእግዚአብሔርም መገለጫ ነው በማለት ያስተምራል። በተጨማሪም ቆላስይስ ምዕራፍ 1 ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ የእግዚአብሔር አምሳል ብቻ አለመሆኑን ያረጋግጣል።

50ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የአርዮስን የተሳሳተ ትምህርት የሚከተሉ ምን ቡድኖች አሉ? ስለ እነዚህ ሰዎች የምታውቁትን ጻፉ። ለ) ከአጠናናቸው ጥቅሶች የትኞቹ የእነዚህ ቡድኖች አስተምህሮ ሐሰት መሆኑን ያጋልጡ?

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በብዛት ይህን የሐሰት የአርዮስ ትምህርት የሚከተሉት የይሖዋ ምስክሮች ናቸው። ልክ እንደ አርዮስ እነርሱም ወልድ የእግዚአብሔር አምላል ነው፥ ስለሆነም እግዚአብሔር አይደለም ይላሉ። ዮሐንስ 1፥ ፊልጵስዩስ 2፥ ቆላስይስ 1 እና ሌሎችም በትምህርት አንድ ላይና ቀደም ሲል በዚህ ትምህርት ያጠናናቸው ጥቅሶች ወልድ ከእግዚአብሔር አምላል በላይ መሆኑንና እርሱ ራሱ አምላክ መሆኑን ያረጋግጣሉ። ሆኖም ግን የይሖዋ ምስክሮች የራሳቸው ትርጉም የሆነ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ አላቸው። ታዲያ አብዛኛዎቹ የተማሩት እነዚህ ጥቅሶች እንደተጻፉት አለመሆናቸውን ነው። እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ሆኖ ሊገኝ አይችልም፥ ሲያስቡትም አይሆንም ይላሉ። እነዚህን የይሖዋ ምስክሮች ወደ ክርስቶስ ለማምጣት እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይዞ ከእነርሱ ጋር መከራከር አያስፈልግም፥ ነገር ግን እኛ ማድረግ የሚገባን በዕለታዊ ኑሮአችን ውስጥ የክርስቶስን ፍቅር ለእነርሱ ማሳየት ነው።

ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን የአርዮስን አስተምህሮ አጥብቃ አውግዛለች። በ325 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኒቂያ ጉባዔ አድርገው የክርስትና እምነት መግለጫ አዘጋጅተዋል። የእምነት መግለጫው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተውጣጡ ክፍሎች ላይ የተመሠረተ ሆኖ በተለይ የአርዮስን አስተምህሮ የሚቃወም ነው። መግለጫውም፥ «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ ከሁሉ በላይ የላቀ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ ከአብ ጋር እኩል የሆነ» ይላል። ምንም እንኳን የአርዮስ ትምህርት የተሳሳተ መሆኑ ቢታወቅም፥ ቤተ ክርስቲያን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ትክክለኛው ግንዛቤ እንዲኖራት በማድረግ ረገድ ረድታታል። እርሱ የእግዚአብሔር አምላል ብቻ አልነበረም። ራሱ አምላክ ነበር። ከእግዚአብሔርም ጋር ህልውናው አንድ ነው።

51ኛ ጥያቄ፡- የኒቃያው ጉባዔ የአርዮስን ትምህርት እንዴት አወገዘው?

በዚህ በኒቂያ ጉባዔ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን በሚመለከቱ አንዳንድ እውነቶች ረገድ ቤተ ክርስቲያን በጣም ግልጽ ነበረች። ኢቢዮናዊነትን፥ ኖስቲካዊነትን ሞናርካዊነትን፥ እና አርዮሳዊነትን አውግዘዋል። ልክ እንደ እግዚአብሔር አብ፥ ኢየሱስም ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ አምነዋል። በመለኮትነቱ፥ ከእግዚአብሔር፣ አብ ጋር በአካል አንድ እንዳልሆነ፥ ነገር ግን በባህሪ አንድ እንደ ሆነ ያምናሉ። ፍጹም ሰው እንደሆነና፥ ነገር ግን ያለ ኃጢአት እንደ ሆነ ያምናሉ። ይሁን እንጂ፥ ኢየሱስ እንዴት ሊሆን ነው በአንድ ጊዜ በአንድ አካል አምላክም ሰውም የሚሆነው? የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በዚህ አስቸጋሪ ጉዳይ ላይ ለመወሰን ሞክራለች። በሚቀጥለው ሳምንት ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ አምላክነትና ሰብአዊነት ጥምረት ለመግለጽ እንዴት ሙከራ እንዳደረጉ እንመለከታለን።

አምስተኛ ቀን

በሳምንቱ ውስጥ ስለ ክርስቶስ ተሠገዎ የተማራችሁትን ከልሳችሁ ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጁ።

ሳምንታዊው የስብሰባ ጊዜ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ፡– መሪው በዚህ ሳምንት ውስጥ ከሚሰጠው ትምህርት ወይም ጥቅስ ወስዶ ከአምስት እስከ አሥር ደቂቃ ለሚደርስ የጥሞና ጊዜ ያውል።

2. ሳምንታዊ የጸሎት ጊዜ፡– አሥር ደቂቃ በጸሎት ላይ አሳልፉ። ኢየሱስን በበለጠ እንድናውቀው፥ እንደዚሁም ትሕትናንና ለሌሎች በጎውን መሻትን በተመለከተ በፈቃዳችን የኢየሱስን ምሳሌ እንድንከተል እንጸልይ።

3. ክለሳ፡– በዚህ ሳምንት በተከታተላችሁት ትምህርት ላይ ያስቸገሩዋችሁ ጥያቄዎችና መልስ ያጣችሁላቸው የትኞቹ እንደሆኑ ለመመልከት የአሥራ አምስት ደቂቃዎች ክለሳ አድርጉ።

4. ተወያዩ፡–

   ሀ) ኢየሱስን ማወቅ እግዚአብሔርን የተሻለ ለማወቅ እንዴት ይረዳናል? ኢየሱስን በበለጠ ለማወቅ የሚያስችሉን መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

   ለ) እኛ የራሳችንን ጥቅም ሳናስቀድም ሌሎችን ለመርዳት ስለምንችልባቸው ልዩ ሁኔታዎች ተወያዩ። እያንዳንዱ የቡድን አባል አስቸጋሪ የሆነውን ነጥብ እያነሣ ይወያይ።

   ሐ) የኢየሱስን ፍጹም ሰብአዊነትና ተሠገዎ፥ አማኞች ስለ ደኅንነታቸው ምልዐተ በረከት ለመገንዘብ እንዲችሉ በማድረግ ረገድ ስላለው ጥቅም ከተሠገዎ የሚፈልቀውን እውነት በመግለጽና በመኖር ትርጉም ያለው አምልኮና ታዛዥነትን የተሞላ ክርስቲያናዊ ሕይወትን እንዴት ማነሣሣት እንችላለን?

   መ) ስለ ኢየሱስ ተሠገዎና ሰብአዊነት የሚኖር ግንዛቤ እንዴት አድርጎ አማኞች ያልሆኑ ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ብርታት ሊሆናቸው ይችላል?

   ሠ) በአካባቢአችሁ የትኞቹን የጥንት ቤተ ክርስቲያን የሐሰት ትምህርቶች ትመለከታላችሁ? የተለያዩ የቡድን አባላት እንዲህ ካሉት ሰዎች ጋር የነበራቸውን ልምድ እንዲያካፍሉና እንዲወያዩ ይሁን። የእነዚህ ሐሰት ትምህርቶች አባል ከሆኑት መካከል ወደ ክርስቶስ የመጡ አሉ? ከሆነ እንግዲህ የቡድኑ አባላት እነዚህ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ሊመጡ የቻሉባቸውን ምክንያቶች በጋራ ይወያዩ።

ትምህርት አራት

ተሠገዎ፥ ክፍል 2

ባለፈው ሳምንት የተሠገዎ ምሥጢርን በጥንቃቄ ማጥናት መጀመራችንን ታስታውሳላችሁ። በዚህ ጥናት ውስጥ ኢየሱስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መሆኑን ተምረናል። ነገር ግን በአንድ ሰው ተፈጥሮ ውስጥ እንዴት አድርጎ ፍጹም እግዚአብሔርና ፍጹም ሰው የሆነ የባሕሪ ውህደት ሊኖር ይችላል? ባለፈው ሳምንት፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ስላለው የአምላክነትና ሰብአዊነት ውህደት የሚያስተምሩ ሦስት ቁልፍ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን መርምረናል። እነርሱም ዮሐንስ 1፥ ፊልጵስዩስ 2 እና ዕብራውያን 2 ነበሩ። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ስለ ኢየሱስ ተሠገዎ እንዴት አሁን ወደአለችበት የግንዛቤ ደረጃ ልትደርስ እንደ ቻለች ታሪኳን ማጥናት በጣም ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ይህን ስናደርግ የተለያዩ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ ተሠገዎ እምነታቸው ምን እንደሆነ በትክክል ለማወቅ እንችላለን። ባለፈው ሳምንት ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን፥ እንዴት ቀስ በቀስ ኢየሱስ ሰውም አምላክም መሆኑን ልትረዳ እንደ ቻለች ማጥናት መጀመራችን የሚታወስ ነው። በኒቂያው ጉባዔ ጊዜ ማለትም በ325 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ፍጹምም ሰው ስለ መሆኑ ሙሉ ስምምነት ላይ ደርሳ ነበር። ሆኖም ግን ጉባዔተኞቹ ፍጹም እግዚአብሔርና ፍጹም ሰው እንዴት በአንድ አካል መዋሃድ እንደ ቻሉ ወደ ማብራራቱ ደረጃ ገና አልደረሱም ነበር። ሆኖም በዚህ ሳምንት ትምህርታችን ላይ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን እንዴት ወደዚህ የክርስቶስ ተሠገዎ ሙሉ ግንዛቤ ላይ እንደ ደረሰችና አያይዘንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥንትም ሆነ ዛሬ የተሠገዎን ምሥጢር እንዴት እንደተረዳችው እንማራለን።

የመጀመሪያ ቀን

ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ላይ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ስለ ኢየሱስ የተሠገዎ ባሕርይ እንዴት አድርጋ ግንዛቤዋን ልታዳብር እንደ ቻለች ተመልክተን ነበር። በኒቂያው ጉባዔ ላይ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው መሆኑን ተቀብላለች። ነገር ግን የክርስቶስ አምላክነትና ሰብአዊነት እንዴት በአንድ አካል ውስጥ ተዋሃደ? ብዙ ክርስቲያኖችም ክርስቶስ በአንድ ጊዜ እግዚአብሔርም ሰውም ስለ መሆኑ መወያየት ጀምረው ነበር። ይህ ውይይት ለተራዎቹ ምእመናንም ቢሆን በጣም አንገብጋቢ ነበር። ምክንያቱም ዘላለማዊው ደኅንነታቸው የተመሠረተው በክርስቶስ አምላካዊና ሥጋዊ ውህደት ትክክለኛ እምነት ላይ ስለሆነ ነው።

አቡሊናርዮሳዊነት

አቡሊናርዮስ የተባለ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ክርስቶስ እንዴት መለኮትም ሰውም ሊሆን እንደ ቻለ ለማብራራት ሞክሮ ነበር። በዚህ

ትምህርቱም ክርስቶስ ሰብአዊም፥ መለኮታዊም የሆነ ሁለት ባሕርይ አለው ብሎ መግለጽ ስሕተት ነው ብሎ አስተምሮአል። ይልቁኑ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ብቻ አለው ብሎ አስተማረ። ክርስቶስ የተለየ ሰብአዊ ባሕርይ ካለው ይህ ሰብአዊ የባሕርይው ክፍል እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም ሲል አመለካከቱን አስቀመጠ። በመሆኑም ከክርስቶስ ባሕርይ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ውህደት የሌለው ቢኖርበት ኖሮ ዓለምን ከኃጢአቱ ባላዳነው ነበር አለ። ስለዚህም አቡሊናርዮስ የክርስቶስ አምላክነት ከሰብአዊነቱ ጋር ፍጹም ስለ ተዋሃደ አምላክነቱ ሰብአዊነቱን ውጦታል ብሎ አስተማረ። በእርሱ እምነት ክርስቶስ ሰብአዊ ነፍስና መንፈስ አልነበረውም። መለኮትነቱ የውስጣዊ ሲሆን፥ ሰብአዊ አካሉ ውጪአዊው ነው በማለት ተናግሮአል። ስለዚህም ክርስቶስ ከሌሎች የሰው ልጆች ሰብአዊነት የተለየ «መለኮታዊ ሰብአዊነት» ነበረው በማለት አስተማረ። በመቀጠልም የክርስቶስ አካልም ቢሆን ከሰው ልጆች አካል የተለየ ነው ሲል ለዚህም የሰጠው ምክንያት ከማይሞት ሥጋ የተሠራ መለኮታዊ አካል በመሆኑ ነው የሚል ነበር። በዚህ አኳኋን የአቡሊናርዮስን አስተምህሮ ስናስተውል፥ ስለ ክርስቶስ የአምላካዊነትና የሰብአዊነት ተዋህዶ የገለጸው የክርስቶስን ሰብአዊነት በሚያሳንስ ደረጃ ነው።

1ኛ ጥያቄ፡– ሀ) አቡሊናርዮስ የበለጠ ትኩረት የሰጠው ለክርስቶስ መለኮታዊነት ነው ወይስ ሰብአዊነት? ለ) አቡሊናርዮስ የክርስቶስ ሰብአዊነት ከእኛ ሰብአዊነት የተለየ ነው ሲል ምን ማለቱ ነበር? ሐ) ክርስቶስ ከኃጢአት በስተቀር እንደኛው ሙሉ በሙሉ ሰው ስለ መሆኑ፥ ለአቡሊናርዮስ ለማሳየት በትምህርት 2ና 3 ላይ ከነበሩት መካከል የትኞቹን ጥቅሶች ለማስረጃነት ታቀርባላችሁ? ስለዚህ የኢየሱስ ሰብአዊነት ከእኛ ሰብአዊነት ጋር ተመሳሳይ ስለ መሆኑ በሚያስረዱት ጥቅሶች በመመለስ ከልሏቸው።

አቡሊናርዮስ የአስተምህሮ ትኩረቱን ያደረገው በክርስቶስ አምላካዊነት ላይ ሲሆን፥ ነገር ግን ለሰብአዊነቱ በቂ የሆነ ትኩረትን አልሰጠም። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከዚህ ከአቡሊናርዮስ አስተምህሮ በመነሣት ኢየሱስ ክርስቶስ ሰብአዊ ነፍስና መንፈስ ያልነበረው ከሆነና የማይሞት ሥጋ የነበረው መለኮታዊ አካል ከሆነ፥ እውነትም እርሱ ልክ እንደ እኛ ሰው አልነበረም አሉ። ነገር ግን ኢየሱስ እውነተኛ ሰው ባይሆን ኖሮ የሰው ልጆችን ከኃጢአት ለማዳን ባልሞተ ነበር። በትምህርት 2 ላይ የተጠቀሱት እንደ ማቴዎስ 4፡2፤ 26፡38፤ ሉቃስ 23፡46፤ ዮሐንስ 4፡6፤ 19፡28፥ 34፤ ዕብራውያን 2፡5–18፤ 4፡15–16፤ ፊልጵስዩስ 2፡6–11 እና 1ኛ ዮሐንስ 1፡1 ያሉት ጥቅሶች ኢየሱስ ከኃጢአት በስተቀር ልክ እንደ እኛው ሰው መሆኑን ያሳመኑአቸው ነበሩ። ኢየሱስ ሰብአዊ ነፍስና መንፈስ ነበረው። የኢየሱስ አካልም ልክ እንደ እኛ አካል ያለ ነበር። ስለሆነም የአቡሊናርዮስ አስተምህሮ በቆስጥንጥኒያ በ381 ዓ.ም በተሰበሰበው የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ላይ ኑፋቄነቱ ተረጋግጦ ተወግዞአል።

2ኛ ጥያቄ፡– በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ላሉ ምእመናን የኢየሱስ ሰብእና ከእኛ ሰብእና ይለይ እንደሆነ ጥያቄ ብታቀርቡላቸው፥ መልሳቸው ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

በኢትዮጵያ ውስጥ በክርስትና ሃይማኖት በጥብቅ የሚያምኑ ብዙ ሰዎች፥ የኢየሱስ ሰብእና ከእኛ ሰብእና የተለየ እንደሆነ አድርገው ያምናሉ። ኢየሱስ አምላክም በመሆኑ በእውነት ሰው መሆኑን አምነው ለመቀበል ያዳግታቸዋል። ኢየሱስ ያለኃጢአት ከመሆኑ በስተቀር፥ ልክ እንደ እኛው ሰው መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስረዳል። ስለዚህ ኢየሱስ በእውነት ሰው ባይሆን ኖሮ የሰውን ልጆች ከኃጢአታቸው ለማዳን ሊሞት ባልቻለ ነበር።

ንስጥሮሳዊነት

አቡሊናርዮስ በአስተምህሮው ውስጥ የኢየሱስን ሰብእና ዝቅ አድርጎ ከማቅረቡ የተነሣ ተወግዞ ነበር። ነገር ግን የኢየሱስ አምላካዊነትና ሰብአዊነት እንዴት በአንድ አካል እንደ ተዋሃዱ ግልጽ በሆነ መንገድ ገና አልተደረሰበትም ነበር። በጊዜው በቆስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን መምህር የነበረ ንስጥሮስ የተባለ ሰው የመፍትሔ አሳብ አቀረበ። መፍትሔ ነው ብሎ አምኖበት ያቀረበው አስተምህሮ፥ ኢየሱስ መለኮታዊና ሰብአዊ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚል ነበር። ብዙዎቹ ሰዎች ንስጥሮስ ኢየሱስ ሁለት አንዱ በመለኮታዊ ሌላው ሰብአዊ አካላት አሉት ብሎ ማስተማሩን ተገነዘቡ። ኢየሱስ አንድ አካል የነበረው ቢሆንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ሰብአዊ አካሉ በመራብ፥ በመጠማትና በመድከም፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ መለኮታዊው አካሉ ተአምራትን በማድረግ ራሱን ይገልጽ ነበር። በአንድ አካል ውስጥ ፍጹም የተለየ መለኮታዊ ኢየሱስና ሰብአዊው ኢየሱስ መኖራቸውን ገለጸ። ንስጥሮስ፥ ድንግል ማርያም ኢየሱስን በወለደች ጊዜ፥ የወለደችው ሰብአዊውን ኢየሱስን ነው እንጂ መለኮታዊውን ኢየሱስ አልነበረም ሲል አስተምሮአል።

ንስጥሮስ በዚህ ትምህርቱ የተነሣ በግብፅ እስክንድሪያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን መሪ በነበረው በሰሪል (Cyril) ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ ደርሶበት ነበር። ሰሪል ኢየሱስ ፍጹምና እውነተኛ ሰው ነው የሚለውን የንስጥሮስ አቋም ቢቀበልም፥ ሰብአዊና መለኮታዊ ባሕርያቱ በአንድ አካል ተዋህደዋል ለሚለው አስተምህሮ ክብደትን ሰጥቷል። የክርስቶስ አንድ ባሕርይ ሁልጊዜ በውህደት እንደሚሠራ ገለጸ። በአንጻሩ ክርስቶስ አንዳንድ ጊዜ በሰብአዊነቱ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ በአምላካዊነቱ ይሠራል ብሎ መወሰን የክርስቶስን ሕልውና በሁለት አካላት መክፈል ነው ሲል ተከራከረ። ከዚህ የተነሣ ሰሪል ክርስቶስ ሁለት የተለያዩ አካላት ቢኖሩት ኖሮ የሰው ልጆችን የማዳን ተግባሩን ባላከናወነ ነበር የሚል አቋም ነበረው። እንዲሁም እንደ ሰሪል እምነት፥ ክርስቶስ በሰብአዊ አካሉ ብቻ ተሠቃይቶ ከሞተ፥ በሞቱ ምክንያት የተገኘው ደኅንነት በማንኛውም ዘመንና ጊዜ ለነበሩ የሰው ልጆች የተፈለገውን ውጤት ባልሰጠ ነበር፤ በአጠቃላይም ለፍጥረታት ሁሉ ባልበጀ ነበር። ስለዚህ ሰሪል ይህን ሲያብራራ የክርስቶስ የደኅንነት ተግባር በየዘመኑ ለነበሩትና ላሉት የሰው ልጆች ሁሉ ሊጠቅም የቻለውና ውጤታማ የሆነው ክርስቶስ በሰብአዊነቱና በመለኮታዊነቱ ሥቃይን ተቀብሎ በመሞቱ ነው ብሏል። ከዚህ ውጭ ያስተማሩትን ሲቃወምም ክርስቶስ በሰብአዊነቱ ብቻ

ተወለደ፥ ተሠቃየ፥ ሞተ፥ ወይም ይህን ወይም ያን ተግባር አከናወነ ብሎ ማስተማር ስሕተት ነው በማለት አቋሙን ገልጾአል። ምንም እንኳን ክርስቶስ በሰብአዊነቱና በአምላካዊነቱ አንዳንድ ጊዜ ልዩነቶችን ያሳየ ቢሆንም፥ በሁለት ተከፍሎአል ማለት እንዳልነበረ አመልክቷል። ስሪል በትምህርቱ ውስጥ ክርስቶስ በአንድ አካል አምላካዊውንና ሰብአዊውን ባሕርይ በውህደት አካትቶ ይዟል ሲል አስተምሯል።

3ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ንስጥሮስ ክርስቶስ ስንት ባሕርያት አሉት ብሎ አስተማረ? ለ) እንደዚሁም ክርስቶስ ስንት አካላት አሉት አለ? ሐ) ንስጥሮስ የኢየሱስን አምላካዊነትና ሰብአዊነት በተመለከተ አጽንኦት የሰጠው ለልዩነት ነው ወይስ ለአንድነቱ? መ) የንስጥሮስ አስተምህሮ ጠንካራና ደካማ ጎን ምንድን ነው?

4ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ስሪል ኢየሱስ ስንት ባሕርያት አሉት አለ? ለ) ስሪል ኢየሱስ እንደ አምላክና እንደ ሰው ለፈጸማቸው ተግባራት ክብደትና ትኩረትን የሰጠው ለአንድነቱ ወይስ ለተካፋይነቱ? ሐ) በስሪል አስተምህሮ ውስጥ ምን ጠንካራና ደካማ ጎን አያችሁ?

የንስጥሮስ አስተምህሮ በአብዛኛው ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር የሚቃረን መሆኑ ለብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግልጽ ነበር። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ ንስጥሮስ አስተምህሮ ኢየሱስ ሁለት ባሕርያ ይኑረው አይኑረው በጊዜው እርግጠኞች አልነበሩም። ሆኖም ግን ንስጥሮስ በአስተምህሮው ውስጥ በግልጽም ባይሆን እንዳለው ኢየሱስ ሁለት አካላት ስላለመሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እርግጠኞች ነበሩ። ንስጥሮስ በክርስቶስ አምላካዊነትና ሰብአዊነት መከፋፈል ላይ የተጋነነ ክብደት ሰጥ ለመግለጽ መሞከሩ ግልጽ ነው። ይህ የንስጥሮስ አስተምህሮ የኢየሱስ ፍጹም አምላክነትና ሰብአዊነት ክብደት መስጠቱ የትምህርቱ ጠንካራ ጎ ሲሆን፥ ደካማ ጎኑ ደግሞ ኢየሱስን በሁለት አካላት መክፈሉ ነበር በመሠረቱ ኢየሱስ ንስጥሮስ እንደሚለው አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔ አንዳንድ ጊዜ ሰው የመሆን ባሕርይ አልነበረውም። ኢየሱስ በባሕርይ ምን ጊዜም ቢሆን አምላክነቱና ሰብአዊነቱ ሳይለያይ በውህደት ያለ ነው ይህ ኑፋቄአዊ የሆነ የንስጥሮስ አስተምህሮ በ431 ዓ.ም ኤፌሶን ውስ በተደረገው ጉባዔ ላይ ተወግዟል። ምንም እንኳን የስሪል አስተምህ የክርስቶስን መለኮታዊና ሰብአዊ የአንድ አካል ውህደት በማስጠበቁ በኩ ጠንካራ አቋም ቢኖረውም፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እር በሚያስተምረው መንገድ የክርስቶስ መለኮታዊና ሰብአዊ ውህደ መፈጸሙን ለመቀበል ገና ከውሳኔ ላይ አልደረሱም ነበር። አንዳንዶቹ የቤ ክርስቲያን መሪዎች ይህ የስሪል አስተምህሮ ሰዎችን፥ ኢየሱስ ትክክለኛ ሰ አልነበረም ወደሚለው የአቡሊናሪዮስ የከህደት ትምህርት ይመልሳል ብለ ፈሩ።

አውጣኪነት

ቤተ ክርስቲያን አቡሊናርዮሳዊነትንና ንስጥሮሳዊነትን አውግዛለች። ነገ ግን የክርስቶስ አምላካዊና ሰብአዊ ባሕርይ እንዴት በአንድ አካል ይዋሃዳ

የሚለው ጥያቄ ገና አልተመለሰም ነበር። በሶሪያና በግብፅ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስሪል (Cyril) ኢየሱስ በአንድ አካል የተዋሃደ መለኮታዊና ሰብአዊ ባሕርይ አለው ብሎ ያስተማረውን ትምህርት ፈቅደውታል። በአኳያው ደግሞ የሮም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ ሁለት ባሕርያት በአንድ አካል ውስጥ የሚለውን አስተምህሮ መርጠዋል። ስሪል በ444 ዓ.ም ከሞተ በኋላ ደቀ መዝሙሩ የነበረው ዲስቆሮስ ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት አለው የሚለውን አስተምህሮ አጥብቆ ይቃወም ጀመር። እንዲያውም አውጣኪ የተባለው መነኩሴ ከዚህ ጠልቆ በመግባት፥ የክርስቶስ አምላክነትና ሰብአዊነት በተዋሃዱ ጊዜ፥ ሁለቱም ባሕርያቱ በአንድ ተጣምረው ሰብአዊነቱ በአምላክነቱ ውስጥ ስለ ተዋጠ ሥጋው እንኳ ሰብአዊ መሆኑ ቀርቶ መለኮታዊ ሆኗል ሲል አስተማረ። የአውጣኪ አስተምህሮ፥ የአቡሊናርዮሳዊነትን ትምህርት በተሃድሶ ያመጣ ይመስላል።

5ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በግብፅና በሶሪያ በነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ የትኛው የተሠገዎ አስተምህሮ ተወዳጅነትን አገኘ? ለ) የሮም ቤተ ክርስቲያን መሪዎችስ የትኛውን የተሠገዎ ትምህርት መረጡ? ሐ) አውጣኪ ስለ ክርስቶስ አምላካዊና ሰብአዊ ተዋህዶ ምን አስተማረ?

በግብፅና በሶሪያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘው በአንድ አካል ውስጥ የመለኮታዊና ሰብአዊ ውህደት የሚለውና በሮም ቤተ ክርስቲያን ዘንድ የተመረጠው ሁለት ባሕርያት በአንድ አካል የሚሉት አስተምህሮዎች ለቤተ ክርስቲያናቱ መለያየት ምክንያት ሆኑ። አውጣኪ የክርስቶስ መለኮታዊው ባሕርይ ሰብአዊውን ባሕርይ ዋጠው ያለው አገላለጽ የኢየሱስን ሰብአዊነት ዝቅ ያደረገ ነበር። ለዚህ ችግር መፍትሔ ለመሻት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሌላ ጉባኤ መቀመጥ አስፈለጋቸው።

የኬልቄዶን ጉባዔ (451 ዓ.ም)

በዚህ በክርስቶስ ባሕርይ ላይ ለቀረቡት አስተምህሮዎችና ክርክሮች ክለምምነት ደርሶ ውሳኔ ለመስጠት፥ በ451 ዓ.ም በኬልቄዶን ላይ በተደረገው ጉባዔ ላይ ብዛት የነበራቸው የቤተ ክርስቲያናት መሪዎች ተሰበሰቡ። በዚህ ጉባዔ ላይ የነበሩት አብዛኛዎቹ የሮም ሊቀ ጳጳሳት የሌዎን አሳብ ለመከተል ወሰኑ። ፓፓ ሌዎ የክርስቶስን ፍጹም አምላካዊነትና ፍጹም ሰብአዊነት መሠረተ እምነት ለመጠበቅ የላቀው አካሄድ ሁለት ባሕርያት ማለትም ሰብአዊና አምላካዊ ባሕርያት እንዳሉት መቀበል ነው አለ። በመቀጠልም እነዚህ ሁለት ባሕርያት በአንድ አካል ውስጥ ፍጹም ሆነው የተዋሃዱ መሆናቸውን ገለጸ። እንደዚሁም የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርያት ከመለኮታዊው ጋር አይነካኩም፤ መለኮታዊውም ባሕርያት ከሰብአዊው ጋር አይነካኩም ሲል ተናግሯል። ክርስቶስ በሥጋዊ ባሕርይው እንደ ረሃብ፥ ጥማትና ሞት ያሉ አንዳንድ ሁኔታዎች ታይተውበታል። በአምላክነቱ ደግሞ ተአምራትን የመሳሰሉትን አድርጓል። ይሁን እንጂ ክርስቶስ ምን ጊዜም አንድ አካል ነበር እንጂ አንድ ጊዜ እግዚአብሔር በሌላ ጊዜ ሰው አልነበረም።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኬልቄዶን ጉባዔ ላይ ኢየሱስ በአንድ አካል ሁለት ባሕርያት አለው ሲሉ የሃይማኖት መግለጫ አውጥተዋል። በምዕራብ የነበሩ ሁሉም ቤተ ክርስቲያናት ይህ የተሠገዎን ምሥጢር ለመገንዘብ የላቀ መንገድ ነው በማለት መግለጫውን ተቀብለውታል። እነርሱም ኢየሱስ በአንድ አካል ሁለት ባሕርያት አሉት፥ በዚህም ፍጹም አምላክነቱና ፍጹም የሆነ ሰብአዊነቱ ፍጹም በሆነ አንድነት ተጠብቆአል በማለት ተስማሙ። በግብፅና በሶሪያ ከነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ጥቂቶቹም የኬልቄዶንን ውሳኔ ተቀብለዋል። ነገር ግን ብዙዎች የግብፅና የሶሪያ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የኬልቄዶንን ጉባዔ ውሳኔ ሳይቀበሉ ቀርተዋል። እነርሱም ይህን ቅዋሜያቸውን ሲያብራሩ፥ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት ማለት ባሕርያቱን ከልክ በላይ መከፋፈል ስለሆነ፥ ይህ ድርጊት በደኅንነታችን ላይ አደጋ ያስከትላል ብለዋል። ከእነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዳንዶቹ አውጣኪ፥ የኢየሱስ ሰብአዊነትና አምላክነት ውህደት ፍጹም ከመሆኑ የተነሣ ከእኛ ሰብአዊነት የተለየ ነው በማለት ያቀረበውን አሳብ ተቀብለው ነበር። ሌሎች ደግሞ በዚሁ በኬልቄዶን ጉባዔ ላይ የኢየሱስ ሰብአዊነት ከሌሎች ሰዎች ሰብአዊነት ጋር ይመሳሰላል በማለት አምላካዊና ሰብአዊ ባሕርይው በአንድ አካል ውስጥ ይዋሃዳሉ የሚለውን አልተቀበሉም። እነዚህኞቹ ወገኖች ይህ አስተምህሮ ክርስቶስን በጣም የሚከፋፍልና ባለ ሁለት ባሕርያት አድርጎ የሚያቀርብ ነው ባይ ነበሩ። ይልቁንም ኢየሱስ አንዳንድ ጊዜ እንደ አምላክ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደ ሰው የሚታይና የሚሠራ አልነበረም ለሚለው አስተሳሰብ ክብደትን ሰጡ። ይህን ሲያጠናክሩም እርሱ ምን ጊዜም ቢሆን ሲሠራ የታየው ሰብአዊም መለኮታዊም ባሕርይ ተዋህዶት ነው ብለዋል።

6ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በኬልቄዶን የተደረገው ጉባዔ ስለ ክርስቶስ መለኮታዊና ሰብአዊ የተሠገዎ ውህደት የሰጠው ማብራሪያ እንዴት ያለ ነበር? ለ) በኬልቄዶን የተደረገውን ጉባዔ የተቀበሉት የትኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው? ሐ) የኬልቄዶንን ጉባዔ ያልተቀበሉትስ አብያተ ክርስቲያናት የትኞቹ ነበሩ?

በኬልቄዶን ጉባዔ ያልነበረ አስተምህሮ ወደ ኢትዮጵያ መጣ።

በምዕራብ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በኬልቄዶን ጉባዔ ላይ የተገለጸውን ክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይና መለኮታዊ ባሕርይ አለው፥ እነዚህ ባሕርያት በአንድ አካል የተዋሃዱ ናቸው የሚለውን ተቀብለዋል። ነገር ግን በግብፅና በሶሪያ የነበሩ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የኢየሱስ ሁለት ባሕርያት በአንድ ባሕረ ተጣመሩ የሚለውን አስተምህሮ መረጡ። ለዚህ የአስተምህሮ ውዝግብ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልስ ምን ነበር?

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር ትስስር አድርጋ ቆይታለች። ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር ከነበራት ከዚህ የቅርብ ትስስር የተነሣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልክ እንደ ግብፅ ቤተ ክርስቲያን የኬልቄዶን ጉባዔ ያስተላለፈውን ውሳኔ ውድቅ አድርጋዋለች። እንዲያውም ወደ 400 ዓ.ም መገባደጃ ገደማ ተስዓቱ ቅዱሳን (ዘጠኙ ቅዱሳን) ከመጡ በኋላ ኢትዮጵያ የኬልቄዶንን ጉባዔ ያለመቀበልዋ ሁኔታ

ይበልጥ የከረረ ሆነ። እነዚህ ዘጠኝ ቅዱሳን የመጡት ከሶሪያ ሲሆን፥ የኬልቄዶንን ጉባዔ ውሳኔ በጥብቅ ውድቅ አድርገውታል። ቅዱሳኑም የክርስቶስ አካል አሃዳዊነት ሊጠበቅ የሚችለው ስለ እርሱ ባሕርይ አሃዳዊነት በማስተማር ነው የሚል እምነት ነበራቸው። ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ምክንያት የኬልቄዶኑን ጉባዔ ውሳኔ ስላልተቀበሉ በአገራቸው ስደት ስለደረሰባቸውና ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ብቻ አለው የሚለው ትምህርታቸውን ለማስፋፍት ሳይሆን አይቀርም። እነዚህ ዘጠኙ ቅዱሳን መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግዕዝ ተርጉመዋል። በኢትዮጵያ ውስጥም እየተዘዋወሩ ሰብከዋል፤ አስተምረዋልም። ከእነርሱ ስብከትና ትምህርት የተነሣ ብዙ ሰዎች ክርስትናን ሊቀበሉ ችለዋል። በጊዜያቸውም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተዋል። በዚሁ ጊዜ የክርስቶስ ሁለት ባሕርያት በአንድ መዋሃዳቸውን አንድ ባሕርይ መሆናቸውን የሚገልጹ፥ በአንጻሩ የኬልቄዶኑን ጉባዔ ውሳኔ የሚቃወሙ መጻሕፍትን ጽፈዋል። እነዚህ ዘጠኝ ቅዱሳን ክርስትናን በኢትዮጵያ ውስጥ በማስፋፋታቸው ሳቢያና በአስተማሩትም ትምህርት ባስከተሉት ተጽዕኖ የተነሣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ብቻ አለው የሚለውን አስተምህሮ አጥብቃ ያዘች። የኬልቄዶኑንም ውሳኔ አጥብቃ ነቀፈች።

7ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዘጠኙ ቅዱሳን ስለ ክርስቶስ ባሕርይ ምን አስተማሩ? ለ) የክርስቶስን ባሕርይ ወይም ማንነትን በተመለከተ እነዚህ ዘጠኙ ቅዱሳን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እምነት ላይ ምን ተጽዕኖ አደረጉ?

ዘጠኙ ቅዱሳን የክርስቶስ ሁለት ባሕርያት በአንድ ባሕርይ ውስጥ ተዋሃዱ የሚለውን እምነታቸውን አጥብቀው በመያዝ በዚያ ጸኑ። ይህንንም ትምህርታቸውን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማስፋፋታቸውና ተጽዕኖም በማሳደራቸው፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ልክ እንደ እነርሱ የኬልቄዶንን ጉባዔ አስተምህሮ አጥብቀው መቃወምን መረጡ።

8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ክርስቶስ በአንድ አካል የተዋሃዱ የተለያዩ አምላካዊና ሰብአዊ ባሕርያት አሉት የሚለው የኬልቄዶኑ አስተምህሮ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ሆነው የሚታዩአችሁ ምን ምንድን ናቸው? ለ) ዘጠኙ ቅዱሳን የክርስቶስ ሁለት ባሕርያት በአንድ ባሕርይ ውስጥ ተጣምረዋል ሲሉ የወሰዱት አቋም ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምን ምንድን ናቸው?

የኬልቄዶኑ ጉባዔ አስተምህሮ ጠንካራ ጎን ኢየሱስ እውነተኛ አምላክ እውነተኛ ሰው ነው የሚለው ግልጽ አቋም ነው። ይሁን እንጂ የዚህ አስተምህሮ ጉድለት፥ ክርስቶስ አንዳንድ ጊዜ በሰብአዊነት በሌላ ጊዜ ደግሞ በመለኮታዊነት ይሠራል የሚለውና ክርስቶስን በጣም የሚከፋፍለው አቋሙ ነው። የዘጠኙ ቅዱሳን አስተምህሮ ጥንካሬ የኢየሱስ የባሕርይ ውህደት መጠበቃቸው ነው። ክርስቶስ እግዚአብሔር ብቻ ሆኖ ወይም ሰው ብቻ ሆኖ የሠራበት ጊዜ የለም። ቢሆንም የዘጠኙ ቅዱሳን አገላለጽ የክርስቶስን ሰብአዊነት ከሌሎች ሰዎች ሰብአዊነት የተለየ አድርጎ በማቅረብ ሰዎች የተሳሳተ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ነገ ደግሞ ከኬልቄዶኑ ጉባዔ

አስተምህሮ ጋር አንድነት ያልነበረው የዘጠኙ ቅዱሳን ትምህርት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዴት ሥር ሰድዶ እንደ ተመሠረተ አብረን እንማራለን።

ሁለተኛ ቀን

ትናንትና ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ስለ ኢየሱስ ባሕርያት የነበራትን ግንዛቤ እንዴት እያሳደገች እንደ መጣች ማጥናት የጀመርነውን ትምህርት አጠናቅቀናል። በዚህ ትምህርታችን መጨረሻ ላይ ክርስቶስ «አንድ ባሕርይ» አለው የሚለው አስተምህሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ተለይቶ ተቀባይነትን በማግኘት ብሔራዊ እምነት ለመሆን የቻለበትን ሁኔታ እናጠናለን።

ከዘጠኙ ቅዱሳን በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለአንድ ሺህ ዓመታት ስትስፋፋ ቆይታለች። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በሙሉ አንሥተን ለመወያየት አንችልም። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ በታሪኳ ውስጥ በክርስቶስ ባሕርያት ላይ ያላትን የአስተምህሮዋ አቋም መገንዘብ እንፈልጋለን። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዚህ የአንድ ሺህ ዓመታት ታሪኳ ውስጥ የኢየሱስ ሰብአዊና መለኮታዊ ባሕርያት በተሠገዎ በአንድ ባሕርይ ተዋህደዋል በሚለው አስተምህሮዋ ጸንታ ቆይታለች። ከዚህ የተነሣ በኪልቄዶኑ ጉባዔ ላይ ኢየሱስ መለኮታዊና ሰብአዊ የሆኑ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለውን አስተምህሮ ሲቃወሙት ቆይተዋል። አንዳንዶቹ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የኢየሱስ አካል መለኮታዊና የማይሞት ነው የሚል ትምህርትም ያራምዱ የነበረ ይመስላል። የክርስቶስ ሰብአዊነት ከተቀሩት የሰው ልጆች ሰብአዊነት የተለየ ነው ብለውም ያምናሉ። ይሁን እንጂ ሌሎች ደግሞ ኢየሱስ ያለ ኃጢአት ከመሆኑ በስተቀር ፍጹም አምላክ ፍጹምም ሰው ነው ሲሉ ይቀበላሉ። ሁሉም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አስተማሪዎች የአቡነ ሌዎ አስተምህሮ የሆነውን ማንኛውንም ትምህርትና የኢየሱስን ሁለት ባሕርያት አስተምህሮ በጥብቅ ይቃወሙት ነበር።

9ኛ ጥያቄ፡– ከዘጠኙ ቅዱሳን በኋላ በነበረው አንድ ሺህ ዓመታት ውስጥ፥ ስለ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት የኪልቄዶኑ ጉባዔ ባስተላለፈው ውሳኔ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ያለ አቋም ስትወስድ ቆየች?

የካቶሊካውያን ሚሲዮኖች መምጣት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከ500–1500 ዓ.ም ድረስ፥ ለአንድ ሺህ ዓመታት ኢየሱስ መለኮታዊና ሰብአዊ የሆኑ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለውን የኪልቄዶኑ ጉባዔ ተቀብሎ ያጸደቀውን አስተምህሮ ስትቃወም ቆይታለች። በእነዚህ ዓመታት በአብዛኛው አረቦች ሰሜን አፍሪካንና ዐረቢያን ስለ ያዙ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር የነበራት ግንኙነትም ያነሰ ሆኖ ቆይቷል። ነገር ግን በ1500 እና በ1600 ዓመታት ላይ በቁጥር ጥቂት የሆኑ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ መጡ። እነዚህ ሚሲዮናውያን ይዘውት የነበረው

አስተምህሮ በኬልቄዶኑ ጉባዔ ላይ ተቀባይነትን ያገኘው ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለውን ነበር። ታዲያ የእነዚህ ሚሲዮናውያን መምጣትና ይህን ትምህርት ለማስፋፋት መሞከር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ነውጥን አስከተለ።

የመጀመሪያዎቹ ሚሲዮናውያን አመጣጥ መሐመድ ግራኝ ባስከተለው ወረራ ምክንያት ነበር። ስለሆነም መሐመድ ግራኝ የአፄ ልብነ ድንግልን መንግሥት በወረረ ጊዜ፥ ንጉሡ በጊዜው ወዳጃቸው ከነበረው ከፖርቹጋሉ መንግሥት የጦር እርዳታ ጠየቁ። ከዚያም የፖርቹጋል መንግሥት አራት መቶ ወታደሮችን ከጥቂት የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ጋር አድርጎ ወደ ኢትዮጵያ ላከ። እነዚህ ወታደሮች ከፖርቹጋል ተልከው ኢትዮጵያ በደረሱበት ጊዜ አፄ ልብነ ድንግል ሞተው ቆይተዋቸው። ሆኖም ልጃቸው አፄ ገላውዲዮስ ነግሠው ዙፋኑን ወርሰው ነበር። ከዚያም የፖርቹጋል ሠራዊት ከአፄ ገላውዴዎስ ወታደሮች ጋር በመሆን መሐመድ ግራኝንና ሠራዊቱን ገጥመው በማሸነፍ ግራኝን ገደሉ። ከዚህ በኋላ አብዛኛዎቹ የፖርቱጋል ወታደሮች በኢትዮጵያ ነዋሪ ሆነው ቀሩ። ኋላም ብዙ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን መጡላቸው። ከዚህ በኋላ ሚሲዮናውያኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አማኞች ካቶሊኮች እንዲሆኑ ለማሳመን በጣም ጣሩ። በጊዜው ከመሪዎቹ ጋር ክርክር ከገጠሙባቸው አስተምህሮዎች ውስጥ አንዱ የክርስቶስ ባሕርያት ነበር። ካቶሊካውያኑ ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት ነበሩት፥ እነርሱም አንዱ መለኮታዊ ሌላው ሰብአዊ ሲሆን፥ ሁለቱም በአንድ አካል ውስጥ የተጣመሩ ናቸው የሚለውን አስተምህሮአቸውን ለማሳመን ጣሩ። ኦርቶዶክሳውያኑም ኢየሱስ መለኮታዊና ሰብአዊ ባሕርያት እንዳሉት ቢያምኑም፥ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለውን አስተምህሮ አልተቀበሉትም። ይህ አስተምህሮ ኢየሱስን ይከፋፍለዋል አሉ። በመጨረሻም፥ ክርክሩ በአፄ ገላውዴዎስና በአንደኛው የካቶሊክ ካህን መካከል ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ። ከዚያም አፄ ገላውዴዎስ ክርክሩን አሸነፉ። በመሆኑም ከኢትዮጵያውያን መካከል ካቶሊካዊነትን እምነት የተቀበሉ ጥቂቶች ነበሩ።

10ኛ ጥያቄ፡– የመጀመሪያዎቹ የፖርቹጋል ካቶሊክ ሚሲዮናውያን በምን ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ መጡ?

11ኛ ጥያቄ፡– የክርስቶስን ባሕርያት በሚመለከት በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በፖርቹጋል ካቶሊካዊያን ሚሲዮናውያን መካከል የነበረው ልዩነት ምን ነበር?

12ኛ ጥያቄ፡– ካቶሊካውያን ሚሲዮናውያኑ ኢትዮጵያውያኑ የካቶሊክን እምነት እንዲቀበሉ ጥረት ባደረጉበት ጊዜ ኦርቶዶክሳውያኑ ምን አቋም አሳዩ?

እንደሚታወሰው የመጀመሪያዎቹ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ግራኝ መሐመድን ለመዋጋት ከመጡት ወታደሮች ጋር ነበር። እነዚህ ሚሲዮናውያንም ኦርቶዶክሳውያኑን አማኒያን ካቶሊካዊውን እምነት እንዲቀበሉ ብዙ ጥረት አድርገዋል። ነገር ግን በሁለቱ መካከል ትልቅ ልዩነት ነበር። ያም ካቶሊካውያን ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት አሉት ሲሉ፥ ኦርቶዶክሳውያን ደግሞ አንድ ባሕርይ ብቻ አለው ይሉ ነበር። አብዛኛዎቹ

ካቶሊካውያን ሚሲዮናውያን ሕይወታቸውን በሙሉ እዚሁ ሲያገለግሉ ቆይተው እዚሁ በኢትዮጵያ ውስጥ አርፈዋል። ጠንካራው ጥረታቸው ብዙ ፍሬም ባያፈራ፥ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ካቶሊኮች ሊሆኑ ችለዋል።

ይሁን እንጂ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጥረትዋን እንደገና አድሳ ብትቀጥል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን አሳምና ወደ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እንደምታመጣ በመተማመን ትምህርቱን ቀጠለች። ከዚህ የተነሣ ከፖርቹጋል ተጨማሪ ሚሲዮናውያንን ወደ ኢትዮጵያ መላክ ቀጠለች። ከአፄ ገላውዴዎስ ጋር ከተካሄደው ክርክር ከሃምሳ ዓመት ገደማ በኋላ፥ ፒያዝ የተባለ ሚሲዮናዊ ወደ ኢትዮጵያ መጣ። ይህ ፒያዝ የተባለ ሰው ትሑት ሰው ከመሆኑም በላይ፥ ትምህርት ቤት ከፍቶ እምነቱን አድምጠው ለሚቀበሉት የካቶሊካውያንን አስተምህሮ መስበክ ጀመረ። በመጨረሻውም ላይ አፄ ዘድንግል ስለ ፒያዝ ትምህርት ሰምተው አድናቆት ስላደረባቸው ወደ ቤተ መንግሥታቸው አስጠሩት። ፒያዝም ሲናገር በሰሙት ጊዜ፥ በትምህርቱ ተመስጠው የክርስቶስን የሁለት ባሕርያት አስተምህሮ በመቀበል ካቶሊክ ሆኑ። ይሁን እንጂ ይህ በመላው መንግሥታቸው ውስጥ ዓመፅን ቀስቅሶ እርሳቸውም ወዲያው ተገደሉ። ከዘድንግል ቀጥለው የነገሡት ሱስንዮስ ነበሩ። አፄ ሱስንዮስም ቢሆኑ ለካቶሊክ አስተምህሮ አድናቆትና ፍላጎት ነበራቸው። ሆኖም ከዘድንግል በበለጠ ጥንቃቄ አደረጉ። ለብዙ ዓመታትም ከቆዩ በኋላ ከታላላቅ የኢትዮጵያ ልዑላን ዘንድ ድጋፍ አገኙ። ከዚያም ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለውን የካቶሊክ እምነት የሚቀበሉ መሆናቸውን በይፋ አሳወቁ። አሁንም እንደገና ዓመፅ ተቀሰቀሰ። ስለዚህ አፄ ሱስንዮስ የካቶሊክን ሃይማኖት በኢትዮጵያ ለማቆየት ከገዛ ሕዝባቸው ጋር መዋጋት ነበረባቸው።

በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ፒየዝ ሞቶ ነበር። ስለዚህ ሜንዴዝ የተባለ ሚሲዮናዊ ዱካውን ተከትሎ መሥራት ጀመረ። ሜንዴዝ ከፒያዝ የተለየ ኃይለኛ ቁጡ ሰው ነበር። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን የካቶሊክን እምነት ይቀበሉ ተብሎ ሳይወሰን አልፎ ተርፎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በምትከተለው መንገድ እንደገና መጠመቅ አለባቸው አለ። በቤተ ክርስቲያናቸውም ውስጥ የግዕዙን ቋንቋ ትተው በላቲን መጠቀም አለባቸው፥ ካህናቱም ቢሆኑ በካቶሊክ ሥርዓትና እምነት ሊቀድሱ ይገባል አለ። ታዲያ ይህ የሜንዴዝ አሳብ ኢትዮጵያውያኑን ክፋኛ አናደዳቸው። ይህ የሜንዴዝ አባባል ኦርቶዶክሳውያን የቆዩበትን የአምልኮ ሥርዓትና ባሕል ዝቅ ያደረገና ለመጪው እምነት የበለጠ ስፍራ የሰጠ ሆኖ ተሰማቸው። ከዚህ ከሜንዴዝ ጠንካራ አቋምና አስተሳሰብ የተነሣ የካቶሊክ እምነት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው ብዙ ኢትዮጵያውያን አረጋገጡ። ከዚያም በአፄ ሱስንዮስ ላይ የተቀሰቀሰው ዓመፅ የበለጠ ጠነከረ።

በኋላም አፄ ሱስንዮስ አገራቸው እንድትከፋፈል ምክንያት በመሆናቸው ተስፋ ቆርጠው በ1632 ዓ.ም ዙፋናቸውን ለልጃቸው ለፋሲለደስ ለቀቁለት። አፄ ሱስንዮስም ይህ ከሆነ ከአንድ ዓመት በኋላ ሞቱ። አፄ ፋሲለደስ የአደረጉት የመጀመሪያው ተግባር ካቶሊክ ሚሲዮናውያንን ከአገር ማባረርና

አገሪቱን ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መመለስ ነበር። ሚሲዮናውያኑንም ከአገር በሚያባርሩበት ጊዜ አፄ ፋሲለደስ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች የሁለት ባሕርያትን ትምህርት እንደማይቀበሉና ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹምም ሰው መሆኑን እንደሚያምኑ በመንገር ነበር። ለሕዝቡም አክለው ሲናገሩ፥ «አሁን ኢትዮጵያ ከምዕራባውያን ጅቦች አምልጣለች» ብለዋል።

የካቶሊክ ሚሲዮናውያን መምጣትና የአፄ ሱስንዮስ መንግሥት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ አንድ ባሕርይ አለው የሚለውን እምነቷን በበለጠ እንድታጠናክር ረዳት። በአንጻሩ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለውን አስተምህሮ እንደ ባዕድ– አመጣሽ አስተምህሮ በመቁጠር፥ ይህን መሰል አስተምህሮ በእውነተኞች ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት በነቀፋ ወሰዱት። በቀጣዮቹ ሁለት መቶ ዓመታት ውስጥ የውጭ አገር ተወላጅ የሆነ ሰው ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ቁጥር እምነቱ በኢየሱስ ሁለት ወይም አንድ ባሕርይ እንደሆነ ይጠየቅ ነበር። እኔ የማምነው በሁለት ባሕርያት ነው ካለ ተቀባይነት አያገኝም። የአንድ ባሕርይ አማኝ ሆኖ ከተገኘ ግን ተቀባይነትን ያገኛል።

13ኛ ጥያቄ፡– ዘድንግልንና ሱስንዮስን የካቶሊክን እምነት እንዲቀበሉ ፒያዝ እንዴት ሊያግባባ ቻለ?

14ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ሜንዴዝ ከፒያዝ እንዴት ይለያል? ለ) ሜንዴዝ በተለይ የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች የሚያስቀይም ምን ተግባር ፈጸመ?

15ኛ ጥያቄ፡– የሱስንዮስ ወደ ካቶሊክነት መግባት ውጤቱ ምን ሆነ?

16ኛ ጥያቄ፡– ንጉሥ ፋሲለደስ ወደ ዙፋን ከመጡ በኋላ ምን አደረጉ?

17ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ካቶሊኮች ከመጡ በኋላ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት ብለው ሲያስተምሩ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተቃውሞዋን እንዴት ገለጸች? ለ) ሱስንዮስ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸው ዝና እንዴት ያለ ነው?

18ኛ ጥያቄ፡– ዛሬ የቤተ ክርስቲያናቸውን ታሪክ ደህና አድርገው የሚያውቁ የተማሩ ኦርቶዶክስ ኢትዮጵያውያን ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት ለሚላቸው ሰው መልሳቸው ምን ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ዘዴ በታከለበትና በሚሰብ የትምህርት አቀራረብ ፒያዝ አፄ ዘድንግልንና አፄ ሱስንዮስን ክርስቶስ መለኮታዊና፥ ሰብአዊ ባሕርያት እንዳሉት በማሳመን የካቶሊክን እምነት እንዲቀበሉ አድርጓል። በአንጻሩ ግን ሜንዴዝ በነበረው ኃይለኛ ባሕርይና ለሕዝቡ እንግዳ የሆነ ሥርዓትን ለማስተዋወቅ በመጣሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክሶችን አስቀይሟል። እንዲሁም አፄ ሱስንዮስ የካቶሊክን አምነት ያመቀበላቸው ምክንያት ጦርነት በአገሪቱ ውስጥ ከመነሣቱም ሌላ ኢትዮጵያም እንድትከፋፈል አድርጓል። አፄ ፋሲለደስ ከነገሡ በኋላ፥ ካቶሊኮችን አስወጥተው በፈንታው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ወደ ስፍራው እንዲመለስ አድርገዋል። የዚህ ሁሉ ውጤት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለውን አስተምህሮ እንደ ባዕድ እምነት እንድታየውና እንድትቃወመው

አድርጓል። ስለሆነም በኢየሱስ ሁለቱ ባሕርያት የሚያምኑ ምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት እንደሚያጠፉ ጅቦች ተቆጥረዋል። ዛሬም እንኳ አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን ድርጊታቸው አገሪቱን አሳልፎ ስለ ሰጠና ስለ ከፋፈለ ስለ አፄ ሱስንዮስ መልካም አመለካከት የላቸውም። ዛሬም ቢሆን ስለ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት የሚያስተምሩ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች እንደ ሌላው ሱስንዮስ ተቆጥረው ክስ ሊመሠረትባቸው ይችላል። ምክንያቱም እንዲህ ያሉት ክርስቲያኖች እውነተኛ ክርስቲያኖች ተብለው ተቀባይነት ስለማያገኙ ነው። ብዙዎች የተማሩ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች፥ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን በአገሪቱ ውስጥ ቀስቅሰውት የነበረውን ችግርና መለያየት ስለሚያስቡ ስለ ሁለት ባሕርያት የሚናገር ወይም የሚያስተምር ሰው ሲሰሙ ትዝ የሚላቸው የያኔው ተግባር ነው።

በተዋሕዶ፥ በቅባትና በሥ ስት ልደት መካከል የነበረ ክርክር

ከአፄ ሱስንዮስ ግዛት በኋላ በነበሩት ዓመታት፥ የክርስቶስ መቀባትን በተመለከተ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በተለያየ አስተሳሰብ ሥር ተከፋፈለች። በዚህ ነጥብ ላይ በመጀመሪያ የተነሡት ሁለት ቡድኖች ተዋሕዶና ቅባቶች ነበሩ። ተዋሕዶዎች ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት ሰብአዊና መለኮታዊው ባሕርይ በአንድ አካል ውስጥ ሲጣመሩ በአዳም ውድቀት ምክንያት ጠፍቶ የነበረውን ራሱን ቀብቷል፤ ይህ ቅባት ወደ ክርስቶስ ሰብአዊነት በመመለስ ፍጹም ሰው አድርጎታል ብለው ያምናሉ። ቅባቶች ደግሞ፥ ክርስቶስ በአባቱ ተቀብቶአል፥ ይህ ቅባትም ሁለቱ ባሕርያት በአንድ ባሕርይ እንዲጣመር አድርጓል ይላሉ። እንደዚሁም ሁለቱ ባሕርያት ሲጣመሩ፥ የክርስቶስ መለኮታዊ ባሕርይ ሰብአዊውን ባሕርይ ይውጠዋል የሚል ትምህርትም ያስፋፉ ይመስላል። ዘግየት ብሎ ሌሎቹ በሦስተኛ ደረጃ የሚጠቀሱት የሦስት ልደት አማኞች ተነሡ። ይህ ቡድን ደግሞ ክርስቶስ ሦስት ጊዜ ተወልዱል የሚሉ ነበሩ። ይኸውም ለዘላለም ከእግዚአብሔር አብ፥ በሥጋ ደግሞ ከድንግል ማርያም ማኅፀንና በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀበት ጊዜ ደግሞ እንደ ጸጋ ልጅ ተወልዱል ብለው ያምናሉ።

ወደ ኋላ ላይ በሚመጣው ትምህርት ስለ እነዚህ አሳቦች በዝርዝር እናጠናለን። ለዛሬው በዚህ ትምህርት ላይ ለመመልከት የምንፈልገው *እያንዳንዱ ቡድን በየፊናው ትምህርታችን ክርስቶስ አንድ ባሕርይ እንደ ነበረውና እውነተኛ አምላክም እውነተኛ ሰውም መሆኑን ያስተጋባል በማለት የየግል አቋሙን እንዴት እንደሚከላከል ነው።* ተዋሕዶዎች ስለ ቅባቶች ሲናገሩ፥ ክርስቶስ በአብ የተቀባ በማለት የክርስቶስን ክብር ዝቅ አድርገዋል፤ ይህም የሚያሳየው፥ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር አይደለም ማለታቸው ነው ሲሉ ይተቻቸዋል። ቅባቶች ደግሞ በበኩላቸው ተዋሕዶዎችን፥ ተዋሕዶዎች ክርስቶስ በተቀባ ጊዜ ቅባቱ ሰብአዊ ባሕርይውን አንጽቶታል ብለው ስለሚያምኑ፥ ባለ ሁለት ባሕርያት ያደርጉታል ባይ ናቸው። ታዲያ እነዚህ ሁለት ቡድኖች በየፊናቸው ደግሞ የሦስት ልደት አማኞችን በብርቱ ይቃወማሉ። የሚያቀርቡትም ምክንያት በእውነተኛ ውሕደት አያምኑም የሚል ነው። በመጨረሻውም የተዋሕዶ

እምነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይፋዊ አስተምህሮ ለ.ሆን ችሏል።

19ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ስለ ክርስቶስ መቀባት ተዋሕዶዎች ምን ያምኑ ነበር? ለአቋማቸው የክርስቶስን እውነተኛ ሰብአዊነትና አምላክነት ያስጠብቃል ብለው ያመኑት ለምን ነበር?

20ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ቅባቶች ስለ ክርስቶስ መቀባት የነበራቸው እምነት ምንድን ነው? ለ) ቅባቶች አቋማችን ከማንም ይበልጥ የክርስቶስን አሃዳዊ ባሕርይ ያስጠብቃል ብለው ያመኑት ለምን ነበር?

21ኛ ጥያቄ፡– ተዋሕዶዎችና ቅባቶች በምን ምክንያት ሦስት ልደት አማኞችን አወገዙ?

ስለ ክርስቶስ መቀባት ይካሄድ የነበረው ክርክር ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባው አንደኛው ምክንያት፥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ የተለያዩ ቡድኖች ስለ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ምን ያህል ጠንካራ አቋም እንደነበራቸው ስለሚያመለክት ነው። ተዋሕዶዎች ክርስቶስ በአብ ተቀባ የሚለውን አስተምህሮ አይቀበሉም። ምክንያቱም ይህን እምነት የክርስቶስን እውነተኛ አምላክነት የሚክድ አድርገው ስለሚቆጥሩት ነው። ይህም ክርስቶስ መለኮታዊና ሰብአዊ የሚሆን አንድ ባሕርይ የለውም እንደ ማለት ስለሆነ ነው። ቅባቶች ደግሞ ተዋሕዶዎች፥ የክርስቶስ መቀባት ሰብአዊ ባሕርይውን መልሶለታል የሚለውን አቋም አይቀበሉም። ምክንያቱም፥ ይህ አቋም ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለውን ስለሚያመለክት ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁለት ቡድኖች በበኩላቸው የሦስት ልደት አማኞችን ያወግዛሉ። ምክንያታቸው ባለ ሦስት ልደቶቹ ክርስቶስ የሁለት ባሕርያት ውሕደት መሆኑን አይቀበሉም የሚል ነው። ይህ የእርስ በርስ የአስተምህሮ ክርክርና አለመግባባት የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ለሦስት መቶ ዓመታት ከፋፍሏት ቆይቷል። ስለ ክርስቶስ መቀባት አስተምህሮ በሌላ ትምህርታችን ላይ እናጠናለን። ሆኖም የክርስቶስ ሁለት ባሕርያት በአንድ መለኮታዊና ሰብአዊ ባሕርይ ውስጥ ፍጹም መዋሐዳቸውን የማመኑ ጉዳይ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በጣም ጠቃሚ እንደሆነ በእነዚህ ቡድኖች መካከል የተካሄደው ክርክር ያስገነዝባል።

ሦስተኛ ቀን

በዛሬው ትምህርታችን ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ተሠገዎ ስላላት ምሥጢረ እምነት አስተምህሮ እናጠናለን። እናንተም ብትሆኑ አብዛኛዎቹ የኦርቶዶክስ ምእመን ስለ ክርስቶስ ባሕርያት ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ በተለይ ከሚቀርቡዋችሁ ከአንዳንዶቹ ጋር ልትወያዩ ትችላላችሁ። የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች የየትኛውም ቤተ ክርስቲያን አባሎች ይሁኑ የሚናገሩትን ነገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አማንያን በምን ዓይነት መንገድ እንደሚገነዘቡት ማወቅ አለባቸው። ስለ ተሠገዎ ምሥጢር በምናስተምርበት ጊዜ፥ የምናቀርበው ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ አሳብ በመልእክቱ ውስጥ የሚያስተላልፍ ሊሆን

ይገባል። አንዳንድ ጊዜ ምዕራባውያን ስለ ክርስቶስ ፍጹም አምላካዊነትና ፍጹም ሰብአዊነት ባሕርይ ለመግለጽ የሚጠቀሙባቸው ቃላት ወደ አማርኛ ቋንቋ በሚተረጉሙበት ጊዜ ትክክለኛውን መልእክት ይዘው ለኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይደርሱዋቸው ይችሉ ይሆናል። ለመሆኑ ዛሬ ኦርቶዶክሳውያን ስለ ተሠገዎ ምሥጢር እምነታቸው ምንድን ነው?

ቤተ ክርስቲያኒቱ ስለ ተሠገዎ ምሥጢር ያላትን የእምነት አቋም «በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት» ብላ ሐምሌ 1988 ዓ.ም ባሳተመችው መጽሐፍ በገጽ 27 ላይ እንዲህ ብላለች፡-

> «መለኮት ከሥጋ ሥጋ ከመለኮት ጋር ያለ መለወጥ፥ ያለ መቀላቀል፥ ያለ መለያየትና ያለ መከፈል በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ። ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ሰውም ከሆነ በኋላ አንድ ወልድ አንድ ክርስቶስ ነው። (ቄርሎስ ሃይ. አበ. ምዕ. 78 ክፍ. 48 ቁ. 9-18)። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዝእንዚናዙም) በተዋሕዶ ሰው የሆነ አምላክ አምላክም የሆነ ሰው እርሱ ብቻ ነው ብሎአል። ሀ. አ. ምዕ. 61 ክፍል 4 ቁጥር 23. ሥጋም በተዋሕዶተ ቃል እንደ ከበረ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ‹በሥጋ የነበረ እንዴት በተዋሕዶተ ቃል ጠፋ። የቃል ክብር ለሥጋ በተዋሕዶ ገንዘቡ ሆነ› ብሎአል። (ዮሐ. አፈ. ሃይ/አ/ምዕ. 66. ክፍ. 9. ቁጥ. 18-19)።
>
> ከተወለደም በኋላ ከኃጢአት በቀር ሰው የሚሠራውን ሥራ ሁሉ እየሠራ አደገ በዚህም ዓለም 33 ዓመት ከሦስት ወር ኖሮና አስተምሮ ስለ እኛ የሞት ፍርድን ተቀበለ፤ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ፤ በሞቱም ሞትን አጠፋ፤ ዓለምን አዳነ፤ ሥስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሮ ተነሣ» ይላል።

በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ተሠገዎ ምሥጢር እምነትዋ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈው እንዲህ ይላል፡-

> «ክርስቶስ ቃል የሆነው የእግዚአብሔር አንድ ባሕርይ ነው። ከባሕርያቱ ውሕደት በኋላ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አለው ብሎ መናገር አይቻልም። ባሕርያቱ በተሠገዎ አንድ ባሕርይ ሆነዋል፥ ስለዚህ ባሕርያቱ ያለመለወጥ፥ ያለመቀላቀል፥ ያለ መለያየትና ያለ መከፋፈል በተዋሕዶ አንድ አካል፥ አንድ ባሕርይ ሆነዋል። ባሕርይ ከባሕርይ ሳይቀላቀል መለኮት ቃል ከሥጋ፥ ሥጋ ከመለኮት ቃል በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ... እርሱም በአምላክነቱ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል ነው። ከእኛም ጋር አንድ ሆነ አንድነቱም ከባሕርይው ውሕደት ነው። ቃል ሥጋ ሆነ የሚለው የተፈጸመው በድንግል ማርያም ማኅፀን ውስጥ በመፀነሱ ነው»።

ከዚህ በላይ ከተመለከትናቸው ነጥቦች ብዙ ሁኔታዎች ግልጽ ሆነዋል፡-

1) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፥ ስለ ክርስቶስ አምላክነትና ሰብአዊነት ታስተምራለች። እርሱም በአምላክነቱ ከእግዚአብሔር አብ ጋር

አንድ በሰብአዊነቱም ከኃጢአት በስተቀር ከእኛ ጋር አንድ ነው። ከኃጢአት በቀር ሰው የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ሠርቷል።

2) የክርስቶስን ባሕርይ አሃዳዊነት ለመጠበቅ ቤተ ክርስቲያኒቱ የክርስቶስ አምላክነትና ሰብአዊነት በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ሆኖአል። ክርስቶስ ከተሠገዎ በኋላ ሁለት ባሕርያት አለው የሚለውን አስተምህሮ አጥብቀው ይቃወማሉ። ወልድን በተዋሕዶ አሃዳዊነት ይሠራ ነበር ስለሚሉ ሰው በሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ውሕደት አጥብቀው ያምናሉ።

3) የአምላክነትና የሰብአዊነት ውሕደት፥ የክርስቶስን ሰብአዊነት ከሌሎች ሰዎች ሰብአዊነት ይለይ አይለይ እንደሆነ አስተምህሮዋ ላይ ግራ መጋባት ይታያል። በአንድ በኩል ቤተ ክርስቲያኒቱ «ያለመቀላቀል፥ ያለመከፋፈል» ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ ትላለች። በሌላ በኩል ደግሞ «በሥጋ የነበረ እንዴት በተዋሕዶተ ቃል ጠፋ፥ የቃል ክብር ለሥጋ በተዋሕዶ ገንዘቡ ሆነ» እንደዚሁም፥ «ቃል የሆነው የመለኮት ባሕርይ ከሥጋ፥ ሥጋ ቃል ከሆነው ከመለኮት ባሕርይ ጋር አንድ ነው።» በማለት ታስተምራለች። እንዲህ ማለት የክርስቶስ አካል ሌሎች ሰዎች ያለባቸው ድክመቶች የሉትም፥ እንደዚሁም መለኮታዊው ባሕርይ ሥጋዊውን ባሕርይ ሲነካው ሥጋዊው ባሕርይ ተለውጦአል የሚል ይመስላል። ኢየሱስ ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ አይደለም፥ «በተዋሕዶ ሰው የሆነ አምላክ አምላክም የሆነ ሰው እርሱ ብቻ ነው።» ይህ አገላለጽ የክርስቶስ ሰብአዊነት መለኮታዊ ሰብአዊነት ነበር የሚል ይመስላል። ሌሎች የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ደራሲያን፥ የክርስቶስ አምላካዊና ሰብአዊ ባሕርያት በአንድ ባሕርይ እንደ ተዋሐዱና ክርስቶስም አንድም በአምላካዊነት አልያም በሰብአዊነት ባሕርይው እንደሚሠራ አድርገው ትኩረት በመስጠት ጽፈዋል። ብዙዎቹም ክርስቶስ በሥጋው ብቻ አልሞተም፥ በመለኮታዊና በሰብአዊ አምላክነት ሞምር ነው ሲሉ አበክረው ይገልጻሉ።

22ኛ ጥያቄ፡– የአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ባሕርይ በምታካሂደው ግልጽ ትምህርት አጽንኦት የምትሰጣቸው ሦስት ነጥቦች ምንድን ናቸው?

23ኛ ጥያቄ፡– ሀ) የኢትዮጵያ አርቶዶክስ አስተምህሮ ከኪልቄዶኑ ጉባዔ አስተምህሮ እንዴት ይመሳሰላል? ለ) የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከኪልቄዶኑ ጉባዔ አስተምህሮ ጋር በምን ይለያል?

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በምትሰጠው ግልጽ ትምህርት በሚከተሉት ነጥቦች አጽንኦት ታደርጋለች፡–

1) ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውም አምላክም መሆኑን፥

2) የክርስቶስ መለኮታዊነትና ሰብአዊነት በአንድ ባሕርይ እንደ ተዋሐዱ፥ በተናጠል እንደ አምላክ ወይም እንደ ሰው እንዳልሠራና ነገር ግን ሁልጊዜም የተዋሐደ ሰበ – አምላክ ሆኖ እንደ ሠራ፥

3) የክርስቶስ መለኮታዊነትና ሰብአዊነት ፍጹም ከመዋሐዱ የተነሣ በሆነ መንገድ መለኮቱ ሰብአዊ ክፍሉን በመንካቱ ከሌሎች የተለየ ዓይነት መለኮታዊ– ሰብአዊነት አድርጎታል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልክ እንደ ኬልቄዶኑ ጉባዔ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክም ሰውም መሆኑን ታስተምራለች። እንደዚሁም ልክ እንደ ኬልቄዶኑ ጉባዔ የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ ከመለኮታዊው ባሕርይ ጋር አይቀላቀልም በማለት በአንዳንድ ስፍራ ታስተምራለች። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያኒቱ፥ የክርስቶስ ሰብአዊና መለኮታዊ ባሕርይ በአንድ ተዋሕደዋል በማለት በምትሰጠው ትምህርት ከኬልቄዶኑ ጉባዔ ትለያለች። ደግሞ ኢየሱስ በሰብአዊ ባሕርይው ወይም በመለኮታዊው ባሕርይው በተናጠል ምንም ነገር አላከናወነም ከማለቷም ሌላ በሞተም ጊዜ በተዋሐደ አንድ ሰበ–አምላካዊ ባሕርይ ነው የሞተው ትላለች። በመጨረሻም አንዳንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የክርስቶስ ሰብአዊነት መለኮታዊ ሰብአዊነት ስለሆነ የእርሱ ሰብአዊነት እንደ ተቀረው የሰው ልጅ ሰብአዊነት እንዳልሆነ ተደርጎ ይቀርባል።

24ኛ ጥያቄ፡– ባሕርይና ጠባይ ስለሚሉት ቃላት አስቡ። አካል ስለሚለውም ቃል አስቡ። ባሕርይ ወይም ጠባይ ሳይኖር አካል ሊኖር ይችላል? በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በምዕራባውያን መካከል ያለው የቋንቋ ልዩነት በምሥጢረ ተሠገዎ ግንዛቤአቸው እንዴት ያለ ተጽዕኖ ሊያሳድር ቻለ?

በርካታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ደራሲያን፥ የኬልቄዶኑ ጉባዔ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያትና አንድ አካል እንዳለው አድርገው የተሳሳተ ትምህርት በማቅረባቸው የእነርሱ የሃይማኖት መግለጫ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነት የለውም ይላሉ። ለምሳሌ ያህል፥ ብርሃኑ ነበና «አምደ ሃይማኖት» በሚለው መጽሐፉ ላይ፥ «አካል ያለ ባሕርይ፥ ወይም ባሕርይ ያለ አካል ዋጋ የለውም። ሁለት ባሕርያት ካሉ፥ ሁለት አካላት ሊኖሩ ይገባል» ብሏል።

የኬልቄዶኑን ጉባዔ ሃሳብ በአማርኛ ቋንቋ አገላለጽ ለመገንዘብ ሙከራ በሚደረግበት ጊዜ ግልጽ የሆነውን አሳብ ማግኘት የሚያስቸግር ይመስላል። በኬልቄዶኑ ጉባዔ ላይ የተገኙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሃይማኖት መግለጫውን በጻፉበት ጊዜ፥ ሁለት ባሕርይ በአንድ አካል በማለት ሊገልጹት የፈለጉት አሳብ የተካተተ ኢየሱስ በአንድ አካል ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን ለማሳየት ነበር። ይህን የኬልቄዶኑን የሃይማኖት መግለጫ አንድ ሰው በአማርኛ ቋንቋ ወስዶ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አለው ብሎ ቢያስተምርህ፥ ብዙ ጊዜ የተምታታ አሳብ መስሎ ይታያል። እንደዚሁም አንድ ሰው ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አለው ብሎ ቢያስተምር፥ ይህ ሰው በሚሰጠው ትምህርት አንዳንድ ሰዎች ክርስቶስ በራሱ የተከፋፈለ ነው የሚል የተዛባ ግንዛቤ ሊወስዱ ይችላሉ።

በመሠረቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ብዙ ምእመናን ስለ ክርስቶስ ማንነት የተለያየ አስተሳሰብ አላቸው። ይህን በክርስቶስ ምሥጢረ ተሠገዎ ላይ የጀመርነውን ትምህርት ከማጠቃለላችን

በፊት ለየት ያለ የተግባር ትምህርት ታከናውናላችሁ። ስለዚህ መጻሕፍቶቻችሁን ታስቀምጡና ለምታውቁዋቸው የኦርቶዶክስ ምእመናን ቃለ መጠይቅ ታደርጋላችሁ። ቃለ መጠይቅ እንድታደርጉላቸው ፈቃደኛ የሆኑትን ሦስት ሰዎች ምረጡ። ቃለ መጠይቅ እንድታደርጉላቸውም ፈቃደኞች ይሆኑ ዘንድ ስለ ሃይማኖት በመማር ላይ መሆናችሁን ግለጹላቸው። ከዚያም የእናንተ ሥራ እነዚህ ሦስት ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ስላላቸው ግንዛቤ መጠየቅ ይሆናል። ቃለ መጠየቁን የምታቀርቡላቸው ሦስት ሰዎች አንዱ ወንድ፥ አንዲት ሴትና አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ (ማለትም ቄስ፥ ዲያቆን፥ ደብተራ፥ ወይም መነኩሴ) ሊሆን ይችላል። ምናልባት የሚጠየቅ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ባታገኙ፥ አንድ ስለ ሃይማኖቱ ጠለቅ ያለ ትምህርት ያለውን የኦርቶዶክስ ሰው ልትጠይቁ ትችላላችሁ። ቃለ መጠይቁን ስታደርጉ፥ መልሱን ቃል በቃል አትጻፉት፥ አሳቡን ደህና አድርጋችሁ በማስታወሻ ያዙት።

25ኛ ጥያቄ፡– ለቃለ መጠይቆቻችሁ የምትጠቀሙባቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡–

1) በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነበር?

2) ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ስለነበረው ባሕርይ ዘርዝር።

3) ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ አምላክ ነበር? ሰው ነበር? ወይስ ሁለቱንም ማለትም እግዚአብሔርም ሰውም? (መላሾቹ፥ እርሱ እግዚአብሔርም ሰውም ነበር ካሉ፥ ይህን ጥያቄ ቀጥላችሁ አቅርቡ)፡– ሰብአዊውና አምላካዊው ባሕርያቱ የተጣመሩበትን ሁኔታ ግለጽ።

4) አሁን ኢየሱስ ወደ ሰማይ አርጓል። ታዲያ እርሱ አምላክ ነው? ሰው ነው? ወይስ አምላክም ሰውም ነው?

5) አንድ ሰው ወደ አንተ ዘንድ ቢመጣና ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት አሉት፥ እነርሱም መለኮታዊና ሰብአዊ ባሕርያት ናቸው ቢል፥ መልስህ ምን ይሆን?

6) ኢየሱስ አማላጅ መሆኑን ታምናለህ?

7) ስለ ኢየሱስ ሕይወት ዋና ቁም ነገር ነው የምትለው ምንድን ነው?)

የዛሬ ተግባራችሁ በሚቀራችሁ ጊዜ እነዚህን ቃለ መጠይቆች ማቅረብ ነው። ጠይቃችሁ የምታገኙዋቸውንም መልሶች በማስታወሻ ደብተሮቻችሁ ውስጥ ጻፉዋቸው።

አራተኛ ቀን

በዛሬው ትምህርታችን ሁለት ነገሮችን እናደርጋለን። የመጀመሪያው ተግባራችን፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ባሕርይና አካል እምነትዋ በእርግጥ ፃ፯ እንደሆነ መወያየት ነው። ሁለተኛው፥ ስለ ምሥጢረ ተሠገዎ ስናጠናው የነበርነውን ትምህርት ማጠቃለል ይሆናል። ኢየሱስ እንዴት በአንድ ጊዜ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ሊሆን ይችላል? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ እንጀምራለን። ከዚያ በፊት ግን፥ ትናንት የተሰጣችሁን ቃለ መጠይቅ ካልጨረሳችሁ ወደ ዛሬ ሥራ ከማምራታችን በፊት ጨርሱ።

ክፍል አንድ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ስለ ክርስቶስ ባሕርይና አካል ያላቸው እምነት

ትናንትና ለእናንተ የሰጠኋችሁን ጥያቄዎች እኔ ራሴ ለብዙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አማኞች አቅርቤ ጠይቄአቸው ነበር። በዚህ በአዲስ አበባ ከተማ በአንድ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በሚገኙ በሁለት ቀበሌዎች ውስጥ ነዋሪ የሆኑ አሥራ ሦስት የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችን ማለትም፥ (አምስት ቀሳውስትን፥ አራት ዲያቆናትን፥ ሁለት መነኮሳትንና ሁለት ደብተራዎችን) እንደዚሁም አሥራ ዘጠኝ ወንድ ምእመናንንና አሥራ ዘጠኝ ሴት ምእመናትን ጠይቄአለሁ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረ ጊዜ እግዚአብሔርም ሰውም እንደነበረ የሚያምኑ ናቸው። ብዙዎች እርሱ ሥጋ የለበሰ አምላክ እና አምላክነቱና ሰብአዊነቱ በተዋሕዶ የከበረ ነው ብለዋል። ሌሎች ደግሞ አሳባቸውን ሲሰጡ፥ እነርሱ እንደሚያምኑት ከሆነ፥ የኢየሱስ ሥጋ መልበስ ከተቀሩት የሰው ልጆች የተለየ መሆኑን ተናግረዋል። ጥቂቶቹ እንዳሉት ክርስቶስ የሰው አምሳል ቢሆንም ፍጹም ሰው አይደለም ብለዋል። ስለ ክርስቶስ ሰብአዊነት በተጠየቁ ጊዜ አንዲት ሴት፥ «ይህ አፈኛ ነገር ብቻ ነው» ብለዋል። አንድ ቄስ ደግሞ ሲናገሩ፥ ክርስቶስ የአኗኗርን ሁኔታ ሊያስተምረን የሰውን አምሳል ወሰደ። ስለዚህ እርሱ እውነተኛ አምላክ እንጂ እውነተኛ ሰው አይደለም ሲሉ ተናግረዋል። እንደዚሁም አንደኛው ሰው፥ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ሊያስተምር ሰው ሆነ፥ ነገር ግን ሊቆፍር አልመጣም፥ ቤት ሊሠራም አልመጣም፥ እርሱ እንደ እኛ ሰብአዊ ባሕርይ ያለውም፥ እርሱ ከእኛ በላይ የሆነ ንጉሣችን ነው ሲል የሚያምነውን በጠራ ሁኔታ ገልጾአል። ይህ ሰው ክርስቶስ በሰው ቢመሰልም፥ ሰዎች የሚፈጽሙትን ተራ ተግባራት ለማድረግ አልመጣም በማለት አብራርቷል።

ቃለ መጠይቅ ከአቀረብሁላቸው ሰዎች አብዛኛዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ብቻ እንዳለው አጥብቀው ያምናሉ። አንዳንዶቹም የእርሱ አንድ ባሕርይ፥ መለኮታዊ ባሕርይ ነው፥ ስለዚህ ኢየሱስ አምላክ ብቻ ነው ብለዋል። ሌሎች ደግሞ ትኩረት ሰጥተው የተናገሩት፥ ክርስቶስ ራሱ በራሱ ስለማይከፋፈል፥ አንድ ባሕርይ ብቻ ነው በማለት ነበር። በመጨረሻውም ላይ በርከት ያሉ ካህናት የኢየሱስ አንድ ባሕርይ መሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ስለሆነ እነርሱም በዚህ አስተምህሮ የሚያምኑ መሆናቸውን በአጽንኦት ተናግረዋል። ሁለት ዲያቆናት ደግሞ በመልሳቸው ላይ፥ ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት አለው የሚለው አስተምህሮ መናፍቃዊ አስተምህሮ ነው፥ ትምህርቱም የመጣው በካቶሊኮችና በሌሎች ከውጭ በመጡ ሰዎች ነው በማለት ይህን አስተምህሮ በጥብቅ እንደሚቃወሙት ገልጸዋል።

ኢየሱስ በአሁኑ ጊዜ ስለሚገኝበት ባሕርይው ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ገና አላጠናንም። ስለዚህ በሚቀጥለው ትምህርታችን ላይ ኢየሱስ አሁንም እግዚአብሔር– ሰው፥ ወይም ሁለቱንም ማለትም እግዚአብሔርም ሰውም ስለ መሆኑ ጠለቅ አድርገን እንማራለን። ለመሆኑ ቃለ መጠይቅ

ያደረጋችሁላቸው ሦስት ሰዎች ለዚህ ምን መልስ ሰጡ? እኔ በበኩሌ ከጠየቅኋቸው ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ ክርስቶስ በአሁኑ ጊዜ አምላክ ብቻ ነው ብለው ነው የመለሱት። ሌሎች ደግሞ ጨምረው የመለሱት፥ እርሱ አምላክ ብቻ በመሆኑ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርባቸው የሚችል አማላጅ እንደሚያስፈልጋቸው ነው። እነርሱ እንደሚያምኑት ኢየሱስ አማላጅ ተመላጅም ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ሰው ስላልሆነ በአሁኑ ጊዜ አማላጅ ሊሆን አይችልም። በሌላ ትምህርታችን ላይ ኢየሱስ አሁን ስለሚገኝበት የባሕርይ ሁኔታና፥ ኢየሱስ በአማላጅነት ተግባሩ ስለሚኖረው ስፍራ መለስ ብለን እናጠናለን።

26ኛ ጥያቄ፡– ትናንትናና ዛሬ ላቀረባችኋቸው ቃለ መጠይቆች ያገኛችኋቸውን መልሶች አንብቡ። ሀ) መልሶቹ እኔ ለአቀረብኋቸው ቃለ መጠይቆች ከተሰጡት መልሶች ጋር በምን ይመሳሰላሉ? ለ) እንዴት ይለያሉ? ሐ) ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የተጠየቁት ሰዎች በሰጡት መልሶች በክርስቶስ ማንነት ላይ ስላላቸው ግንዛቤ የእናንተ አጠቃላይ አስተያየት ምንድን ነው?

ክርስቶስ መለኮታዊና ሰብአዊ የሆነ ሁለት ባሕርያት እንዳሉት ማስተማር ለብዙዎቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አማኒያን በጣም አስቸጋሪ መሆኑ ግልጽ ነው። ኢየሱስ ሁለት ባሕርያት አሉት ብላችሁ ብታስተምሩ ለብዙዎቹ የሚመስላቸው ኢየሱስን ራሱን በራሱ እንደ ከፋፈላችሁት ነው። ለአንዳንዶቹ ደግሞ ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር አይደለም እንዳላችሁ ሆኖ ይታያቸዋል። ሌሎች ደግሞ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ መጤ ሃይማኖት ከውጭ ተቀብላችሁ የምታስተምሩ ይመስላቸዋል።

ክፍል ሁለት፥ የተሠገዎ ምሥጢር፡– ኢየሱስ እንዴት አምላክም ሰውም፥ ሁለቱንም ሊሆን ይችላል?

ባለፉት ተከታታይ ሳምንታት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስለ ተሠገዎ ምሥጢር ስንማር ቆይተናል። ይህን የተሠገዎ ምሥጢር አስተምህሮ፥ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ ለማጠቃለል ተመራጩ መንገድ ምንድን ነው? ኢየሱስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው ማለት ምን ማለት እንደሆነ፥ ነገ የራሳችሁን የማጠቃለያ አሳብ ትጽፋላችሁ። ነገር ግን ይህን የማጠቃለያ አሳባችሁን ከመጻፋችሁ በፊት፥ ለዚህ ተግባር ድጋፍ የሚሰጡዋችሁን ልዩ ልዩ ቁልፍ ጥቅሶች አስቀድመን እናጠናለን። እነዚህ ጥቅሶች የሚከተለውን ጥያቄ ለመመለስ ይረዱናል። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ እንዴት ሙሉ በሙሉ አምላክና ሙሉ በሙሉም ሰው ሊሆን ቻለ? እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ በገዛ ፈቃዱ ከመለኮታዊ ባሕርያቱ ውስጥ አንዳንዱን መጠቀም ትቷል የሚሉ ይመስላሉ። እነዚያ ባሕርያት በወቅቱ ያልተለዩ ስለነበሩ በፈቀደ ጊዜ ሊጠቀምባቸው ይችል ነበር። ነገር ግን በአብዛኛዎቹ ጊዜያት ያለመጠቀምን ነበር የመረጠው። ይጠቀምባቸው የነበረውም የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ሲሆን ብቻ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ ሁሉን ነገር ያውቅ ነበር። ነገር ግን የአብ ፈቃድ ካልሆነ በቀር በገዛ ፈቃዱ መለኮታዊ እውቀቱን አይጠቀምበትም ነበር። እርሱ ሁሉን ቻይ ነበር። ሆኖም በገዛ ፈቃዱ በመለኮታዊ ሥልጣኑ ከአባቱ ፈቃድ ውጭ ለመጠቀም አልፈለገም። በየትኛውም ስፍራ በአንድ ጊዜ ሊገኝ ሲችል ነገር

ግን አብዛኛውን ጊዜ ራሱን በነበረው አካል ውስጥ ወስኖ፥ የአባቱ ፈቃድ ሲሆን ብቻ በሌላ ስፍራ ይገኝ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ ራሱ በፈቃዱ አንዳንድ መለኮታዊ ባሕርያቱን ትቶ የአባቱ ፈቃድ ሲሆን ብቻ ይጠቀምበት ነበር።

እነዚህን እውነታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዴት እንመለከታቸዋለን? አስቀድመን የምንመለከተው፥ ኢየሱስ ሁልጊዜ የእግዚአብሔር አብን ፈቃድ በተግባር ላይ እንዳዋለ ነው።

27ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 8፡29 አንብቡ። ኢየሱስ ሁልጊዜ ምን ያደርግ ነበር?

28ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 6፡38 አንብቡ። ኢየሱስ ምን ሊያደርግ ከሰማይ ወደ ምድር መጣ? ለ) ኢየሱስ ያላደረገው ምንድን ነው?

29ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 4፡34 አንብቡ። የኢየሱስ ምግብ ምን ነበር?

30ኛ ጥያቄ፡– ዮሐንስ 5፡30 አንብቡ። ሀ) ኢየሱስ በራሱ ምን ያደርግ ነበር? ለ) ኢየሱስ የማንን ፈቃድ አይፈጽምም ነበር? ሐ) ኢየሱስ የማንን ፈቃድ ይፈጽም ነበር?

31ኛ ጥያቄ፡– ሉቃስ 22፡42 አንብቡ። ኢየሱስ ወደ መስቀል የመሄድና ያለመሄድ ታላቅ ፈተና ሲያጋጥመው ለአብ ምን አለ?

ኢየሱስ በአገልግሎቱ ሁሉ ላይ የእርሱ ፈቃድ ለአባቱ ፈቃድ መገዛት መሆኑን በግልጽ አሳይቷል። የፈለገውን አያደርግም ነበር። አባቱ እንዲያደርግ የሚፈልገውን ብቻ ያደርግ ነበር። በዮሐንስ 8፡29 ላይ ዘወትር አባቱን ደስ የሚያሰኘውን እንደሚያደርግ ተናግሮአል። በዮሐንስ 6፡38 ውስጥም፥ እርሱ ከሰማይ የወረደው የላከውን ፈቃድ ለማድረግ እንጂ የራሱን ፈቃድ ለማድረግ እንዳልሆነ ተናግሯል። እንደዚሁም በዮሐንስ 4፡34 ላይ ደግሞ ኢየሱስ እርሱ ስለሚረካበት ነገር ሲናገር፥ የእርሱ ምግብ የላከውን ፈቃድ ማድረግ መሆኑን ገልጾአል። በዮሐንስ 5፡30 እርሱ በራሱ ሥልጣን ምንም እንደማያደርግ፥ ነገር ግን የላከውን ፈቃድ ብቻ እንደሚያደርግ አረጋግጧል። ከዚህም በስተቀር ኢየሱስ የራሱን ፈቃድ ሳይሆን የአባቱን ፈቃድ እንደሚያደርግ በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራም አሳይቷል። እርሱ የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ በመስቀል ላይ ፍዳ ሲቀበል እንኳ በገዛ ፈቃዱ ከአባቱ ሊለይ አልፈለገም። እናም የአባቱን ፈቃድ ሊፈጽም ሲል የራሱን ፈቃድ መተው ነበረበት።

ኢየሱስ በሕይወቱ ሙሉ ያደረገው የአባቱን ፈቃድ ብቻ መፈጸም ነበር። እንዲህ ማለት ኢየሱስ በመለኮታዊ ባሕርይው የሚጠቀመው የአባቱ ፈቃድ ሲሆን ብቻ ነው ማለት ነው። በዚህ በመለኮታዊ ባሕርይውም ይጠቀም የነበረው ተአምራት ሲሠራ ነበር። እነዚህ ተአምራትም ሽባውን ሰው መፈወስ፥ ዳቦዎቹንና ዓሣዎቹን ማበርከት የመሳሰሉት ነበሩ (ዮሐንስ 5፡8፤ 6፡1–15)። ኢየሱስ መለኮታዊ ዕውቀቱን ይጠቀም የነበረው ስለ ሰዎች የተደበቀ ምሥጢር ካለ ለማውጣት ሲል ነበር። ለዚህ የሚጠቀሰው የሳምራዊትዋ ሴት ቀደምት ሕይወት (ዮሐንስ 4፡17) ወይም በማርቆስ 2፡ ላይ እንደተጠቀሰው፥ ሰዎች ስለሚያስቡት ማወቁ ነው። አንድ ጊዜ ደግሞ ኢየሱስ በመለኮታዊው ባሕርይ ከአንድ ስፍራ አልፎ በአንድ ጊዜ በሌላ ስፍራ የሚገኝ መሆኑን ለናትናኤል፥ ከበለሲቱ ዛፍ ሥር ሆነህ አየሁ

(ዮሐንስ 1፡48) ባለው ጊዜ ገልጾታል። ይሁን እንጂ ኢየሱስ መለኮታዊ ዕውቀቱንና ኃይሉን ያልተጠቀመባቸውም ጊዜያት ነበሩ። እንደዚሁም ኢየሱስ አምላክ ሳለ መለኮታዊ ዕውቀቱን ወይም ሥልጣኑን ትቶ ሰዎች ተወስነው በሚኖሩበት ውስን ሁኔታ ውስጥ የሚኖርበት ጊዜ ነበር።

32ኛ ጥያቄ፡– ማርቆስ 13፡32 አንብቡ። ኢየሱስ ልጅ አያውቅም ያለው ምንድን ነበር? ለ) ኢየሱስ በእውነት አምላክና ሁሉን የሚያውቅ ሆኖ ሳለ በምን ምክንያት ይህን ያለ ይመስላችኋል?

ኢየሱስ ከሚሰቀልበት አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውጭ ሆኖ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ይነጋገር ነበር። በዚህንም ጊዜ የኢየሩሳሌም ከተማ ከፈረሰች በኋላ ሥቃይና ስደት እንደሚመጣና ሐሰተኛ መሢሆችም እንደሚነሡ ነገራቸው። በማርቆስ 13፡26 ውስጥ ከዚህ ሁሉ መከራ በኋላ የሰው ልጅ በታላቅ ኃይልና ክብር በደመና እንደሚመጣ አስጠንቅቋቸዋል። ግን ይህ መቼ ይሆናል? በማርቆስ 13፡32 ደግሞ ያቺን ቀንና ያቺን ሰዓት ከአብ በቀር ማንም ሊያውቃት እንደማይችል የሰማይ መላእክትም እንደማያውቁ፥ ወልድም ራሱ ቢሆን እንደማያውቃት ኢየሱስ ተናግሮአል።

ግን ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ኢየሱስ ይህን ሁኔታ ለደቀ መዛሙርቱ በነገራቸው ጊዜ ፍጹም አምላክ ነበር። እንደ ፍጹም አምላክነቱ ደግሞ በእርግጥ ወደ ምድር ዳግም የሚመለስበትን ጊዜ ያውቅ ነበር። እንዴት ለደቀ መዛሙርቱ የሚመለስበትን ጊዜ እንደማያውቅ ይናገራል? አንዳንዶች ይህን ሲመልሱ ኢየሱስ የሚመለስበትን ጊዜ በእርግጥ ያውቃል፥ ግን ይህን ያለው በትሕትና መንፈስ ነው ይላሉ። እግዚአብሔር አብን ለማክበርና በዚሁ መሠረት ደቀ መዛሙርቱም እግዚአብሔር አብን እንዲያከብሩ ለማሳሰብ ነው። ስለዚህ የሚመለስበትን ቀንና ሰዓት እንደማያውቅ ነገራቸው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ አሳብ ሲሰጡ፥ ኢየሱስ በእርግጥ የመመለሻውን ጊዜ ያውቅ ነበር። ነገር ግን እርሱ ለደቀ መዛሙርቱ ሊነግራቸው የፈለገው የእርሱ ዳግም መምጣት የእነርሱ ጉዳይ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጉዳይ መሆኑን ሊያስጠነቅቃቸው ብሎ ነው ይላሉ። ይህ ጉዳይ ምሥጢር ሆኖባቸው ቀርቷል።

የዚህ ገለጻ ችግር፥ ኢየሱስ ዳግም የሚመጣበትን ጊዜ እያወቀ ለደቀ መዛሙርቱ እንዳላወቀ ሆኖ ከነገራቸው እንዳታለላቸው ይቆጠር ነበር። ኢየሱስ ግን በፍጹም ኃጢአት አላደረገም፤ ዋሽቶም አያውቅም። አላታለለምም። ኢየሱስ የሚመለስበትን ጊዜ አለማወቁን ለመናገሩ የተሻለ መልስ አለ። እርሱም እንደ ሰብ–አምላክነቱ በፈቃዱ አንዳንድ ባሕርያቱን አልተጠቀመም። እግዚአብሔር በመሆኑ ሁሉን ያውቃል። ነገር ግን በሰብአዊ ባሕርይው ለመኖር ሲል በራሱ ፈቃድ ከባሕርያቱ በአንዳንዶቹ መጠቀሙን ተወ። እርሱ በመለኮታዊ ዕውቀቱ ይጠቀም የነበረው፥ በዚህ እንዲጠቀም የአባቱ ፈቃድ ሲሆን ብቻ ነበር።

33ኛ ጥያቄ፡– ማርቆስ 9፡21 አንብቡ። ኢየሱስ እውነተኛ አምላክ ሳለ ሁሉን እያወቀ ታዲያ ለምን ይህን ጥያቄ ያቀረበ ይመስላችኋል?

በማርቆስ 9፡14 ውስጥ ኢየሱስ ከመገለጥ ተራራ፥ ከጴጥሮስ፥ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር ወርዶ ገና ከተቀሩት ደቀ መዛሙርቱ ጋር መደባለቁ ነበር። ያኔውኑ አንድ ሰው ዲያብሎስ ካደረበት ልጁ ጋር እዚያው ሆኖ አገኙት። ሌሎቹ የጌታ ደቀ መዛሙርት ዲያብሎሱን ከልጁ ውስጥ ሊያስወጡ አልቻሉም ነበር። ሰውዬውም ልጁን ወደ ኢየሱስ አመጣው። ልጁም ወደ ኢየሱስ ፊት እንደ ቀረበ በውስጡ የነበረው ዲያብሎስ የልጁን ሰውነት እንደሚጥል በሽታ አድርቆ እንደ በድን አደረገው። ከዚያም ኢየሱስ የልጁን አባት እንዲህ ሲል ጠየቀው፥ «ይህ በሽታ ከጀመረው ምን ያህል ጊዜ ነው?» ኢየሱስ እንደ አምላክነቱ ሁሉን ነገር ስለሚያውቅ የዚህን ጥያቄ መልስም ባወቀ ነበር። በተጨማሪም ጥያቄውን ያቀረበበት ምክንያት አንዳንድ መረጃ ለማግኘት በመፈለጉ ይመስላል። ኢየሱስ ሰብአዊ ሕይወትን እንደ ተራ ሰው ለመኖር በገዛ ፈቃዱ በመለኮታዊ ዕውቀቱ መጠቀምን ተወ። ይሁን እንጂ ይህኔም ቢሆን ሁሉንም የማወቅ ባሕርይ ነበረው። ሆኖም ግን ይህን ባሕርይውንም የተጠቀመው የአብ ፈቃድ ሲሆን ብቻ ነበር።

ኢየሱስ ይህን ጥያቄ ያቀረበው መረጃ ለማግኘት ይመስላል። እንደ አምላክነቱ ልጁ በዲያብሎስ ተይዞ የቆየበትን ጊዜ ያውቃል። ግን በዚህ ዕውቀቱ አልተጠቀመበትም። ራሱን ገድቦ ልጁ ዲያብሎስ ካደረበት ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የልጁን አባት ጠየቀ። ይህን ያደረገውም መረጃ ለማግኘት ነበር።

34ኛ ጥያቄ፡— ዮሐንስ 14፡28 አንብቡ። ሀ) ኢየሱስ እርሱ ከእኔ ይበልጣል ያለው የነበረው ማንን ነው? ለ) ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ አምላክ ከሆነ እንዴት እንደዚህ ይላል? ይህን ሲልስ ምን ማለቱ ነው?

35ኛ ጥያቄ፡— ዮሐንስ 10፡30 አንብቡ። ሀ) ኢየሱስ አንድነቱ ከማን ጋር ነው? ለ) እንዲህስ ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

በዮሐንስ 14፡28 ውስጥ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ አባቴ ከእኔ ይበልጣል ሲል ነገራቸው። ኢየሱስ ይህን ሲል ምን ማለቱ ነበር? ይህን ሲል አብ ሙሉ በሙሉ አምላክ ሲሆን፥ እርሱ ግን ከአምላክ ያነሰና የአምላክ አምሳል ነው ማለት ነው? አይደለም። እንዲህ ማለቱ አይደለም። ምክንያቱም ኢየሱስ በማንኛውም አኳኋን ሙሉ በሙሉ አምላክ ስለ መሆኑ ቀደም ሲል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ ማስረጃዎችን አጥንተናል። በተጨማሪም በዮሐንስ 10፡30 ኢየሱስ እርሱና አብ አንድ መሆናቸውን ገልጾአል። እንዲህ ማለትም እርሱና አብ አንድ የሆነ ባሕርይ አላቸው ማለት ነው። እግዚአብሔር አብ ሕዝቡን እንደሚከላከል ሁሉ እርሱም ይከላከላል (ዮሐ. 10፡28–29)። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ እንኳን የእግዚአብሔር ባሕርይና ፈቃድ ነበረው። ኢየሱስ በአምላክነቱ ከአብ ጋር አንድ ነው። ነገር ግን ወደ ምድር ሲመጣ በመለኮታዊ ሥልጣኑ ሙሉ በሙሉ ሳይጠቀም መኖርን መረጠ። በዚህ ሥልጣኑ ወይም በመለኮታዊ ዕውቀቱ የተጠቀመው የአብ ፈቃድ ሲሆን ብቻ ነበር። ስለዚህ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር ቢሆንም፥ በገዛ ፈቃዱ እንደ ተራ ሰው ሆኖ ኖረ። በሦስተኛ ትምህርታችን ላይ እንደተመለከትነው፥ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ በገዛ ፈቃዱ ራሱን ትሑት አድርጎ ከብሩን ከአብ አሳነሰ።

ራሱንም ለአብ አስገዝቶ የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር በመለኮታዊ ባሕርያቱ በአብዛኛው ሳይጠቀም ኖረ። በእርሱነቱ ከአብ ያነሰ አልነበረም። ነገር ግን የሰው ልጆችን ኑሮ ለመኖር ራሱንና ማዕረጉን በፈቃዱ ከአብ ዝቅ ማድረግን ፈቀደ።

ኢየሱስ ከአምላካዊ ባሕርይው ሁሉ ጋር እንዴት እግዚአብሔር ሊሆን እንደ ቻለና በዚህ ባሕርይው ሳይጠቀም ሰው ሆኖ እንደ ኖረ አንድ ምሳሌ እነሆ። እስቲ ዕድሜያቸው ከ4–5 የሚደርስ ሕፃን በግቢያቸው ውስጥ ኳስ ሲጫወቱ አስቡ። የልጆቹ አባት ወደ እነርሱ ዘንድ መጥቶ አብሮአቸው መጫወት ይጀምራል እንበል። ነገር ግን አባታቸው ከልጆቹ ይልቅ ትልቅ ነው፥ ጠንካራ ነው፥ ደግሞም ፈጣን ነው። ነገር ግን በልጆቹ አቅም መሠረት ለመጫወት ምን ማድረግ አለበት? ተንበርክኮ ከልጆቹ ጋር ኳስ መጫወት አለበት። አሁን እርሱ ቁመቱ ከልጆቹ ቁመት ጋር እኩል ሲሆን፥ የአጨዋወት ፍጥነቱ ከትንንሾቹ ልጆች ፍጥነት ጋር እኩል ይሆናል። ይሁን እንጂ አባታቸው አሁንም ቢሆን፥ ያ ቁመቱ፥ ያ ጉልበቱና የትልቅ ሰው ፍጥነቱ አብሮት አለ። ከእነዚህ ልጆች ጋር በሚጫወትበት ጊዜ በተጠቀሱት የችሎታው ባሕርያት ሁሉ አይጠቀምም። ራሱን ዝቅ አድርጎ ልጆቹ ከሚጫወቱበት ሁኔታ ጋር ያስማማል። ሆኖም በድንገት ብድግ ብሎ እንደ ትልቅ ሰው ሊጫወት ይችላል። ነገር ግን በገዛ ፈቃዱ በትልቅ ቁመቱ በጉልበቱና በፍጥነቱ አለመጠቀምን መርጧል። በዚህ ሁኔታ ኢየሱስ ሰው ሆኖ ሲመጣ፥ ሙሉ በሙሉ ከአምላክነት ባሕርይው ጋር አምላክ ሆኖ ኖረ፥ ሆኖም በገዛ ራሱ ፈቃድና ምርጫ፥ የአብ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር፥ በመለኮታዊው ባሕርይው ሙሉ በሙሉ አልተጠቀመም።

አምስተኛ ቀን

36ኛ ጥያቄ፡– በተማራችሁት ትምህርት አማካይነት ስለ ክርስቶስ አምላክነትና ሰብአዊነት አስቡ። ስለ ተሠገዎ ምሥጢር በመጽሐፍ ቅዱስ ከፍለ ምንባቦች ውስጥ የተማራችሁትን አስታውሱ። እንደዚሁም ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥና በኢትዮጵያ ስለ ተሠገዎ ምሥጢር የተማራችሁትን ታሪክ መለስ ብላችሁ አስታውሱ። ስለ ኢየሱስ፥ ሁለት ባሕርያት በአንድ አካል ሲባል ስላለው ችግር አስቡ። እንደዚሁም ክርስቶስ አንድ ባሕሪ ነው ሲባል ስላለውም አስቸጋሪ ሁኔታ አስቡ። ከዚህ በኋላ ስለ ተሠገዎ ምሥጢር ራሳችሁ ያገኛችሁትን ግንዛቤ ጠቅለል ባለ ሁኔታ በማስታወሻ ደብተራችሁ ውስጥ ጻፉት። በጽሑፋችሁ ውስጥም ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ሰብአዊና መለኮታዊ መሆኑን በግልጽ ሊያስረዱ በሚችሉ ቃላት ተጠቀሙ።

የምታጠቃልሉበት አንቀጽ ልዩ ልዩ ጠቃሚ ነጥቦችን ማካተት አለበት። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ቀድሞም ሆነ ዛሬም እንደ እግዚአብሔር አብ ሁሉ እርሱም አምላክ መሆኑን አጉልቶ ያሳይ። ማጠቃለያው ኢየሱስ ክርስቶስ ፊትም ሆነ አሁን ኃጢአት ካለማድረጉና የኃጢአት ባሕርይ ካለመላበሱ በስተቀር እንደ እኛው ሰው መሆኑን ያትኩርበት። እንደዚሁም ጽሑፉ ኢየሱስ አምላክ የመሆኑ ነገር ሰብአዊ ባሕርይውን ከእኛ ሰብአዊነት እንደማይቀንሰውና እንዲሁም ሰው የመሆኑ ነገር መለኮትነቱን

ከእግዚአብሔር አብ ዝቅ እንደማያደርገው አጽንኦት ይሰጠው። በአንቀጹ ውስጥ የኢየሱስ ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰብአዊነት በአንድ አካል የተዋሐዱ መሆናቸውና ኢየሱስ ሁልጊዜ በሚያደርገው ሁሉ እግዚአብሔርም – ሰውም እንደ ነበረ አጽንኦት ይሰጠው። ኢየሱስ አንዳንድ ጊዜ አምላክ በሌላ ጊዜ ሰው አልነበረም። አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ በነበረው መለኮታዊ ባሕርይ ዕውቀትና ኃይል አልተጠቀመም። ነገር ግን የእነዚህ ሁሉ ባሕርያት ባለቤት ነበር። የሚጠቀምባቸው የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ሲሆን ብቻ ነበር። በምትጽፉት ማጠቃለያ ኢየሱስ ስንት ባሕርያት እንዳሉት መግለጽ አስፈላጊ አይደለም። መግለጽ ያለባችሁ ኢየሱስ ቀድሞም ሆነ አሁን በአንድ አካል የተዋሐደ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መሆኑን ብቻ ነው።

ሳምንታዊ የስብሰባ ጊዜ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ፡– የቡድኑ መሪ በዚህ ሳምንት ከቀረበው ትምህርት ወይም ጥቅስ አንዱን መርጦ በእርሱ ላይ በመመሥረት ከ5–10 ደቂቃ የሚደርስ የአምልኮ ፕሮግራም ያዘጋጅ።
2. ሳምንታዊ የጸሎት ጊዜ፡– አሥር ደቂቃ በጸሎት አሳልፉ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነና ሰውን በማያስከፋ መንገድ ማካፈል እንድንችል እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጠን እንጸልይ።
3. ክለሳ፡– ለ15 ደቂቃ በዚህ ሳምንት የተማራችሁትን ትምህርት ከልሱትና የትኞቹ ጥያቄዎች ለመመለስ አስቸጋሪዎች እንደ ነበሩና ተማሪዎቹም የተማሩትን ለመመልከት ሞክሩ።
4. ተወያዩ፡–

ሀ) በዚህ ሳምንት ከተማራችሁት ታሪክ ውስጥ የትኛው ክፍል ከአካባቢያችሁ ሰዎች ጋር ስለ ክርስቶስ ለመወያየት ይጠቅማል?

ለ) ለእያንዳንዱ ሰው ስለቀረበው ቃለ መጠይቅ ውጤት ተወያዩ። በአካባቢአችሁ የሚኖሩ አብዛኛዎቹ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ አምላክነትና ሰብአዊነት እምነታቸው ምንድን ነው?

ሐ) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለሦስት ሰዎች ያቀረባችኋቸውን ጥያቄዎች መለስ ብላችሁ አስቡ። እናንተ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ባትሆኑ ኖሮ፥ አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያናችሁ አባላት እነዚህን ጥያቄዎች እንዴት ይመልሱ ነበር?

መ) ኢየሱስ በአንድ አካል በአንድ ጊዜ ፍጹም አምላክ ፍጹምም ሰው ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ ደህና አድርጋችሁ መግለጽ የምትችሉበትን መንገድ መወያየት ጀምሩ። የቡድኑ አባላት የጻፉትን ማጠቃለያ ጽሑፍ ከጓደኞቻቸው ጋር ተቀባብለው አንዱ የሌላውን ጽሑፍ በማንበብ አሳብ ይለዋወጡ። ከዚያም ከየጽሑፉ ውስጥ ያገኟችኋቸውን አንኳር አሳቦች አውጥታችሁ ተወያዩባቸው።